## (፴፱) ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር (የደቡብ ባፕቲስት ፤ ቦርን አጌን)

ጂሚ ካርተር በደቡብ ባፕቲስት የክርስትና እምነት ሰባኪ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ኾኖ ሲመረጥ የመጀመሪያ ሰው ነው ። ጂሚ ካርተር ያደገው በትንሽ ከተማ ፕሌይንስ በምትባል በደቡቡ ግዛት በጆርጂያ ውስጥ ነው። በዚያ ሲኖር የአካባቢው የባፕቲስትቦርን አጌን ክርስቲያን አገልጋይ ኾኖ አደገ ። በቅጽል ስሙ የሚታወቀው ቀላል የገጠር ልጅ (ሲንፐል ካንትሪ ቦይ) በመባል ነው።

ጂሚ ካርተር የኮሌጅ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ባሕር ኃይል (ናቫል አካዳሚ) በመግባት ተምሮ ባገኘው ውጤት የክብር ማዕረግ አግኝቶ በማጠናቀቅ በባሕር ኃይል ውስጥ ተቀጥሮ ሠርቷል ። እንዲኹም የኒኩሊየር ፊዚክስ አጥንቶ በዚህ ሙያው ሲሠራ ቆይቷል ። በ38 ዓመቱ ግዛቱን (እስቴቱን) ወክሎ የሴኔተር አባል ኾኖ አገልግሏል። ከዚያ በ46 ዓመቱ የጆርጂያ አስተዳደር አገረ ገዢ ለመኾን ተመርጦ አገልግሏል።

ጂሚ ካርተር ዲሞክራቲክ ፓርቲውን ወክሎ ጀራልድ ፎርድን በጥቂት ብልጫ አሸንፎ የፕሬዚዳንትነትን ቦታ ይዞ የአሜሪካ 39ኛው ፕሬዚዳንት (1977-1981)ኾነ ። ለዚህ ምርጫ ውድድር አሸናፊ ፕሬዚዳንት ለመኾን ያበቃው ከቬይትናም ጦርነት እንደዚሁም ከወተር ጌት ውርደት ትምህርት ስላገኘ የአሜሪካንን ሕዝብ ምንም እንደማይዋሸው ቃል ስለገባና በተጨማሪ የቦርን አጌን የክርስትና እምነት አገልጋይ ነኝ ብሎ ታማኝ እንደኾነ ቅስቀሳ ስላደረገ ነው። በዚህም የፕሬዚዳንትነት ውድድር 56% በመቶ የደቡብ የባፕቲስት ክርስትና እምነት አባላት መርጠውታል፡

የፕሬዚዳንትነት ቦታውን ከያዘ በኋል ሥራ አጥን ለማጥፋት ብዙ ታግሏል። በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው መጋቢት 1979 ግብፅን እና እስራኤልን እጅ ለእጅ በማጨባበጥ ሰላም ለማምጣት ጥረት አድርጓል። የኢራን ተማሪዎች በኢራን ያለውን የአሜሪካ ኢምባሲ በመያዝ 52 አሜሪካውያንን አፍነው (ሆስቴጅ) በመያዛቸው አሜሪካውያንን አስቆጥቶና አስደንግጦ ስለነበረ ለማስለቀቅ በመደራደር ብቻ ዓመት በመፍጀቱ ከአሜሪካውያን ዘንድ ዝና እና ድጋፍ ቀንሶበታል። በተጨማሪም 125,000 የኪዩባ ስደተኞች አሜሪካ በመግባታቸው በዚህ ኹሉ የተነሳ በ1980 ምርጫ ጊዜ እነዚህ ጉዳዮች ዋና የምርጫ መሸነፊያ ምክንያት ኾነው ቀርበዋል ። እነዚህ በኢራን የተያዙት አሜሪካውያን



በተለቀቁ ጊዜ ዐዲሱ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን በአሸናፊነት ቢሮውን ተረክቦት ነበር።

በዚሁ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ዘመን በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው ወዳጅነት ተቋረጠ ። ዋናው ምክንያት በ1977 እስከ 1979 ሶማሌያ ኢትዮጵያን በጦርነት ስትወር የጦር መሣሪያ ግዢ ማዕቀብ በኢትዮጵያ ላይ ስለጣለ እና ቀደም ብሎ በጥሬ ገንዘብ የተገዛውንም የጦር መሣሪያ ስለከለከለ ነው።

ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር በአኹኑ የጡረታ ዕድሜው ከባለቤቱ ከሮዛሊን እስሚዝ ጋራ በመኾን የሰበአዊ መብት ተከራካሪነትን ሥራቸው አድርገውት ይዘውታል። በዚህ ሥራ በየአህጉሩ ይዞራሉ። በይበልጥም በአፍሪካ ቶጎ፣ ጋና፣ ማሊና ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ተጉዘዋል ። ኢትዮጵያ ውስጥ በደቡብ ክፍል በወባ በሽታ የሚያዙትን ለማርዳት በግል ከባለቤቱ ጋር ጥረት አድርገዋል ። በግንቦት ወር 2005 ተደርጎ በነበረው የመንግሥት የምርጫ ውድድር ላይ በታዛቢነት በመገኘት ተሳትፎ አድርገዋል። ነገር ግን ምርጫው ተጭበርብሯል ተብሎ ስለታመነበት እሱ ደግሞ ትክክል መኾኑን ለመግለጽ በመሞከሩ ከፍተኛ ተቃውሞ ይበልጥ የአሜሪካ ነዋሪዎች በኾኑ ኢትዮጵያውያን ደርሶበታል።

ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር በ2002 ኖቤል የሰላም (ኖብል ፒስ ፕራይዝ) ሽልማት ተሸልሟል።

የኖብል ሽልማት የተሸለመበት ምክንያት ለ10 ዓመት ለሰላም እና ለሰብአዊ መብት ባደረገው አስተዋጽኦ ነው ። ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ በኢራቅ ላይ ያደረገውን ወረራ ይቃወማል ። በትርፍ ጊዜው ፓልማ ጆርጂያ ባለው የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። በዚህ ትምህርቱ "ኹሉም የሰው ዘር በእግዚአብሔር ዓይን እኩል ነው " ይላል። ይህም የአሜሪካ የነጻነት አዋጅ መንፈስ ነው።

## (፵) ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን (ዲሳይፕል ኦፍ ክራይስት)

አሜሪካ የተመሠረተችው እግዚአብሔር የደኅንነታቸው የማዕዘን ድንጊያ እንደኾነ በሚያምኑ ሰዎች ነው ። አኹንም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መኾኑን እርግጠኛ መኾን እንደሚኖርብን እገነዘባለሁ። በአንጻሩ ደግሞ እኛ ራሳችን ከእርሱ ጋር መኾናችንን መረዳት የግድ ይኾናል፤ ይል ነበር ።

ሮናልድ ሬጋን 40ኛ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ኾኖ ሲመረጥ ዕድሜው 69 ዓመት ነበር (1981-89) ። የተወለደበት ቦታ ኢሊንዮስ ግዛት ውስጥ ታምፒኮ በምትባለው ቦታ ሲኾን ያደገበት ቦታ ዲክሶን ይባላል ። በልጅነቱ በትምህርት ቤት የአሜሪካ እግር ኳስ ጨዋታ ይጫወት ነበር። እንደዚሁ የውሃ ዋናተኞች ቡድን ዋና መሪ (ካፒቴን) በመኾን አገልግሏል።

ሮናልድ ሬጋን ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ በሬዲዮ የስፖርት ክፍል ሪፖርት አቅራቢ ኾነ። በዚህ የጋዜጠኝነት የሪፖርት አቅራቢነት ሙያ በ1937 የቺካጎ የኳስ ጫወታ ክለብ ወደ ካሊፎርንያ ሊጫወት ሲኼድ ቡድኑን ተከትሎ ግጥሚያውን በዜና ሲያሰራጭ በኳሽ ወዳጁ ሕዝብ ታዋቂነትንና አድናቆትን አገኘ ። ወዲያው ለፊልም ሥራ ታጭቶ በፊልም ሠሪነት ኮከብ (እስታር) ኾኖ በመታየት ወደ 50 የሚደርሱ ፊልሞችን ሠርቷል። እነዚህ በየጊዜው በቴሌቪዥን ሲተላለፉ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትንና ገናናነትን አስጡት።

በአገር ፖለቲካ ላይ ተሳትፎ በማድረግ የዲሞክራቱ ሀሪ ትሩማን በ1948 ለምርጫ ሲወዳደር ሬጋን ቅስቀሳ ያደርግ ነበር። ነገር ግን በ1950 አመለካከቱ ተለውጦ የሪፑብሊካን ደጋፊ መኾን ጀመረ። ከዚያም ከ1970 እስከ 1975 የካሊፎርኒያ ግዛት አገረ ገዥ ኾኖ መርቷል።

ሮናልድ ሬጋን በ1980 ሪፑብሊኩንን ወክሎ ለአሜሪካ የፕሬዚዳንትነት ምርጫ ተወዳድሮ ጂሚ ካርተርን በማሸነፍ የቀድሞ የፊልም ሠሪ የአሜሪካንን ሕዝብ ለመምራት በዋይት ሀውስ ከባለቤቱ ከነንሲ ሬጋን ጋራ በመግባት መሥራት ጀመረ ። ፊቱ ፈገግታ የተመላበት ደስተኛ የኾነ እና ሃይማኖተኛ ሰው ነበረ። ፕሬዚዳንት ከመኾኑ በፊት "ክራይስት ቸርች" ኹል ጊዜ እየኼደ ይጸልይ ነበር ። ፕሬዚዳንት ከኾነ በኋላ ግን አንድ ኹለት ጊዜ ዋሽንግተን በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት በጥበቃ (በሴኩሪቲ) ታጅቦ ኹል ጊዜ ሲኼድ ምእመናኑን የሚረብሽ ኾኖ ስላገኘው አለመኼዱን መርጦ አቋረጠ።

በ1981 ኮሎምቢያ ተብላ የተጠራች ሮኬት ወደ ጠፈር ተልካ በአየር ላይ ከፍ እንዳለች ፈነዳች ። እንዲሁም በአገሪቷ ታሪክ የበላይ ፍርድ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የሴት ዳኛ የተመረጠችበት በዚሁ ዓመት ሲኾን የመጀመሪያ ሰው ሰራሽ (የአርቲፍሻል) ልብ በ1982 ሥራ ላይ የዋለበት ጊዜ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሶቭዬት ኅብረት ፕሬዚዳንት ሚካኤል ጎርባቾቭ ጋራ በዋሽንግተን ስለ ኒኩሊየር ሚሳኤል ቅነሳ የተፈራረሙበት እንዲሁም ሚካኤል ጎረቫቾቭ የበርሊንን ግንብ



እንዲያፈርስ የተደረገበት የቀዝቃዛው ጦርነት ያከተመበት ይወድቃል
ተብሎ ለዘላለም የማይታሰበው የኮሚኒዝም ሥርዓት የወደቀበት ጊዜ
ነው።[201]

ፕሬዚዳንት ሬጋን ኹለት ዙር ከመራ በኋላ በ1989 ከዋይት
ሀውስ ወጥቶ ወደ ካሊፎርንያ በመኼድ በዚያ ኑሮውን ጀመረ ።
በኋላም በአልዛይመር በሽታ ተይዞ ለዐሥር ዓመት ሲሰቃይ ቆይቶ በ9
ዓመቱ በሰኔ ወር በ2004 ዐረፈ።

## (፲) ፕሬዚዳንት ጆርጅ ሄርበርት ዎከር ቡሽ (ኤጲስኮፓል)

ጆርጅ ሄርበርት ዎከር ቡሽ 41ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ነው (1989-
1993)። ኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን ተከታይና በፖለቲካ የረዥም
ጊዜ ልምድ ያለው በመኾኑ ለሮናልድ ሬጋን ምክትል ፕሬዚዳንትነት
ታጭቶ ለስምንት ዓመት አገልግሏል።

ጆርጅ ሄ. ቡሽ የተወለደው ማሣቹሰት ግዛት በሚልቶን በተባለ
ቦታ ነው ። ያደገው ከሦስት ወንድሞቹና ከእኅቱ ጋራ በኮነቲኬት ግዛት
ግሪንዊች በሚባለው ቦታ ከሀብታም ቤተሰቦች ነው። ቡሽ የቅርጫት
ኳስ (የባስኬት ቦል) ካፕቴንና ቤዝቦል ተጫዋች ነበር። በ1942 ትምህ
ቱን እንዳጠናቀቀ የኹለተኛ ዓለም ጦርነት በመጀመሩ ወደ ኮሌጅ ሳ
ገባ በአውሮፕላን አብራሪነት በጦርነት ላይ ተሳትፏል ። በጊዜው ወ
ት ከኾኑት ጀት አብራሪዎች አንዱ ነበር ። ከጦርነቱ በኋላ በዬል ዩኒ
ቨርሲቲ ትምህርቱን ቀጠለ። በ1948 በከፍተኛ ማዕረግ በኢኮኖሚክስ
ድግሪ ተመረቀ። ከዚያ ዐዲሱን ሕይወቱን በቴክሳስ ግዛት ከባለቤቱና
ከወጣት ልጆቹ ጋራ የተፈጥሮ ነዳጅ ክርሰ ምድር ውስጥ በዘይት ማው
ጣት ሥራ ተሠማራ።

በ1962 አባቱ የኮነቲኬት የሴኔተር አባል በመኾን ተመረጠ ።
ጆርጅ ሄ ቡሽ እንደ አባቱ ፖለቲከኛ ለመኾን ፍላጎት አደረበት። ለተ
ወካዮች ምክር ቤት (ለሀውስ ኦፍ ሪፕሬዘንታቲቭ) በ1966 ተወዳድሮ የ
ክሳስ ግዛትን ወክሎ ተመረጠ።[202] የሪፐብሊኩኑ ሮናልድ ሬጋን የአሜሪ
ካን ፕሬዚዳንት ኾኖ ሲመረጥ ምክትል ፕሬዚዳንት ኾኖ እንዲሠራ
ሾመው ። በጣም ጠንካራ ሠራተኛና ታዋቂ የፕሬዚዳንቱን መመሪያ
(ፖሊሲ) የሚያስፈጽም ነበር።

[201] **Harry Smith.**, *p., 240*
[202] **George Sullivan.**, *p., 158*

በመጨረሻም በ1988 ለፕሬዚዳንትነት ሲመረጥ ሬጋን ጠንካራ ሠራተኛነቱን መስክሮለታል ። የፕሬዚዳንተነት ቦታውን ሲይዝ በምሥራቁ የአውሮፓ ክፍል የኮሚኒዝምን ሥርዓት ከ1961 ጀምሮ የምሥራቅንና የምዕራብ ጀርመንን ለኹለት የከፈለው የግንብ አጥር ፈርሶ የተቀላቀሉበት ጊዜ ነበር ።

ፕሬዚዳንት ቡሽ በ1990 ወደ ኢራቅ የባሕር ሰላጤ የአሜሪካንን ጦር በመላኩ የበለጠ ገናና አደረገው። ኢራቅ ኩዌትን በመውረሯ የተነሳ በ1991 ዓለምን ያስጨነቀ ኦፕሬሽን ዴዘርት እስቶርም የሚባለው ጦርነት ሊጀመር በዝግጅት ላይ የተደረሰበት እና የሶማልያ ዚያድ ባሬ መንግሥት የወደቀበት ጊዜ ነበር ። ነገር ግን በ1992 በተደረገው ምርጫ ላይ ሊመረጥ አልቻለም።

ፕሬዘዳንት ቡሽ የግሪክ ኦርቶዶክስ ኤኩሜኒካል ፓትርያርክ በርተሎሜዎስ መጋቢት 9ቀን 2002 ለሚስቱ ባርባራ ቡሽና ለእሱ የአትናጎራስ የሰብአዊ መብት ሽልማት ሸልመዋቸዋል።

## (፳) ፕሬዘዳንት ዊልያም ቢል ጄፈርሰን ክሊንተን (ባፕቲስት)

ቢል ክሊንተን 42ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ነው። ቢል ክሊንተን የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ የተነሳ ታላቅ ፖለቲከኛና ተወዳጅ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ነበር። ለፕሬዘዳንትነት ከ1993 እስከ 2001 ድረስ ኹለት ዙር ተመርጦ አገልግሏል።

ቢል ክሊንተን የተወለደው ነሐሴ 19 ቀን 1946 አርካንሳስ ግዛት ነው ። አባቱ በሕይወት ዘመኑ በመኪና መለዋወጫ ንግድ ይተዳደር ነበር ። ቢል ክሊንተን ከተወለደ ከሦስት ወር በኋላ አባቱ በመኪና አደጋ ሞተ። እናቱ ቨርጂንያ ካስዲ ትባላለች። ?ክሊንተን አባት ሲሞት የመኪና ነጋዴ (ዲለር) የኾነውን ሮጀር ክሊንተንን አገባች ። ቢል ክሊንተን ሰባት ዓመት ሲሞላው ቤተሰቡ አርካንሳስ ግዛት ውስጥ ሆት ስፕሪንግ ወደሚባለው ቦታ ተዛወሩ። በዚያም ከታናሽ ወንድሙ ሮጀር ጁኒየር ጋር የሕዝብ ትምህርት ቤት ገቡ። እናቱ ፖለቲከኛ እንዲኾን ኹልጊዜ ታበረታታው ነበር ። የእንጀራ አባቱ ሮጀር መጠጥ ጠጭ ስለኾነ እናቱን ይመታት ነበር። በመጨረሻ ግን ጋብቻው አልቀጠለም ተለያዩ፤ ወዲያው እሱን ፈትታ ሌላ ባል አገባች።

ቢል ክሊንተን በትምህርት ቤት በብዙ ቦታ በመሪነት አገልግሏል። በ1963 በበጋው ወራት ከትምህርት ቤቱ በመመረጥ የመንግሥት



አስተዳደር የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመገኘት ተወክሎ አርካንሳስ ግዛት በሊትል ሮክ ላይ ተካፍሏል። ዋሽንግተን በመኼድ ከፕሬዚዳንት ኬኔዲ ጋር ተገናኝቷል ። በ1968 ወደ ጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲ በመኼድ በዓለም ዓቀፍ ነጻ የትምህርት ዕድል (በኢንተርናሽናል ፌሎውሺፕ) በአርትድግሪ ተመረቋል።

ቢል ክሊንተን በወጣትነት ዘመኑ የቭዬትናምን ጦርነት ይቃወም ነበር። ትምህርቱን በመቀጠል የውጭ የትምህርት ዕድል አግኝቶ ለኹለት ዓመት በእንግሊዝ አገር በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ሙያ አጥንቷል። በድጋሚ በ1970 በዬል የሕግ ትምህርት ቤት ገብቶ የሕግ ትምህርት ሲያጠና በዚያው የዛሬዋን ባለቤቱን ሂላሪ ሮደሀም ክሊንተንን ከቺካጎ ከተማ ዳርቻ ዌስሊ ኮሌጅ የተመረቀችውን ጓደኛው አደረጋት።

በ1973 የሕግ ትምህርቱን አጠናቆ በአርካንሳስ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት አስተማሪ ሲኾን ወደፖለቲካው ዓለም በደምብ ገባበት፤ በዚህ ጊዜ 28 ዓመቱ ነበር ። ወዲያው ከሂላሪ ጋራ ጋብቻቸውን አደረጉ። ይህች ባለቤቱ ሂላሪ የሜተዲስት (ዌዝሊ) የክርስቲያን እምነት ተከታይ ነች ። አስተዳደጓ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፤ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ነበር። ከተጋቡ በኋላ ወዲያው የአርካንሳስ ሮቃቤ ሕግ ኾኖ ተመረጠ ። ከኹለት ዓመት በኋላ የአርካንሳስ ግዛት አገረ ገዢ አስተዳደር ኾኖ ተመረጠ ። በ1980 ሴት ልጃቸውን ቼልሲያ ክሊንተንን ወለዱ።[203]

በአርካንሳስ ለ5 ዓመት በመንግሥት አስተዳደር ካገለገለ በኋላ ለአገሪቷ ፕሬዚዳንት ለመኾን ውድድር አደረገ ። በዚህ ውድድር የቴነሲ የሴኔተር ተወካዩን አልበርት ጎር ጋር ኾነው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽን አሸነፉ። በጥቅምት 3 ቀን 1991 የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በመኾን ተመረጠ። ቢሮውን በወጣትነት ዕድሜው በጥቅምት 20 ቀን 1993 በ46 ዓመቱ ዋይት ሀውስ በመግባት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ኾነ ።

በድጋሚ በ1996 ለኹለተኛ ዙር ተወዳድሮ አሸነፈ ። በዚህ በኹለተኛው ዙር ላይ በዋይት ሀውስ ከምትሠራው ጸሐፊው ከሞኒካ ሊዊንስኪ ጋር ባደረገው ከጋብቻ ውጭ ግንኙነት የውርደት ቅሌት ስለደረሰበት በወንጀለኛነት በመከሰስ ተጠይቆ ውሸት ዋሸ ። እንደገና ደግሞ አምኖ ንሥሐ ገብቶ ያሳሳተውን ሕዝብን ይቅርታ ጠይቋል።

በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ባለቤቱ በጉዳዩ በመቆጣትና ወደ መጥፎ አቅጣጫ በመኼድ ፈንታ ቃል ኪዳኗን ጠብቃለች ። የቀድሞው የመ

[203] George Sullivan., *p., 166*

ንፈሳዊ አገልግሎቷ ለጋብቻዋ በጣም ረድቷታል ። ከጎኑ ቆማ እሱን በመምከርና በግንባር ቀደምትነት ይቅርታ አድራጊ ኾና የአሜሪካን ሕዝብ የእሷን ምሳሌነት ተከትሎ ይቅርታ እንዲያደርግለት የጠየቀች ጠንካራና የምትደነቅ ባለቤት መኾኗን አስመሰከረች። ምክር ለማግኘት ወደ ዩናይትድ ሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን ቄስ ዘንድ ዘወትር ይዛው ትኼድ ነበር ። የቀድሞ የባፕቲስት ክርስትና ጥምቀቱን ትቶ በዚህ በሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን ተጠመቀ ። በዚህ በችግሩ ጊዜ ከእጁ መጽሐፍ ቅዱስ አይለይም ነበር ። ትንቢተ ኢሳይያስ ዘወትር ያነብ ነበር።

በመጨረሻ ዓመቱ ምክትል ፕሬዚዳንቱ አልጎር የሱን ቦታ እን ዲይዝ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን አልተሳካም ። በዘመኑ በ1995 ጥቂሮችን ከሚጠሉት ክፍል የኾነ አሸባሪ (ቴረሪስት) የአሜሪካ ወታደር የነበረው ቲሞቲ ጄ. ማክቤዝ በኦክሎሆማ ግዛት ያለውን ሕንጻ በቦምብ በማፍ ረሱ 169 ሰው አልቀዋል፤ ይህ ሰው በኋላ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል።

በመጨረሻም ቢል ክሊንተን በ2004 በልብ ሕመም ተይዞ በቀዶ ጥገና እንዲሻለው ኾነ፤ ይህም ህመሙ የአሜሪካንን ሕዝብ አስደንግጦ ነበር። ፕሬዚዳንት ክሊንተን የተደነቀ ፖለቲከኛ እና በሕዝብ የተወደደ ነው። ከ2001 ጀምሮ በኒው ዮርክ ከተማ ሀርለም የኤድስ በሽታ ፣ የጤና ጥበቃ እና ድህነትን ለመቀነስ ባቋቋመው ድርጅት ዕርዳታ ሥራ ውን እያከናወነ ይገኛል።

## (፪) ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዎከር ቡሽ (ሜተዲስት ቦርን አጌን)

ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዎከር ቡሽ 43ኛው የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ሲኾን ለመጀመሪያ በ2001 ተመረጠ ከዚያም በድጋሚ በ2005 ተመርጦ ለ2ኛ ዙር በመምራት እስከ 2008 የመጨረሻ የፕሬዘዳንትነት ሥራውን እያ ጠናቀቀ ነው ። አባቱ ከፕሬዚዳን ክሊንተን በፊት የነበረ 41ኛ ፕሬዚዳ ንት ነበር።

ፕሬዚዳንት ቡሽ ሰኔ 6 ቀን 1946 በኒው ሄቨን ከነክቲከት ግዛት ተወለደ ። በልጅነቱ ያደገበት ቦታ በሚድላንድ እንዲሁም ቴክሳስ ግዛት ነው። የ3 ዓመት እኅቱ ሮቢን የደም ካንሰር (ሉኪምያ) ይዟት ስትሞት ቡሽ የሰባት ዓመት ልጅ ነበር። ሦስት ወንድሞች አንድ እኅት አለው። ስማቸው ጆን፣ ኒል፣ ማርቪንና እኅታቸው ዶረቲ ይባላሉ ።



ጆርጅ ቡሽ ከኹሉም ታላቅ ነው። አባቱ ከተማረበት ትምህርት ቤት ፊሊፕ አካዳሚ በአድቨር ማሣቹሴት ግዛት ተማረ ። ከዚያም በኋላ ወደ ዬል ዩኒቨርሲቲ በመግባትበ 1968 በባችለር ድግሪ ተመርቋል ። ከዚያም ኤፍ 102 ተዋጊ ጀት አብራሪ በመኾን በቴክሳስ አየር ኃይል ሠርቷል ። በመቀጠልም በ1975 ከሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በንግድ አስተዳ ደር (ቢዝነስ አድምንስትሬሽን) ተምሮ የማስተርስ ድግሪ አግኝቷል።

በ1977 ቀደም ብሎ አስተማሪ የነበረችና በኋላ የሚድላንድ ትምህርት ቤት የመጻሕፍት ቤት ሠራተኛ (ላይበረሪያን) የነበረች ሎራ ዌልቺ ቡሽን አግብቶ መንታ ሴቶች ልጆች ባርባራን እና ጄና በ1982 ወልደዋል።

ቡሽ ያባቱ አማካሪ ኾኖ የሠራ ነው። በ1988 በአባቱ ምርጫ ውድድር ጊዜ የተሳካ እንዲኾን ቅስቀሳ ያደርግ ነበር። ከዚያም በ1989 የቴክሳስ ሬንጀር የቤዝቦል ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ (ጀነራል ማኔጀር) ኾኖ ነበር። በመቀጠልም የቴክሳስ አስተዳደር አገረ ገዢ (ገቨርነር) በመኾኖ በከፍተኛ ድምፅ ኅዳር 8 ቀን 1994 ተመርጦ ዐራት ዓመት ሠርቷል። በድጋሚ እንዲያገለግል ኅዳር 3 ቀን 1998 በከፍተኛ ቁጥር ተመርጧል ። በዚህ ምርጫው ጊዜ ያደረገው ንግግር እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

> እምነቴ የሚነግረኝ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒቴና አዳኜ መኾኑን እቀበላለሁ ። ይህንም ግልጽ ማድረግ እወዳለሁ ። ማን ወደ ሰማይ መውጣት እንዳለበት የአገር ገዢ ሥራ ጉዳይ አይደለም ። ወደ ሰማይ የሚወጣውን የሚወስነው እግዚአብሔር መኾኑን አምናለሁ ፤ ጆርጅ ቡሽ ግን አይደለም።

ጆርጅ ቡሽ ከቤተሰቦቹ የወረደውን እምነት ተቀብሎ የኤጲስቆጶል አባል ኾኖ ሲኖር ቆይቶ ከሜቴዲስት የክርስትና እምነት ሥር የተወለ ደውን ከረር ያለውን የቦርን አጌን እምነት በ40 ዓመቱ ተቀብሎ ተጠ ምቋል። በዚህ ሃይማኖቱ በመካከለኛው የአሜሪካ ክፍል በጣም ይከብ ሩታል ።

ጆርጅ ቡሽ ጁኒየር አልጎርን በአጠራጣሪ ኹኔታ በምርጫ ውድ ድር አሸንፎ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት በመኾን ቃለ መሐላ የፈጸመው ጥር 20 ቀን 2001 ነው።[204] ዐራት ዓመት ከመራ በኋላ እንደገና ተወዳ

[204] George Sullivan., *p., 169*

ድሮ የሴናተር አባል የኾነውን ጆን ኬሪን ለኹለተኛ ዙር አሸንፎ የአሜሪካንን ሕዝብ በመሪነት ባድጋሚ ዐራት ዓመት ለማገልገል ቃለ መሐላ በጥር 20 ቀን 2005 ፈጸመ።

የመስከረም ወር 2002 (ሴብቴምበር 11) አደጋ የአሜሪካ ሕዝብ ሕይወትን ለወጠ። ጊዜው በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር የዐዲስ ዓመት መግቢያ ቅዱስ ዮሐንስ ዕለት ዐራት የንግድ አውሮፕላኖች ተጠለፉ። ኹለቱ አውሮፕላኖች በኒው ዮርክ ያለውን የዓለም የንግድ ማዕከል የኾኑትን ኹለት የሚመሳሰሉ ሕንጻዎችን መቱ ። ሦስተኛው አውሮፕላን በዋሽንግተን የሚገኘውን የጦር ጽሕፈት ቤቱን (ፔንታጎንን) ጎኑ ላይ በመጋጨት መታ። ዐራተኛው በፔንሲላቫንያ ግዛት ፒተርስበርግ አጠገብ ወደቀ ። ኹሉም አውሮፕላኖች ውስጥ ያሉ ሰዎች በሙሉ አለቁ ። በዚህ አደጋ ጥቂት ኢትዮጵያውያንና ለአሜሪካ በህክምና ሥራ ላይ ተሠማርቶ ይሠራ የነበረው ዶክተር ዮሐንስ በትሩ በዚህ ሕይወታቸው አልፏል ። የኢትዮጵያውያን ቁጥር ጥቂት ሊኾን የቻለው የቅዱስ ዮሐንስ በዓል ስለነበረ በብዛት ዐውደ ዓመትን በቤተ ክርስቲያንና በቤቱ ስላሳለፉ ነው ። ይህ ባይኾን ኖሮ ቁጥሩ ከፍተኛ ሊኾን ይችል ነበር።

ባጠቃላይ በዚህ አሸባሪነትና የአጥፍቶ መጥፋት (የቴረሪስት) አደጋ ቁጥራቸው ከ3000 ሰዎች በላይ የኾኑ ሞተዋል ። እነዚህ አሸባሪዎች ወደፊት ፍጥረትን የሚያጠፉ ፤ ሕዝባዊ ጥፋትን የሚያደርስ (ማስ ዲስትራክሽን) የኒኩሊየር ቦምብ እንዲሁም ባዮሎጂካል ወይም የኬሚካል ጦር ይጠቀማሉ በሚል ጉዳዩ ዓለምን አሳሰበ።[205]

ፕሬዚዳንት ቡሽም በአፍጋኒስታን ባሉት በታላባን አሸባሪ መንግሥት ላይ ጦርነት አወጀ። ቤን ላደንን ፍለጋ አፍጋኒስታን ተደበደበች ቤን ላደን ግን አልተገኘም ። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሽብርተኞች ማሰስ ተጀመረ። ብዙዎች በጦርነት ሲሞቱ ሌሎቹ ደግሞ ተማርከው የተጠረጠሩት ጭምር በሞንታና ቤይ ታሠሩ።

[205] Jacob E. Safra & Ian Yeshua *The new Encyclopedia Britannica., No, 11., p. 650*





የቦርን አጌን እምነት ተከታይ ፕሬዘዳንት ቡሽና ካቢኔቱ ስብሰባ ከመጀመራቸው በፊት ኹል ጊዜ በጸሎት ይከፍታሉ። መጋቢት 19 ቀን 2003 ኢራቅን ለመደብደብ ሲዘጋጁ ስብሰባው በጸሎት ተከፍቶ ነበር ።

ፕሬዘዳንት ቡሽ አባቱ የጀመረውን በድጋሚ እሱም ኢራቅን ለመውረር ተነሳ። በዚህ ጊዜ ኹሉ የካቢኔቶቹ አባላት ኮሊን ፓውል፣ ዶናልድ ራምስፊልድ፣ ዲክ ቼኒ ሌሎችም ስለ ጦርነቱ ስብሰባ ከመጀመራቸው በፊት እንደተለመደው ዓይናቸውን ጨፍነው ጸሎት አድርገው ነበር።

ፕሬዚዳንት ቡሽ ሚያዚያ 13 ቀን 2003 በዋሽንግተን ባደረገው ንግግር እንዲህ ብሎ ነበር።

አንዱ ታላቅ ነገር፤ በዚህ አገር ብዙ ሰዎች ጸሎት ይጸልያሉ። እኛም በነጻነት እናምናለን ፤ ነጻነትም በኹሉ ቦታ እንዲኾን እናምናለን፤ ነጻነትም ከኃያሉ ከእግዚአብሔር ለኹሉም ሰው የተሰጠ መኾኑንን እናምናለን፤ በማለት ንግግር አድርጓል።

ብዙዎች ሰዎች የፕሬዚዳንት ቡሽ ጸሎቱና በእግዚአብሔር አምናለሁ ማለቱ እውነተኛ ሳይኾን የግብዝነት ነው ይሉታል ። ይህንን ሊባል የቻለበት በኢራቅ ጦርነት በመካኼዱ የተነሳ ነው ፤ በዚህ ጦርነት ንጹሐን የኾኑ ዜጎች በጥይትና በቦምብ ምንም በማያቁት ነገር ተጨፍጭፈዋል። ፕሬዚዳንት ቡሽ ግን በኢራቅ ዲሞክራሲን ለማስፈን፣ ጭቆናን ለማስወገድ የተነሳ መኾኑን ብዙ ጊዜ ገልጿል።

ኢራቅ የቀድሞዋ ባቢሎን እንዲሁም ሜሶፖታሚያ ተብላ ስት
ጠራ የነበረች አገርነች። ከክርስቶስ ልደት በፊት 3500 ዓ. ዓ. ጀምሮ
በዓለም የቀደመ ሥልጣኔ የነበራት አገር ነች ። ኤፍራጥስ እና ጤግ
ሮስ የሚባሉት ወንዞች አገሪቷን መሐል ለመሐል አቋርጠው የሚፈ
ሱባት ፣ የታሪክ ቦታ ባቢሎን በአኹኑ በሥልጣኔ ዘመን ኢራቅ ትባላ
ለች፤ የጥንት ዘመን መሪዎቿ የሰናአር ንጉሥ አምራፌል (ዘፍ. 14፥1)
ኃያሉ ናቡከደነጾር እስራኤላውያንን እነዳንኤልን የማረከባት አገር ናት
(ዳን.4፥30)። የተማረኩት እስራኤላውያንም እንዲህ ይሉ ነበር።

> በባቢሎን ወንዞች አጠገብ በዚያ ተቀመጥን ፤
> ጽዮንን (ኢየሩሳሌምን) ባሰብናት ጊዜ አለቀስን።
> በአኻያ ዛፎችዋ ላይ መሰንቆቻችንን ሰቀልን ።
> የማረኩን በዚያ የዝማሬ ቃልን ፈለጉብን ፥
> የወሰዱንም የጽዮንን ዝማሬ ዘምሩልን አሉን።
> (መዝ. 136 (137) ፥1)

ይህ የመዝሙረ ዳዊት ክፍል አስደናቂ እውነታነት አለው። ኢራቅ የን
ስጥሮሳውያን ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች እንዲሁም ሺያት፣ ሱኒና ኩርድ
የሚባሉ በአመለካከት ተለያይተው የሚኖሩ የእስልምና ሃይማኖት
ቡድን ያለባት አገር ነች።

የኢራቅ መሪ ሳዳም ሑሴን እንደ ናቡከደነጾር ገናና ፈላጭ
ቆራጭ መኾንን ፈለገ። ይህ የጥንታዊ የባቢሎን ነገሥታት ታሪክ እና
ኃያልነት በቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈውን ብዙ ሥራቸውን በብሔራዊ
ሙዝየሙ አሰባሰቧል። እሱም እነሱን መኾን ፈለገ። ለኃያላን መንግ
ሥታት ለአሜሪካና ለብሪታንያ መታዘዝን አልፈለገም። በ1991 ኩዌትን
ወረረ። አሜሪካም "ዴዘርት አስቶርም" በተባለ ጦር ኃይል ጥር 16 ቀን
1991 ከኩዌት ከአስወጡት ከ12 ዓመት በኋላ የኒኩሊር ቦምብ ስላ
ለው እንዲያስረክብ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ዩናይትድ ኔሽን)
ተጠየቀ። መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የተመደቡ ባለሙያዎች (ኢክ
ስፐርቶች) እንዲመረምሩ ተላኩ ። ነገር ግን ሳይደረሰበት መገኘት አለ
መገኘቱ ሳይታወቅ ጦርነቱ ለኹለተኛ ጊዜ በ2002 በፕሬዘዳንት ቡሽ
ታወጀበት ። ዓለምን የሚያጠፋው መሣሪያ (ማስ ዲስትራክሽኦ) አልተ
ገኘም ። ነገር ግን በጦርነቱ ብዙ ሰው አለቀ ። 55 ባለሥልጣኖች ለፍ
ርድ ቀረቡ ። የኢራቁ መሪ ሳዳም ሑሴን ከተደበቀበት ቦታ ታኅሣሥ
16 ቀን 2003 ላይ ተገኘ።[206]

[206] TIME *The Year In Review., p., 61*



ፕሬዘዳንት ቡሽ ኢራቅንና አፍጋኒስታንን ለመውረር ከእግዚአብ
ሔር ትእዛዝ ተሰጥቶኝ ነው በማለት ሰኔ 2003 ለፍልስጥኤም ጠቅላይ
ሚኒስቴር ለመሐመድ አባስና ለፍልስጥኤም መሪዎች የተነገረውን፤ የፍ
ልስጥኤም የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥቅምት 6 ቀን 2005
ለቢቢሲ ጋዜጠኞች ገለጸ።

> እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ አዘዘኝ፦ ጆርጅ ! ሂድ እና ከነዛ
> ከአፍጋኒስታን ሽብር ፈጣሪዎች ጋራ ታገል አለኝ፤ እኔም አደረ
> ግሁት። እንደገናም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ ጆርጅ! ሂድ
> በኢራቅ የተመሠረተውን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አጥፋ አለኝ፤
> እኔም አደረግሁት ። አኹን ደግሞ እንደገና መካከለኛው
> ምሥራቅን ሰላም እንዳደርግ እግዚአብሔር አነጋገረኝ። ለፍል
> ስጥኤም ግዛታቸውን ስጣቸው ፤ ለእስራኤል ጥበቃ እንዲደረግ
> ላቸው አድርግ ብሎ አዘዘኝ ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ስም
> አደርገዋለሁ፤ በማለት ፕሬዘዳንት ቡሽ አስረዳ።

በዚህ ንግግሩ ወዲያው የብሪታንያ ጋዜጦች "ቅዱስ ቡሽ" በማለት የቅ
ድስና ምልክት የኾነውን ክብ ብርሃን የተሞላበት የመንፈስ ቅዱስ ምል
ክት (ሄሎ) በራሱ ላይ በማድረግ መሳለቂያ አደረጉት።

ጦርነቱ መጋቢት 19 ቀን 2003 ተጀመረ። ብዙ ሰው አለቀ ፤

በመጋቢት 19 ቀን 2007 በአውስትራላውያን በቀረበው ጥናት አንድ
ሚልዮን እንደ ደረሰ በጋዜጣ ወጣ። ኹለት ሚሊዮን ከመኖሪያ ቦታ
ቸው ተፈናቀሉ ። ኹለት ሚሊዮን የሚደርሱት ደግሞ ወደ ጎረቤት
አገሮች እና ወደ ሶርያ ተሰደዱ። እየዋለ እያደር የአሜሪካንን ሕዝብ
ብቻ ሳይ'ኾን በኮንግረስ ጉዳዩ አነጋጋሪ ኾነ።

ኅዳር 4 ቀን 2006 የቀድሞ የኢራቁ ፕሬዘዳንት ሳዳም ሑሴን
በስቅላት እንዲቀጣ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ። ጦርነቱ ግን በብዙዎች
አሜሪካውያንና የዓለም ሕዝቦች እንዲሁም የክርስትናም ይኹን የእስ
ልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ድጋፍ አላገኘም።[207]

ይህን ጦርነት አሜሪካና ብሪታንያ ተባብረው ሲወሩ ብዙዎቹ
የአውሮፓ አገሮች ሊተባበሯቸው አልፈለጉም። ጦርነቱን ሲጀምሩት
በቶሎ አጠናቀው የሚወጡ መስሏቸው ነበር ። የኢራቃውያን ሕዝ
ቦች ተፈጥሮና ባህል ግን ከጠላት ጋር አብሬ ተናንቄ እጥፋቼ ልጥፋ
የሚል ስለኾነ ቦንብ እየታጠቁ ብዙዎችን ፈጁ።

[207] Guardian Co. UK Friday October 7, 2005

አሜሪካ እና ብሪታንያ ይህን ባህል ቀደም ብለው ባለመረዳታቸው ይመስላል ጦርነቱ በቶሎ ሊያቆም እና ሊረጋጋ አልቻለም ። የአሜሪካ ወታደሮች ሲሞቱ ይነገራል ጀግና ተብለውም ይጠራሉ። የኢራቃውያን ግን ሰላማዊ ሰዎች እንኳን ሲሞቱ አይጠሩም ። በእግዚአብሔርም ዘንድ በአሜሪካውያን አባቶች የነጻነት አዋጅ የሰው ልጅ ኹሉ እኩል ነው ያሉት አልሠራም ።

የአሜሪካ ወታደሮች ከዓራት ሺህ በላይ ብጦርነቱ እንዳለቁ ሲታወቅ ይህ ጦርነት ከቬዬትናም ቀጥሎ ኹለተኛው የአልቂት ጦርነት እንደኾነ ይነገራል።

ጦርነቱ እንዲፈጸም ብዙዎች አሜሪካውያን ፣ የኰንግረስ እና የሴኔትር አባላት እንዲሁም የብሪታንያ ሕዝብ እና የፓርላማ አባላት ቢያስቡም ፤ ኢራቅን ሳያረጋጉ ቢወጡ ሽንፈት ስለመሰላቸውና የከፋ የእርስ በእርስ ጦርነት በኢራቅ ላይ ይመጣል ብለው ስለሰጉ የጦርነቱ ማብቂያ ጊዜ ሊራዘም ቻለ ። የዓለም ሕዝብ ሳይቀር የማብቂያውን ጊዜ በናፍቆት እንዲጠብቀው አድርጎታል።

## (፲) ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ (ከራይስት ቸርች)

ከሙሴ ጋር እንደ ኾንኩ እንዲሁ ካንተ ጋር
እኾናለሁ ፤ አልተውህም አልጥልህም። (ኢያ. 1፥5)

ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ ኹለተኛውን የፕሬዚዳንትነት ያገልግሎት ዘመኑን ማጠናቀቂያ ዋዜማ ላይ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት የምርጫ ውድድር ተካኼደ ። ይህኛው የምርጫ ውድድር በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ዐዲስ ነገር ነበር ። ከዲሞክራት ፓርቲ ሄላሪ ክሊንተን እና ባራክ ኦባማ በዚያው በፓርቲያቸው ውስጥ ለፕሬዘዳንት እጩነት ለመቅረብ ያደረጉት ውድድር እልህ አስጨራሽ ነበር። በመጨረሻ ግን ባራክ ኦባማ ድል አደረገ ።

ባራክ ኦባማ በመቀጠል ከተቃራኒው ሪፓብሊካን ፓርቲ እጩ ከጆን መኬን ጋር ለምርጫ ውድድር ቀርቦ የሪፓብሊካኑን ጆን መኬንን በከፍተኛ ቁጥር በልጦ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ኾኖ ተመረጠ ። የህም ዐዲስ ነገር ለዘመናት የኖረውን የአሜሪካንን ሕይወት ለወጠ ፤ የነጭ የበላይነት ተገፈፈ ፤ ከ 45 ዓመት ቢፊት የጥቁት መብት ተከራካሪው ዶክተር ኪንግ የተናገረው ሕልም እውን ኾኖ ታየ ።



ይህ የፕሬዜዳንት ምርጫ አሜሪካንን ብቻ ሳይኾን የዓለምን ሕዝብ አነጋገረ ።

ባራክ ኦባማ በአባቱ አፍሪካዊ የኬንያ ተወላጅ ነው። አባቱ ኦባማ ሑሴን ይባላል ። እናቱ ደግሞ የካንሳስ ግዛት ተወላጅ የኾነች አን ዳንሀም ትባላለች።

በ1959 የጥቁር መብት እንዲከበር ትግል በሚደረግበት ዘመን የ20 ዓመት ወጣት አፍሪካዊ ኦባማ ሑሴን እስኮላር ሽፕ አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሀዋዪ ደሴት ሆኖሉሉ በምትባለው ቦታ ደረሰ። በጣም ጥቂት ጥቁሮች በሚማሩበት ፣ ዘረኛነት በበዛበት አንድ የኬንያ ተወላጅ አፍሪካዊ ኢኮኖሚክስ ለማጥናት ትምህርት ጀመረ ። ወዲያውም የባራክን እናት ወጣቷን አሜሪካዊት አንን ተዋወቀ ። ፍቅር ወደ ጋብቻ እንዲያመሩ አደረጋቸው። ጥቁር ከነጭ ጋር ሊጋባ ቀርቶ አብሮ የማይበላበት ጊዜ ፍቅር አሸንፎ ጋብቻው ቀጠለ ። የአሜሪካዊቷ አን ወላጆች ጋብቻውን አልተቃወሙም ። በ1961 ነሐሴ 4 ቀን ባራክ ተወለደ ። የባራክ አባት ኦባማ ድግሪውን ከያዘ በኋላ ሥራ አግኝቶ ገንዘብ በማፍራት ቤተሰቡን ለመርዳት ባለመቻሉ ወደ ቦትሰን ኼደ ። በዚያ ትምህርቱን ቀጥሎ የዶክትሬት ድግሪውን ይዞ ወደ ኬንያ ተመለሰ ።

የባራክ እናት አን ለብቻዋ ኑሮን መግፋት ስላልቻለች ሌላ ወጣት ተማሪ አገባች ። ይህም ሰው የኢንዶኔዥያ ተወላጅ ነበር ። ባራክ የ6 ዓመት ልጅ በኾነው ጊዜ ወደ ኢንዶኔዥያ እንጀራ አባቱንና እናቱን ተከትሎ ተጓዘ ። አን ከኤንዶኔዢያው ባልዋ ሌላ ቤት ልጅ ወለደች ። ይህችም የባራክ ታናሽ እኅት ማያ ትባላለች።

በ1971 አን ከኢንዶኔዥያ ልጇን ባራክን ወደ አሜሪካ ሀዋዪ ወደ ወላጆቿ ላከችው ። እሱም ከነጭ አያቶቹ ጋር መኖር ጀመረ ። አያቶቹም ጥሩ የታወቀ ትምህርት ቤት አስገቡት ። በትምህርቱም በጣም ጎበዝ ነበር። በ1979 ቤተሰቡን ተሰናብቶ ወደ ሎሳንጀለስ ኮለጅ ገባ። በትምህርት ቤቱም የቅርጫት ኳስ ቡድን ውስጥ ገብቶ ይጫወት ነበር ። ከሎሳንጀለም ኰለጅ ቢኤ ድግሪውን በ1983 ከኮሎንቢያ ዩንበርሲቲ ተቀበለ።

ባራክ ከኰሊጅ ሲወጣ ዘረኝነትን ለመታገል ቆርጦ ተነሳ ። ከዚያም በመቀጠል ወደ ኒው ዮርክ ከተማ በሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የአሜሪካንን ሕገ መንግሥት ለማጥናት አሰበ ። በዚህ ወቅት በኒው ዮርክ ዐዲሱን ትምህርት ለማመልከት በዝግጅት ላይ እያለ ኬኒያዊው አባቱ ኦባማ በመኪና አደጋ መሞቱን ስልክ ተደውሎ ተነገረው።

በ1988 ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አባቱ አገር ኬንያ ኼዶ የአባቱን መቃብር እና ቤተሰቡን፣ አያቱን፣ ዘመዶቹን አገኘ ። ከአፍሪካም በመመለስ በጣም ውድድር ባለበት ሐርቫርድ ዩንቨርሲቲ ገባ። በዚያም ጎበዝ ተማሪ ኾነ ። በመቀጠል በኅብረተ ሰቡ ውስጥ በኑሮ በጣም የተጐዱትን ድሆችን ለማሻሻል፣ ለመርዳት፣ በቤተ ክርስቲያኑ ስር ኾኖ ማሰባሰብ ጀመረ ።

በበጋው ወራት በዚሁ ያገልግሎት ሥራው ላይ ተሰማርቶ ወደ ቺካጎ ከተማ ኼደ። በዚያም የጥብቅና ትምህርት የተማረችውን ሚሸል የምትባለውን ጥቁር አሜሪካዊት ተዋወቀ ።

በሐርቫርድ ዩንቨርስቲ በጣም ጎበዝ ተማሪ በመኾኑ ዕውቅናን አገኘ ። በ1991 የመጀመሪያው ጥቁር አሜሪካዊ የሐርቫርድ ዩንቨርሲቲ የሕግ መጽሔት ክፍል ዋና አዘጋጅ ፕሬዘዳንት ኾኖ ተመረጠ። ታላላቅ የኒዮርክ ጋዜጣዎች የመጀመሪያው ጥቁር አሜሪካዊ የሕግ መጽሔት ዋና አዘጋጅ ፕሬዚዳንት ኾኖ ተመረጠ ብለው ባድናቆት በየገጾቻቸው አወጡት። ባራክ ኦባማ በዚሁ ዓመት የሕግ ድግሪውን አገኘ። ይህ የሕግ መጽሔት የዋና አዘጋጅነት ሥራው ለወደፊት የፖለቲካ ሕይወቱ ረድቶታል ።

የአባቶቼ ሕልም የሚል የመጀመሪያውን መጽሐፉን ጻፈ ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በሕዝብ ዓይን ገባ ። ወዲያው ወደ ቺካጎ በመኼድ የሰብአዊ መበት ትክራካሪ ጠበቃ ኾነ። በዚያው አያይዞ የአሜሪካንን ሕግ ያስተምር ጀመር ። ይህ ሥራውም ለኢሊኖይስ ሴነተር ለመኾን ውድድር ውስጥ ገባ። በከፍተኛ ውድድር ለኢሊኖይስ ሲናተርንት ተመርጦ ለ8 ዓመት አገለገልግሎት ሰጠ።

ከዚያም 2004 ለአሜሪካ ሴነተር ለመኾን ተወዳድሮ በማሸነፍ ወደ ዋሸንግተን ገባ ። ጋዜጦች ታላቅ የፖለቲካ ሰው መፈጠሩን በየአቅጣጫው መጻፍ ጀመሩ ። ሦስትተኛ መጽሐፎች ጻፈ ።

በፖለቲካ ንግግሩ አሳማኝነት ፣ ተወዳጅ ኾነ ። የአሜሪካንን ሕግ ጠንቅቆ የሚያውቅም በመኾኑ ንግግሩ የተመዘነ፣ ጥበብን የተሞላ ተስፋ ሰጭ ነው። በተስፋ ሰጭ ንግግሩ ዓለም ወደደው።

ለአሜሪካ ፕሬዘዳንትነት ለእጩነት ቀረበ። በንግግሩ፣ በፖለቲካ አቀራረቡ ከዚህ በፊት በፖለቲካ ዓለም ተሳትፈው የማያቁት ኹሉ በውዴታ ተነሳስተው ድጋፋቸውን ገለጡ ። አንድ ሕዝብ ፣ አንድ ቤተሰብ ...። የሚለውን የአሜሪካን የባህል ንግግር ፤ ኹሉም የሰው ዘር እኩል ነው የሚለውን የነቶማስ ጀፈርሰንን የነጻነት አዋጅ ሲናገር የአ



ሜሪካ ሕዝብ ከፍተኛ አድናቆት እና ድጋፍ አደረገለት ። በየቤተ ክርስቲያኑም ሲኼድ በመጽሐፍ ቅዱስም እያጣቀሰ አኹን የኢያሱ ጊዜ ነው፤ ኢያሱ ከሙሴ ተረክቦ ቃል ኪዳኗ ቦታ ለማድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ተነስቷል። ስለዚህም ለኢያሱ መሪነትን የሰጠ እግዚአብሔር ለእኛም እንዲሰጠን ጸልዩ ይል ነበር። ይህ የንግግሩ ምስጢር ከኪንግ የመጨረሻ ንግግር ጋር በማያያዝ ተስፋ ወደተደረገባት አገር ገባን ማለቱ ነው።

ባራክ ኦባማ የአሜሪካንን ሕዝብ የሚወክል ነው። አሜሪካዊ ነው፣ አፍሪካዊ፣ ኢንዶኔዢያዊ ፣ በአሜሪካ ግዛቶች የሀዋዪ ደሴት ተወላጅ ነው፤ የኒው ዮርክ ተማሪ ፤ የቺካጎ ነዋሪ የኢልኖይስ ሴናተር ነው ። ይህን ኹሉ በማየቱ የተሟላ ችሎታ አለው።

ባባቱ ጥቁር፣ በእናቱ ነጭ ፣ በእንጀራ አባቱ ሩቅ ምሥራቅ፣ በባለቤቱ በባርነት ይሰቃዩ ከነበሩት ቤተሰብ የተወለደች ኹሉንም የሚወክል ነው ። በንግግሩ ወገናዊነት ስሜት የሌለበት ፣ በእኩልነት የሚያምን ፣ ከጦርነት ሰላምን የሚሻ ሰው ነው።

ሰኔ 24 ቀን 2008 አፍጋኒስታን፣ ኢራቅ፣ እስራኤልን፣ ፓኪስታንን፣ ዮርዳኖስን (ጆርዳን) በክብር እንግድነት ጎበኘ። በየኼደበት ኹሉ የከበረ አቀባበል ተደርጎለታል። በተለይም በጀርመን ከፍተኛ አቀባበል ተደርጎለት ከኹለት መቶ ሺ ሕዝብ በላይ ባለበት ቦታ የተዋጣለት ንግግር አድርጓል ። ንግግሩ የድንፋታ ሳይኾን የተስፋ፣ የሰላም ንግግር ነው።

## ባራክ ኦባማ እና ኢትዮጵያውያን

ባራክ ኦባማ ኢትዮጵያ ውስጥ በ2005 ሐምሌ ወር በድሬደዋ ከተማ በደረሰው የጎርፍ መጥለቅለቅ ጊዜ በቦታው ተገኝቶ ነበር ።

ባራክ ማለት በግእዝ ቋንቋ ቡሩክ ተብሎ ይተረጐማል ይህ ሰው በተስፋ ሰጭነቱ እውነትም ቡሩክ ነህ ያሰኘዋል ። ስምና ግብሩ አብሮ ኼዷል ። በንግግራቸው ከተደነቁት የአሜሪካውያን ተናጋሪዎች ከፕሬዚዳንት ኬኔዲ፣ ከፕሬዚዳንት ክሊንተን የማይተናነስ ነው። አትችሉም እንባል ነበር እንችላለን (Yes We Can) ፤ አሜሪካንን እንለውጥ ፤ እያለ በመናገሩ ኢትዮጵያውያንም (ኢትዮ-አሜሪካን) በተስፋ ለመምረጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አደረጉ።

በፔንስላቫንያ ኢትዮጵያውያን በፖስተር ላይ ፎቶውን በማድረግ ይቻላል የሚል መፈክር በዐማርኛ ተጽፎ ለምርጫ ቅስቀሳ አውጥ

ተውለት ነበር። ባራክ አባማ ለአሜሪካ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ደብዳቤ ጻፈ። ደብዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር።

ይድረስ በአሜሪካ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን።

ይህንን መልእክት ስላነበባችሁልኝና ለአሜሪካ ፕሬዘዳንትነት እጩነቴን በጥሞና ስላሰባችሁበት ልባዊ የኾነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በፖለቲካ ምርጫ መሳተፍ ከዜጎች ዋንኛ መብቶችና ግዴታዎች አንዱ ነው። ስለዚህም ተመዝግባችሁ በምርጫው እንደምትሳተፉ እተማመና ለሁ ።

እኔ ፕሬዚዳንት ለመኾን ስወዳደር ዓላማዬ የሕዝብን ኑሮ ለማ ሻሻል ከተሞችን እና ሠፈሮቻችንን ለመገንባት ፤ የዜጎችን መሠረታዊ መብት ለማስከበር እና በመላው ዓለም የአሜሪካንን መሪነት እንደገና ለማደስ ነው። አሜሪካ የገዛ ዜጎቹዋ ለሌሎች አርአያ ሊኾን በሚችል መልኩ መንከባከቧና ሀገራችን የቆመችላቸውን ከፍተኛ ዓላማዎች የሚያንጸባርቅ የውጭ ጉዳይ መርህ መራመዷ ምንኛ አስፈላጊ እንደ ኾነ እንደምትረዱ አውቃለሁ ።

በአሜሪካ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ለሀገራችን እና ለባህላችን ሠፊ አስተዋጽኦ አድርጋችኋል። ስለዚህም ከናንተ የሚገኘው ከፍተኛ ድጋፍ ያኮራኛል። ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ ሕዝብ በዚህ ምርጫ እንዲሳተፍ እየሠራን ስለኾነ ተመዝግባችሁ በመምረጥ የዚህ ጥረታችን ተሳታፊ እንደምትኾኑ ተስፋ አደርጋለ ።

የአሜሪካንን ዓለም አቀፍ መሪነት ለማደስና በ2006 አፍሪካ ሄጄ ሳለ እንዳገኘኋቸው ሰዎች ያሉትን ለመርዳት ቆርጬ ተነስቻለሁ። ይኽንንም የማደርገው ትክክል ስለኾነ ብቻ ሳይኾን ለአሜሪካም ስለሚ ጠቅም ነው። ነገር ግን ይህንን ለማድረግ በመጀመሪያ የናንተን ርዳታ እና ተሳትፎ እሻለሁ። ለውጥ እንደሚጠይቅ አሜሪካዊ ለመብታችሁ ቆማችሁ ራሳችኹን እንድታስቀጥሩ እፈልጋለሁ ።

ስለምርጫ ጥያቄ ካላችሁ ወይም ደግሞ በዚህ የምርጫ ዘመቻ ችን መሳተፍ ከፈለጋችሁ። በአካባቢያችን ያሉትን የምርጫ አስተባባሪ ዎች አነጋግሯቸው ። ይህንንም ደብዳቤ ስላነበባችሁና በምርጫውም ስለተሳተፋችሁ በድጋሚ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ባንድነት የምንሻውን ለውጥ እናመጣለን ።

ከክብሮት ጋራ
ባራክ አባማ



የቅስቀሳ ምላሹ በከፊል እንዲህ የሚል ነበር፦

ዓለምን ያቀፈ ወገኔ አባማ፤
ፍጹም ልዩ የኾነ ለኹሉ የሚስማማ፤
እናት ካሜሪካ አባት ከኬንያ፤
....
ጭንቅላቱ ንጹሕ ጥላቻ የለው፤
ተንኮል ሲታሰብበት ፍጹም አይከፋው፤
ኹሉም ይቻላል መፈክሩ ነው።
ወደፊት እንጂ ወደኋላ የማይለው፤
ዘሩ ከኬንያ የአፍሪካ አንበሳ፤
ጥቁርን አስከባሪ ለኹሉ የሚያገባ፤
....።
እግዚአብሔር ይባርክህ አይዞህ ወንድማችን
ዕድልኽን ያቅናው የእኛ መመኪያችን ...። [208]

በኢትዮጵያውያንም ዘንድ ቅስቀሳው፣ ትብብሩ በየግዛቱ ከፍተኛ ነበር። ከአሜሪካ ውጭ ያሉት በርካታ አህጉራት እንዲሁም ዜጎች ኹሉ በፕሬዚዳንታዊው ፋክክር ወቅት ድጋፍ ይሰጡት ነበር ።

የአሜሪካም ሕዝብ ባራክን ለመምረጥ ወደኋላ አላለም። ለም ርጫ 106 ዓመት የሞላቸው በባርነት ሥርዓቱ ይደርስ የነበረውን ግፍ ጠንቅቀው የሚያውቁ አማንዳ ጆናስ በምርጫ ቦታ በመኼድ መርጠ ዋል።

ከዚህ ኹሉ ውጣ ውረድ በኋላ ማክሰኞ ለረቡዕ አጥቢያ ጥቅ ምት 28 ቀን 2001 ዓ. ም. (ኅዳር 5 ቀን 2008 ) የአሜሪካ ሕዝብ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ጥቁር አሜሪካዊ ለፕሬዚዳንትነት መረጠ። ሴናተር ባራክ አባማ 44ኛ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ኾኖ ተመረጠ። ይህ ምርጫም ታሪ ካዊ ምርጫ ኾነ ። ዋይት ሀውስ የመጀመሪያውን ጥቁር ቀዳማዊት እመቤት ሚሸል አባማን አገኘ ። ልጆቹ ማሊያ እና ሳይሻ በልጅነታ ቸው ወደ ዋይት ሀውስ ለመግባት መንገድ ጀመሩ።

ከ45 ዓመት በኋላ የኪንግ ሕልም እውን ኾነ ። ባራክ አባማ በመኖሪያው ቺካጎ አኩስ ሌሊት ላይ ንግግር አደረገ። አሜሪካን እንለ ውጥ የሚለው የመወዳደሪያ መፈክር በልበ ሙሉነት ይናገረው ነበር።

[208] መልካሙ ካሳሁን ከገጠመው ግጥም የተወሰደ ጥቅ. 29 ቀን 2008

የአሜሪካን ሕዝብ እንዲሁ የዓለም ሕዝብ በንግግሩ ተማረከ። ተስፋ ሰጭ፣ ታሪክ የሚጠቅስ፣ በተለይም የአሜሪካንን ጥቁር ታሪክ በደንብ የሚያውቅ ፤ በዕውቀት የተሞላ ፤ ፍርሀቻ የማይታይበት፣ በቀላሉ የማይሸበር ሰው ነው።

በዚህ ዕለት በወጣትነቱ ከኪንግ ጋር አብሮ ለጥቁሮች መብት ይከራከር የነበረው ጄሲ ጃክሰን በኦባማ ምርጫ እና ንግግር በመደሰቱ ይህን ታላቅ ለውጥ በማየቱ አልቅሷል። ብዙዎች ያለቅሱ ነበር። ጄሲ ጃክሰን የሰብአዊ መብት ተከራካሪና በ1984 እና በ1988 የዴሞክራቲክ ፓርቲ እጩ ፕሬዚዳንት የነበረ ነው።

የባራክ ኦባማ የእናቱ እናት አያቱ ማድሊን ፓይኔ ዱሃም ምርጫው ኹለት ቀን ሲቀረው ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ. ም. (ኅዳር 23 ቀን 2008 በካንሰር ምክንያት በ86 ዓመታቸው ስለሞቱ በዚህ በምርጫ ወቅት ደስታ ለማየት ጥቂት ቀን ሲቀራቸው በሞት ተለዩ ፤ ባራክን በፍቅር ያሳደጉት አያቱ ናቸው።

ባራክ በዚህ ዓይነት ለፕሬዘዳንትትነት ተመረጠ ። ወደ ዋይት ሀውስ የሚገባበት ቀን ጥር 20 ቀን 2009 ነው ። በዚህ ዕለት የአሜሪካንን ሕግ ለማስፈጸም፣ ለመፈጸም ፤ ሕዝብን ለመምራት ቃለ መሐላውን በካፒቶል ፊት ለፊት ወንጌል ጨብጦ ያደርጋል።

ከፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ብዙ ተስፋ ይጠበቅበታል፦ አሜሪካ በተለይም በከፍተኛ ኹኔታ የተጎዳውን ያሜሪካንን ኢኮኖሚ ያስተካክላል የሚል ምኞት አለ። የአሜሪካ ኢኮኖሚ መናጋት የሌሎችንም አገሮች ኑሮ እያናጋ ነው። ሠራተኞች በወር ደሞዛቸው አስፈላጊውን ነገር ገዝተው ለመጠቀም ያልቻሉበት ኹኔታ ተፈጥሯል ። እነዚህን የመሳሰሉትን ችግሮች ይፈታል ተብሎ በተስፋ ይጠበቃል።

ሥራውን እንደ ጀመረ ወዲያው የአሜሪካንን ወታደር ከኢራቅ ውስጥ ማስወጣት እጀምራለሁ ብሎ ቃል ገብቷል።



# ምዕራፍ ፲፪

## አሜሪካንን የሚያጠቁ አደጋዎች

በዚህ በያዝነው ዘመን ላይ ዓለምን እያስፈራ ያለው የአየር መለወጥ ነው ። የምድራችን ወደ በረሀነት እየተለወጠ መምጣት በሚያሰጋ ኹኔታ ላይ ነው። በክርስቲያን የዕርዳታ ድርጅት ሳምንታዊ መጽሔት በቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ፤ በሚቀጥሉት 40 ዓመታት ውስጥ አንድ ቢልዮን ሕዝብ በድርቅ ፣ በረሀብ እና በውሃ መጥለቅለቅ የተነሳ ከትውልድ አገሩ እንደሚፈናቀል ተዘግቧል። መፈናቀልም ብቻ አይደለም በዚህ የተነሳ መሠረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በሚደረገው ትግል ጦርነት እንደሚቀሰቀስም ተዘግቧል። የኹለተኛው ዓለም ጦርነት መነሻው አንዱ መሠረታዊ ፍላጎት አለመሟላት በተደረገው ትግል ነበር። መከራው ሲመጣ የሌለው ያለውን አካፍለኝ ወይም አስጠጋኝ ሲል ችግር መግጠሙ አይቀርም።

በአኹኑ ጊዜ በዚህ የዓለም አማካይ የሙቀት መጨመርና በሙቀት ብዛት (ግሎባል ወርሚንግ እና ኡዞን ሌየር) የተነሳ ከሰሜኑ ክፍለ ዓለም የበረዶው ክምር ሲቀልጥ የውቅያኖሶች ውሃ ከፍ እያለ እየጨመረ እና እየሰፋ ነው ። በቅርቡ 30 ኪሎ ሜትር ያህል ስፋት የነበረው ለዘመናት ይኖር የነበረው የበረዶ ክምር በመደርመሱ ዓለምን አሳስቧል። በውቅያኖስ ላይ ኀይለኛ ሙቀት በመነሳቱ ወኃው ተኖ ወደ ሰማይ ከፍ ካለ በኋላ አየሩ ሲሞቅ ብዙ ውሃ ያዝላል ፤ ከዚያም በነፋስ እየተገፋ የተነነውን የባሕሩ ዝናብ ተሸክሞት ወደ የብስ በመኼድ መሬት ላይ በመውረድ እያጥለቀለቀ ነው።

> በተነ ጊሜ ረቂቅ ዘየአቁር ለማይ ፤ የዓርጎ እምቀላይ ፤ ወያወርዶ እምኑኅ ሰማይ።ትርጉም
> በረቂቅ ጉም ጢስ (እንፋሎት) ውሃን የሚቋጥረው ከጥልቅ ባሕር ወደ ላይ አውጥቶ ወደ ምድር የሚያወርደው እሱ ነው፤ እንዳሉት ማለት ነው።[209]

ይህ በዚህ ዘመን የተፈጠረው ምድር ላይ እየደረሰ ያለ ከመጠን ያለፈ የውሃ መጥለቅለቅ፤ አውሎ ነፋስ እንዲሁም በድርቅ የሚነሳው ቃጠሎ

[209] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (1417)፤ *ሰዓታት የጸሎት መጽሐፍ።*

በየጊዜው በአሜሪካ በየዓመቱ እየተደጋገመ የሚታይ ነው። በሌሎች አህጉራትም በብዙ ቦታ በቅርብ ጊዜያቶች ታይቷል ፤ ይህም ከሰው ልጆች ቁጥጥር ውጭ ነው።

## (፮) የሚሲሲፒ ወንዝ

በአሜሪካ የታወቀው ትልቁ ወንዝ ሚሲሲፒ ይባላል። ሚሲሲፒ ማለት በአገሬው ተወላጆች ኢንዲያን የጎሳ ቋንቋ ታላቅ ወንዝ ማለት ነው። ይህም አሜሪካንን መሐል ለመሐል ሰንጥቆ የሚጓዝ ጠቃሚ ወንዝ ነው ። ጥቅም መስጠት ብቻም አይደለም ጉዳትም የሚያደርስ ወንዝ ነው። ኹል ጊዜ በሰው ሕይወትና በእርሻ ቦታ ላይ ጥፋት ያደርሳል። ለብዙ ዓመታት በሚሲሲፒ ወንዝ አጠገብ የሚኖሩ ሰዎች ከፍተኛ ዝናብ ዘንቦ ወንዙ ሲጥለቀለቅ እንዳያጠቃቸው ውሃውን መመለሻ የሚኾን ታላላቅ ግንብ ይገነባሉ፤ ግን ይህም አላቆመው እያለ ብዙ ጥፋት አድርሷል።

በሚያዚያ ወር 1927 ወንዙ ሞልቶ የተገነባውን ግንብ ገንጥሎ በየሰው ቤት በመግባት 750,000 ሰዎች ከውሃ በታች በመኾን ጠፍተዋል። አንድ ሚሊዮን እስኩዬር ኪሎ ሜትር የሚኾን መሬት በሰባት ግዛቶች (ስቴቶች) በውሃ ተጥለቅልቋል። በአንድ ቦታ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ራሳቸውን ለማዳን በድልድይ ላይ በመውጣትና በመንጠልጠል ሰዎች እስከሚያድኗቸው ድረስ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ቆይተዋል። በዚህ ታላቅ የጎርፍ መጥለቅለቅ ከሚያዚያ ጀምሮ እስከ ሐምሌ ድረስ በሙሉ ሊቆጣጠሩት አልቻሉም። 350,000 ሰዎች ቤት የለሽ ኾነዋል፤ 300 ሰዎች ሞተዋል ። ባጠቃላይ 300 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ወጭ አስወጥቶ ነበር።[210]

ከዚህ የውሃ መጥለቅለቅ በኋላ የሚሲሲፒ ወንዝን ለመገንባት እና ለመቆጣጠር ዐዲስ ሐሳብ ተነደፈ ፤ ይኹንና ይህም ሐሳብ የውሃውን ኀይል ሊገታውና ሊከላከል አልቻለም። በ1973 እና በ1983 ሌላ የውሃ ማጥለቅለቅ ደርሷል ። በቅርቡ በተጠናው ጥናት የሚሲሲፒ ወንዝ በሃምሳ ዓመት ይዞታው ውስጥ በጣም እየጨመረ መምጣቱ በጥናት ተረጋግጧል ። ወደ ፊትም ይህ የውሃ መጥለቅለቅ እንደማይቀር እንደሚያሰጋ ይነገራል ።

[210] Disaster Oxford U.P. 1998. p., 16



## (፯) ኀይለኛ የውሽንፍር ነፋስ (ኸሪኬን)

ኸሪኬን ዝናብና ነፋስ የተቀላቀለ በጣም ኀይለኛ እንደ ውሽንፍር ያለ ነው ። ዝናብና ነፋስ ተቀላቅሎ ከባሕር ላይ የሚነሳ ሲኾን ለጊዜው ሰላማዊ ይመስላል ። በአሜሪካ በየዓመቱ ከ50 እስከ 100 ሰዎች ይገላል። በጣም የከፋ የነበረው ኸሪኬን አንድርው የተባለው ነበር ።[211] ይህ ዝናብ የቀላቀለ አውሎ ነፋስ በፍሎሪዳ ግዛት ነሐሴ 23 እና 26 ቀን 1992 ባደረሰው ጉዳት $15.5 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ንብረት ጠፍቷል።

ሌላው የበለጠ የከፋው ደግሞ በነሐሴ 23 ቀን 2005 ካትሪና በመባል በሴት ጾታ ስም የተሰየመች ነፋስና ዝናብ ተቀላቅሎ የወረደ አደጋ ከምንጊዜውም የከፋ ነበር። በሉዊዚያና፣ በሚሲሲፒ እና በአላባማ ግዛቶች ላይ የደረሰው ጉዳት በአሜሪካ ታሪክ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኝ የእግዜር ቁጣ ነበር።

እነዚህ የተጥለቀለቁ ሦስት ግዛቶች የቆዳ ስፋታቸው ታላቂቱን ብሪታንያንን ያክላሉ። መአቱ በወረደ ጊዜ የሉዊዚያና ታላቂቷ ከተማ ኒው ኦርሊን ከውሃ በታች ኾነች ። በኖኅ ዘመን እንደ ነበረው ያለ መጥለቅለቅ አጋጠማት።

> ውሃውም በምድር ላይ እጅግ በጣም አሸነፈ ፤ ከሰማይም በታች ያሉ ታላላቆች ተራሮች ኹሉ ተሸፈኑ ። ውሃው ወደ ላይ አሥራ አምስት ክንድ ከፍ ከፍ አለ ተራሮችም ተሸፈኑ።
> (ዘፍ. 7፥19 ፤ ማቴ. 24፥37)

ይህ በኖህ ዘመን በሰው ልጆች ስሕተትና ጥፋት የተነሳ ከፈጣሪ የታዘዘው ቁጣ ያስከተለው የጥፋት መጥለቅለቅ የደረሰ በቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈ ነው።

ኸሪኬን ካተሪን በኒው ኦርሊን ከሰማይ በወረደው ውሃ ምድሪቷ ተጥለቀለቀች በብዙ ሺህ የሚገመት ሕዝብ አለቀ ፤ ቤቶች ፈራረሱ፤ ብዙ ንብረትም ወደመ ። ሰኞ ነሐሴ 23 ቀን የአሜሪካ የሄሪከን ማዕከል ማስጠንቀቂያ ሰጠ። ሐሙስ ነሐሴ 25 በፍሎሪዳ ጠረፍ ላይ ደርሶ 9 ሰዎችን ገደለ። ከአንድ ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ መብራት ኃይል አጡ። ይህ የኤሌክትሪክ ኃይል ከመሠረታዊ ነገሮች አንዱን እና ዋናውን ነው።

[211] **DISCOVERY CHANNEL** *Raging Planet Hurricane 10334*

ካተሪን በሜክሲኮ ጠረፍ ኃይሏ እየጨመረ በመጣ ጊዜ ባለ
ሥልጣኖች በሉዚያና ግዛት ታላቂቷ ከተማ ኒው ኦርሌን ያሉት ነዋሪ
ዎች በቶሎ ለቀው እንዲወጡ አዘዙ ። የውሃ ሙላት ወደ ማይደርስ
በት ከፍተኛ ቦታዎች ለመኼድ በሩጫ ሽሽት ኾነ። መንገዶች በመኪና
ተጓዥ ተጨናነቁ ። አንድ ሚሊዮን የሚደረስ ሕዝብ ለማምለጥ በመ
ንገድ ላይ ነበር ። መሸሻ የሚኾን መኪና የሌላቸው ደሀ ጥቁሮች
ቀሩ። ዐርብ ከንጋቱ 12 ሰዓት (6.a.m.) ላይ ኸሪኬን ካትሪና አገሪቷን
መምታት ጀመረች ። ወደ ላይ ውሃ እየጨመረ ሲመጣ በቤት ውስጥ
ያሉ ሰዎች ወደ ጣራ ላይ መውጣት ጀመሩ ። መውጣት ያልቻሉ
አቅመ ደካሞች ግን ተዋጡ ። የአካባቢው የራዲዮ ጣቢያ ብዙ ሰው
እንደሰጠመ እና በውሃው ጎርፍ እየተወሰደ አስከሬን ሲንሳፈፍ በቴሌቪ
ዢን ጭምር ያሳዩ ጀመር ፤ በዚህም ከአንድ ሺ ሰው በላይ ሞተ።

ይህ ኹሉ ሲኾን ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ ዕረፍት ላይ ነበር ።
የአሜሪካ ሕዝቦች የጉዳዩ ክብደት አላሳሰበውም በማለት ብዙዎቹ
ተቹት። ጥፋቱ ከደረሰ ከሦስት ቀን በኋላ ፕሬዚዳንት ቡሽ ብቅ አለ።
በዚህ ጊዜ ፈጥኖ ደራሽ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ ። ሉዊዚያና እና
ሚሲሲፒ ጠረፍ ላይ ያሉት የነዳጅ ማጣሪያዎች እንዲሁም በውቅያ
ኖስ ያሉት የነዳጅ ማጣሪያዎች ተናግተው መፈራረስ ጀመሩ ። ይህ
የነዳጅ ማጣሪያ 26 ቢሊዮን የሚገመት ጥፋት ደረሰበት ። ወዲያው
የነዳጅ ዋጋ በአውሮፓ እንዲሁም በሌሎች አገሮች ጨመረ። ጸሎት
በየቦታው መጸለይ ተጀመረ።

> ነገር ግን ድንጋጤ እንደ ጎርፍ በደረሰባችሁ ጊዜ፤ ጥፋታችሁ
> እንደ አውሎ ነፋስ በመጣ ጊዜ፤ ጭንቅና መከራ በደረሰባችሁ
> ጊዜ ። የዚያን ጊዜ ይጠሩኛል። (ምሳሌ. 1፥27)

የተባለው ዓይነት ኾነ።
80 በመቶ ኒው ኦርሌን ከተማ ከውሃ በታች ኾነች። 25ሺ የሚኾኑት
በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩት ይበልጡን አፍሪካን አሜሪካን የኳስ ሜዳ
እስታዲዮም ውስጥ ሰፈሩ። ሕገ ወጥነት ወንጀል መፈጸም እና ለመዝ
ረፍ ኹሉም ይሯሯጥ ጀመር ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችና 7,500
የሕግ እስረኞች በከተማዋ ከፍተኛ የመኪና መንገድ ላይ በመውጣት
ያለቅሱ ነበር። ሰዎችን በሄሊኮፕተር ወደሌላ ቦታ ማጓጓዝ ተጀመረ።
ስደተኛ በመኾን በሂዩስተን ፣ ባተን ሮጁ ፣ ሳን አንቶንዮ ፣ ዳላስ ፣
ሜንፊስና ቴኔሲ ሰፈሩ።

18 የሚደርሱ የኤጲስኮፓል አብያተ ክርስቲያናት ሌሎችም
የጸሎት ቤቶች ሳይቀሩ በውሃ ተጥለቀለቁ፤ በጎርፍና በነፋስ ተወስደው



ፈራረሱ ፤ ፕሬዘዳንት ቡሽ በኸሪኬን ካትሪና የተጥለቀለቀው ቦታ ታላ
ቋን ብሪታንያን ያክላል በማለት መግለጫ ሰጠ። ይህም ብቻ አይደለም
አሜሪካ ወደፊት ለሚመጣባትና ለሚደርስባት አደጋ መዘጋጀት አለብን
በማለት ንግግር አደረገ። በአጠቃላይ 400,000 ሺ ሰው ሥራውን አጣ።

ርዳታ ከአውሮፓ አገሮች ለተጎዱት ቦታዎች መላክ ተጀመረ፤
ምግብ ፣ ልብስና መድኃኒት እነዚህ በአፋጣኝ መድረስ የሚገባቸው
ነበሩ ። ጀርመንና እንግሊዝ 500,000 ሺ የታሸገ ምግብ በ24 ሰዓት
ውስጥ አደረሱ። ፈረንሳይ ድንኳኖችን ፤ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎች
የመሳሰሉትን ለማድረስ ተፋጠኑ። የዳች (ኔዘርላንድስ) መንግሥት መድ
ኃኒትና ሔሊኮፕተርን ፤ ግሪክ ብርድ ልብስና አልጋ ፤ ስዊድን የእጅ
ስልክ ሞባይልና መጠጋገኛዎችን። ሩማንያና ሌሎችም አገሮች ባላቸው
አቅም ተራዱ ። ዓለምን መሪና ሀብታም ነች ለተባለች አገር ርዳታ
አደረጉ ፤ በአገሩ ወስጥ ያሉት ግዛቶችም ተባበሩ።

ወዲያው መስከረም 20 አካባቢ ሌላ ኸሪኬን ከሜክሲኮ ጠረፍ
ተነሳ፤ ስሟን ሪታ አሏት። ሪታ እየተንከባለለች መጥታ በቴክሳስ ጠረፍ
መስከረም 23 ደረሰች ። ከቴክሳስ ሂዩስተን በሚያስጨንቅ ኹኔታ
አኹንም ስደት ወደ ዳላስ ከተማና በየአቅጣጫው ተጀመረ ። በአ
ሜሪካ ታሪክ በድጋሚ ኹለት ሚሊዮን ሕዝብ ሽሽት ጀመረ ፤ ታላቁ
የመኪና መንገድ ተጨናነቀ። 24 ጡረተኞች በዕድሜ የገፉ በአውቶቡስ
ተሳፍረው ሲኼዱ ዳላስ ለመድረስ ሲቃረቡ ሞተሩ ግሎ ከመኪናው
ሳይወርዱ ተቃጥለው ሞቱ ። ሪታ በቴክሳስ 4 ቢሊዮን ንብረት አጠ
ፋች ። በሽሺቱ ወቅት ከሂዩስትን ያሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ
ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳታቸውንና ታቦተ መድኃኔዓለምና ታቦተ ኪዳነ
ምሕረትን ይዘው ወደ ዳላስ ሚካኤል ለማዳበል ጉዞ አድርገው ነበር።
በሉዚዊያና ፣ በአላባማና በሚሲሲፒ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት
ገና አልተመሠረቱም ነበር።

ይህም የመጥለቅለቅ አደጋ ዓለምን ኹሉ አስደንግጧል ። በዚ
ያው ልክ ደግሞ አስተዛዝቧል። "ላለው ኹሉም ያሸረግዳል" እንደሚባ
ለው ደሀ አገር እንኳን ሳትቀር አሜሪካንን ለመርዳት ተሳትፋለች ።
ነገር ግን በሱዳን ዳርፉር 4 ሚልዮን ተኩል ሕዝብ መጠለያ ፣ ምግብ
እና መድኃኒት ለዓመታት አጥቶ በበርሃ ሲንከራተትና ሲሰቃይ በዜና
ማሰራጫ እንዲህ ኾነ ሲባል ከመስማቱ በስተቀር የሚደረግ አፋጣኝ
የርዳታ እንቅስቃሴ ብዙ ባለመኖሩ ትዝብቱ እዚህ ላይ ነው።

## (፪) ኀይለኛው አውሎ ነፋስ (ቶርኔዶ)

ሌላው በአሜሪካ ድንገተኛው መቅሰፍት ኾኖ የሚታየው ቶርኔዶ የሚባለው በጣም ኀይለኛው ንፋስ ነው። እየተሽከረከረና እየተጠቀለለ የሚጓዝ ትልቅ ክፍታ ያለው መሐሉ እንደ ቧንቧ ክፍት የኾነ ነው ። ሲመጣ ለመዘጋጀት እንኳን ጊዜ አይሰጥም። ይህም በሚያስደንቅ ፍጥነት አየሩን እንዲገፋ ያደርገዋል። በሰዓት ከ480 ኪሎ ሜትር በላይ ይጓዛል። ይህ ነፋስ አሜሪካንን ኹል ጊዜ የሚያጠቃ ነው። በተለይም በመካከለኛው ምዕራብ በየዓመቱ የማይቀር መኾኑ የታወቀ ነው።

ቶርኔዶ በተነሳ ጊዜ ብዙ ንብረት ያወድማል፤ ሕንጻዎችን ያፈራርሳል፤ ሰዎችን ይጎዳል፤ ይህ ኀያል ነፋስ መቼ እንደሚመጣ እና ምን እንደሚያደርግ ወይም እንደሚያጠፋ አይታወቅም ። ነፋሱ ሲመጣ የሚሰጠው ምክር፤ የምትኖሩበት ቤት ምድር ቤት ካላው ወደ ምድር ቤት ውረዱና ተቀመጡ የሚል ነው ። ከመድረሱ በፊት ለመዘጋጀት እንኳን ዕድል ባለመስጠቱ ለዓመታት በአሜሪካ የብዙ ሰዎችን ሕይወት አጥፍቷል። በመኻለኛው ምዕራብ አገር ከሜክሲኮ ጠረፍ እስከ ሰሜኑ ካናዳ ብዙ ንብረት አውድሟል። በተለይም በመጋቢትና በሐምሌ ወራት መሐከል ቶርኔዶ የሚነሳ መኾኑ የተለመደ ነው ።

ሚያዚያ 2 እና 3 ቀን 1974 ለስምንት ሰዐታት በመካከለኛው ምዕራብ የተነሳው ቴርኔዶ 324 ሰዎችን ገድሏል። በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎችን አቆሳስሏል ። 400 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ንብረት የእርሻ ቦታን፣ ቤቶችንና ሕንጻዎችን አጠፋፍቷል። የዘጠኝ ዓመት ልጅ ውጪ እየተጫወተ በድንገት ቶርኔዶ ብድግ አድርጎ 180 ሜትር ላይ ካደረሰው በኋላ አውርዶ መሬት ላይ ፈጥፍጦ ገድሎታል።[212] ባጠቃላይ ከ1900 እስከ 1969 መኻል ቶርኔዶ 12,000 ሰዎችን ገድሏል።[213]

አውሎ ነፋስ (ቶርኔዶ) ግንቦት 4 ቀን 2003 እሑድ ቀን ስምንት ግዛቶችን (እስቴት) ሲመታ 41 ሰዎችን ገድሏል። በዚህ ነፋስ (ቶርኔዶ) በጣም ብዙ ቤቶች እንዳልነበሩ ኾነው ወድመዋል።
እሑድ ሚያዚያ 2 ቀን 2006 ተነስቶ የነበረው ቶርኔዶ ክራይስት ዩናይትድ ሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን የሚባለውን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ከስሩ መንግሎ ብትንትኑን በማውጣት አድቆታል።[214]

[212] Norman Pearlstine *Time Annual.,*
[213] *Disaster Oxford U.P. 1998. p., 18*
[214] Reader's Digest December 2009 p. 148



ስለ ቴርኔዶ ከተነሳ ብዙ ነገር አለ ፤ በቅርቡ ግንቦት 4 ቀን 2007 በካንሳስን ግሪንስበርግ 8 ሰዎች ሲሞቱ ከተማዋ ውስጥ ያሉት ቤቶችና ትምህርት ቤቶች ተደመሰሱ ፤ የሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሳይቀር ተደመሰሰ። ይህ ለምሳሌ ያህል ተጠቀሰ እንጂ ቶርኔዶ በአሜሪካ ምድር በየዓመቱ አቋርጦ አያውቅም። በሰው ላይና በንብረት ላይ በየዓመቱ ጉዳት ያደርሳል።

## (፫) ሰደድ እሳት

በአሜሪካ በበጋ ወራት ደረቅ በኾኑ ግዛቶች ሰደድ እሳት ይነሳል ። የዚህም የእሳት መነሻው ዋና ምክንያቶች የሲጋራ ቁራጭ ፣ መብረቅ እና በነፋስ የተነሳ እንጨት ከእንጨት ሲተሻሸ በሚፈጥረው ሰበቀት ሙቀቱ ጨምሮ እሳት መቀጣጠል ይጀምራል። እንደዚሁም በጥንቃቄ ጉድለት ኾን ብለው እሳት የሚጭሩ ሌላም መነሻ አለው።

በጥቅምት 27 ቀን 2003 ወርቃማው ግዛት (እስቴት) የተባለው የደቡብ ካሊፎርኒያ ሳንዲያጎ በተባለው ክፍል ከዱር የተነሳው ትንሽ እሳት በዙ ጉዳት አድርሷል ። ይህ እሳት ደረቅ ሳር ላይ መንደድ ጀመረ ። በዚህ የተነሳ ንፋሱ እያግለበለበው ሰደድ እሳቱን በቀላሉ እየተግለበለበ መቀጣጠል ጀመረ፤ ይህንን እሳት ማቆም አልተቻለም። በሰሜኑ ምሥራቁ ሳንዲያጎ ቤቶችና ጫካው መቀጣጠል ጀመሩ 14,000 የሚደርሱ ነበልባሉን የሚያጠፉ የእሳት አደጋ ሠራተኞች ተሰማርተው ሊቆጣጠሩት-አልቻሉም። 750,000 ኼክታር አጠፋ ። ከከተማ ወጣ ያሉት 3,000 ቤቶች እንዲሁም 20 ሰዎች የቃጠሎው ሰለባ ኾነዋል።[215] ይህ የሳት ቃጠሎ በካሊፎርኒያ ታሪክ የከፋ ጥፋት ያደረሰ ነው።

እንደገና በሌላ ጊዜ ጥቅምት 25 ቀን 2007 በሰሜን ምሥራቁ ሳንዲያጎ ተነስቶ ከነበረው ቃጠሎ የበለጠ የደቡብ ካሊፎርንያ ግዛት ጀምሮ በአውሎ ነፋስ እየተገፋ ባለማቋረጥ ለሳምንታት ያህል ተቀጣጠለ። ይህ የሰደድ እሳት ቃጠሎ ይዞት የነበረው ቦታ የኒው ዮርክ ከተማን ስፋት ያህል ነበር ። በዚህ ቃጠሎ የተነሳ 10, 000 ሺህ ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው መኪናቸውን እያስነሱ መሸሽ ጀመሩ ። ቀን እና ሌሊት ሰማዩ ቀልቶ ከርቀት ይታይ ነበር ። በዚህ ክልል ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች አብዛኛዎቹ በጣም ሀብታሞች የኾኑ ከድሆች ጋር አንኖርም

[215] Norman Pearlstine Time Annual.,2004 San Diego Union Tribune

ብለው በየተራራው ላይ ቪላ ቤት የሠሩ የሆሊውድ የፊልም ሠራተኞች እንዲሁም ታላላቅ የንግድ ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ ነው። እነዚሁ ሀብታሞቹ ወደ ሁቴል ሲኼዱ፤ መለስተኛ ኑሮ የሚኖሩት ደግሞ በእስታዲዮም እና በትምህርት ቤት አዳራሽ ተጠለሉ። 10,000 ሺህ ሰዎች በሳ-ንዲያጎ እስታዲዮም በመጠለያ ውስጥ ሠፍረው ነበር።

ይህ ቃጠሎ በምን ምክንያት እንደተነሳ በግልጽ የታወቀ ነገር የለም ። አንዳንዶች እንደሚሉት ኾን ተብሎ በሰዎች የተደረገ ነው ይላሉ።

ይህንን ሎሳ አንጀለስ፣ ሳንታ ማርያ፣ ሳንታ ባርያ፣ ሳን-ዲያጎ ክልል (ካውንቲ) የተነሳውን የሰደድ እሳት ለማጥፋት በሰማይ ካርጎ አውሮፕላን ኬሚካል እየጫኑ እንዲሁም ሄሊኮፕተር ውሃ ከውቅያኖስ ላይ በማፈስና በሳቱ ላይ በመርጨት ለማጥፋት ተሞከረ ፤ በምድር 9000ሺ የእሳት አደጋ ሠራተኞች ሌሊትና ቀን ያለ ዕረፍት ለማጥፋት ተሳትፈውበት ነበር። ነገር ግን እሳቱን በቀላሉ ሊቆጣጠሩት አልቻሉም ነበር ።

በዚህ የሰደድ እሳት 40 ሺህ ቤቶች ተቃጠሉ። 1.2 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ንብረት ጠፋ ። በሸሸት ላይ እያሉ በእሳት በመከበባቸው ማስፊያ መንገድ አጥተው 12 ሰዎች ሲሞቱ ወደ 45 የሚደርሱት በእሳት ተለብልበው ቆሳስለው ነበር ። ይህ የሰደድ እሳት ለማጥፋት በተደረገው ያልተቋረጠ ርብርብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቆጣጠሩት ቻሉ።

የሰደድ እሳት ይህን በመሰለ ኹኔታ በየዓመቱ በሰው ላይና በንብረት ላይ በተለይ ጥፋት ያደርሳል ። ይህም የሰደድ እሳት በጣም ጎልቶ የሚታየው በምዕራቡ የአሜሪካ ክፍል ነው። እነዚህ የተገለጹት አደጋዎች አሜሪካንን በድንገት የሚያጠቁና የሚያፈራርሱ ናቸው።

## (፭) የመሬት መንቀጥቀጥ

በያዝነው ክፍለ ዘመን በፈጠነ ኹኔታ በዓለም ላይ የመሬት መንቀጥቀጥ ይታያል በአለፉት ቅርብ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከ2003 ጀምሮ አልጄርያ፣ ኢራን፣ ቱርክ፣ ህንድ፣ ፓኪስታን በሌሎችም የመሬት መንቀጥቀጥ ታይቶ ብዙ ሰዎች አልቀዋል፤ ብዙ ንብረት ወድሟል።

በአሜሪካ በሳንፍራንሲስኮ ይህ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ደርሶ ነበር ። ይህች ከተማ በጣም የደመቀች ከተማ ናት ። የተመሠረተችው በከፍተኛ ቦታ ላይ ነው። ከዓለም በርዝመቱ ተወዳዳሪ የሌለው ድልድይ አላት ፤ ርዝመቱም 1280 ሜትር ይደርሳል ። በቀን 100,000 መኪናዎች በላዩ ላይ ያልፋሉ።[216] በዘህች ባሸበረቀች ሳንፍራንሲስኮ ከተማ ወደፊትም ይህ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደማይቀርላትና እንደሚያሰጋት በባለሙያዎች ይነገራል።

በሚያዚያ 18 ቀን 1906 በዚሁ ቦታ የመሬት መንቀጥቀጥ ተነስቶ ወዲያውኑ 5,000 ሕንፃዎች ተገለባብጠው ፈራርሰው ነበር። በዚህ የመሬት መንቀጥቀጥ 3,000 ሺ ሰዎች ሲሞቱ 300,000 ሺ ሰዎች ቤታቸውንና ንብረታቸውን አጥተዋል እንዲሁም በ1989 ሌላ የመሬት መንቀጥቀጥ በዚሁ የምዕራብ የአሜሪካ ክፍል ተነስቶ ነበር ፤ በሰዎችና በንብረት ላይ ጥፋት አድርሷል።

ዛሬ ይህ ዓይነቱ የመሬት መንቀጥቀጥ ይደርሳል ተብሎ የሚፈራበትና የሚጠረጠረው ቦታ ኹሉ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ቤቶች ከመሠራታቸው በፊት ጥንቃቄ ይደረጋል ። የሚሠሩት ቤቶች መሬት መንቀጥቀጥ ሲደርስ እንዲቋቋሙት ተደርጎ ነው።

## ማጠቃለያ

በዚህ በሥልጣኔ ዘመን ከኮለምበስ ጀምሮ ከክርስትና እምነት ጋራ ተያይዞ የመጣው የአሜሪካ ኑሮ እና ከአውሮፓ፣ ከእስያ፣ ከአፍሪካ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ ተሰደው በአሜሪካ ነዋሪ የኾኑትን ሕዝቦች ያለውን የኑሮና የታሪክ ግኑኙነት አይተናል ። ፕሬዚዳንቶች፣ የሰብአዊ መብት ተካራካሪዎች፦ አስደሳቹም፣ አስከፊም ታሪክ በአሜሪካ ምድር ተፈጽሟል።

ከቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች የተወረሰው የአሜሪካ የዲሞክራሲ ባህል እንዲሁም ኹሉም የሰው ዘር እኩል ነው የሚለው ፤ የነጻነት፣ የፍትህ፣ የሰብአዊ መብት አክባሪ ሞዴል ነኝ የምትል ሀገር በተቃራኒ የሌሎችን ሀገሮች ብሔራዊ መብት በኀይሏ በመጠቀም ስትነፍግ ኖራለች። ፕሬዜዳንት ባራክ ኦባማ ግን ይህን ኹሉ የጥላቻ ስም ዐድስ ዋለሁ የሚል ምኞት አለው።

አገራቸውን ለቀው ከተለያዩት የዓለም ክፍል የሚገቡት ኹሉ ኑሮን ለማሸነፍ የሚያደርጉት መፍጨርጨር እንዲሁም በአገር ቤት ወደኋላ ጥለው የኼዱትን ቤተሰቦችና ራስን ለመርዳት፤ ተምሮ ራስን ለመለወጥ የሚደርገው ሩጫ ቀላል አይደለም ። አሜሪካ ለባህሏና

[216] John Escott, California Oxford 2001 p., 4

ለቋንቋዋ እንግዳ ለኾነ ቀርቶ እዚያው ተወልዶና ጥርሱን ነቅሎ ላደገባት ጥቁር ሕዝብም በሙያው ሥራ ፈልጎ ማግኘት በቀላሉ የማይቻልበት አገር ነው። በአገራቸው በከፍተኛ ሙያ ላይ ተሠማርተው ይሠሩ የነበሩ ባለሙያዎች ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ መሐንዲሶች (ኢንጂነሮች) ሌሎችም በአሜሪካ አንዳንዴ አነስተኛና የጉልበት ሥራ ላይ መሠማራት የተለመደ ነው።

አሜሪካ የሰለጠነ የሰው ኀይል ለማግኘት ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ ፖሊሲ አላት። ይህውም ማንኛውም ነገር ቅድሚያ ለአሜሪካ የሚለው ነው። ሎተሪ (ዲቪ) ደርሷቸው ከአገራቸው ወደ አሜሪካ ለሚኼዱ እንኳን የዐሥራ ኹለተኛ ክፍልን ማጠናቀቅ እንደሚያስፈልግ ይጠየቃል ።

አሜሪካን ብዙዎች በርቀት ላይ ኾነው ለሚያዩዋት ሰዎች በቀላሉ የሚኖርባት ፤ ገንዘብ በቀላሉ የሚታፈስባት ይመስል ይኾናል ፤ ውስጡ ተገብቶ ሲታይ ግን ኑሮን አሸንፎ ለመኖር ፤ በትጋትና በንቃት ሌሊትና ቀን ፤ ክረምቱ ሲመጣ በቁርና በበረዶ ተጨማዶ እንዲሁም በጋው ሲመጣ በሐሩር ተለብልቦ ፤ የባለጸጋው አሠሪ ፊት እንደ ረመጥ ገርፎ ፤ ከሥራ ብዛት የተነሳ የቆሙበት እግር አብጦ፤ ሰውነት ደንዝዞ፤ ወገብ ተቆርጦ ፤ የውስጥ እግር ነዶ "ጥረህ ግረህ ብላ" ከተባለው በላይ ተለፍቶ የሚኖርበት አገር ነው። ከድካም የተነሳ ራቱን ሳንድዊች ዳቦ ገምጦ ሳይጨርሰው በዚያው አልጋው ላይ እንቅልፍ ይዞት የሚኼደው ብዙ ነው ። ይህን ልፋት ያልተረዱት እንደምንም ተማጥረው ከደረሱ በኋላ እውነቱ ሲታይ ይህንን ባውቅ ኖሮ ከአገሬ እግሬን አላነሳም ነበር በማለት የሚበሰጫጩ ብዙዎች ናቸው።

በኢትዮጵያም ኾነ በአፍሪካ ይተኛል፤ ጊዜ በከንቱ ይባክናል፤ ሐሳብን አፍልቆ ሥራ መሥራት ገና ብዙ ይቀራል ። በአሜሪካ ሥራ አይናቅም ፤ አሜሪካ የሚተኛው ከምሽቱ ስድስት ሰዓት እስከ ጠዋቱ አሥራ ኹለት ሰዓት ነው ። (ብዙ ጊዜ የእንቅልፍ ሰዓቱ ከስድስት ሰዓት በታች ነው።) በዚህ አይነት ጥረትና ትግል ሕይወት ላይ ለውጥ ይመጣል።

በአሜሪካ ዐዲስ በመኾን የሚገቡት ብስጭቱንና ጭንቀቱን አልፈው ኑሮውን ሲለምዱት፤ ቀስ እየተባለ ሲዋሐዳቸው ፤ ዶላሩ እንደ ባሕር ጨው ሲጥማቸው ደግሞ መኖር አሜሪካ ነው እንጂ! አሜሪካንን ወድጀዋለሁ! የሚሉም ሞልተዋል። ከዚያም እኔ አፍ ባይኖረኝ (እንግሊዘኛ መናገር ባልችል) ገንዘቤ "አፍ አላት" (Money Talks) የሚለው ብሂል የአሜሪካ አንዱ ባህል በመኾኑ ይህም ይወረሳል ማለት ነው።



በአሜሪካ በሀብት የበለጸጉት ደግሞ የመንደራቸው ዙሪያው በፖሊስ ተጠብቆ በመንደላቀቅ የሚኖርበት አገር ነው ። ሀብት ለማግኘት ኑሮን አሸንፎ ለመኖር ሲባል እውነትን ለውጦ ሽምጥጥ አድርጎ ውሸት በማድረግ ቅጠፍትና ማጭበርበር የተለመደ ነው ። ውሸት ስለተለመደ ኃጢአት መኾኑ ቀርቷል ። ገንዘብ ለማግኘት አሠሪ በሠራተኛው ላይ ትርፍ ለማግኘት የሚያደርገው የሥራ ጫና ቀላል አይደለም። ይህም ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ የእርሻ ከበርቴዎች በባርነት ቀንበር የያዙትን ሲያንገላቷቸው እንደነበረ ዛሬም ያን ጊዜ የነበረው ባህል በተዘዋዋሪ ቀጥሎ ገንዘብ ለማግኘት ፤ ሀብት ለማትረፍ ምንም ይሉኝታ የለም ። ይህም ዛሬ ለሚታየው የኑሮ ውድነት አንዱ የኢኮኖሚ መቃወስ ምክንያት ነው።

ዛሬ በአሜሪካ ባርነት በውዴታ መልኩን ለወጥ ብሎ የሚታይበት ነው ። ኑሮውን ለማሸነፍ ኹለት ሥራ በመሥራት በመሠማራቱ እንደኢትዮጵያው ማኅበራዊው ኑሮ ብዙ የለም ፤ ኢትዮጵያዊው በቀላሉ ሆደባሻ ነው። በተለይም በአገር ጉዳይ በጣም ይቆጫል።

ሌላውም የአሜሪካ ነዋሪ ባሕሪው ለየት ያለ ነው ። ከመፈራራቱ የተነሳ ቤቱን ዘግቶ መኖርን ይመርጣል። ሰዎች ሲገናኙ የመጀመሪያው የመነጋገሪያ አጀንዳ ከወዴት አገር ነህ? (Wher are you from?) የሚል ነው ። ይህም ማንነትን ለማወቅ የመጀመሪያ የግምገማ ንግግር ነው ፤ ከመፈራራት የተነሳ መኾኑ የታወቀ ነው ። ከችግር ነጻ የኾነ አገር ባይኖርም አሜሪካ የዘር፣ የቀለም፣ የአኗኗር ልዩነቶችና የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች አሉባት።

የዕለት ጉርስ ባይታጣም ሀብት ማግኘት ብቻ ሳይኾን ድህነትም በአሜሪካ አለ ። ከገንዘብ እጦት ከችግር የተነሳ ዕድሜውን ሙሉ የመንገድ ዳር ምግብ ወይም ማክዶናልድ እየተመገበ የሚኖር ፤ በዕፀ ፋርስ ሱሰኛ ኾኖ ስመ እግዚአብሔርን ሳይጠራ አባክህ ገንዘብ ስጠኝ እያለ በየመንገድ ዳር ሲለምን የሚውል ሞልቷል።

በአሜሪካ መሐይምነትም አለ ። ጋዜጣ ማንበብ እንዲሁም የመንገድ ምልክት ማንበብ የማይችሉም አሉ ። አንዳንዶቹ ከደጉ በኋላ መማር ስለሚያሳፍራቸው ራሳቸውን በመሸሸግ የሚኖሩ እንደኾነም ተገልጿል። ለምሳሌ ማክስሊ የምትባለው የ41 ዓመት የነጭ ወይዘሮ ጋዜጣ ማንበብ የማትችል ፤ የሥራ ፎርም መሙላት የማትችል፤ በገበያ በሱቅ የተደረደሩትን የምግብ ዓይነቶች አንብባ መግዛት እንደማትችል፤ ይህንንም ችግሯን ለ30 ዓመት ያህል ማንም እንዲያውቅባት

ስትሸሽግ ኖራለች። ይህንን ከገለጸች በኋላ ግን መማር ጀምራለች ። በቅርቡ በተጠናው ጥናትና በተሌቪዢን በቀረበው ሪፖርት 7 ሚሊዮን የአሜሪካ ነዋሪ አንዲት ቃል አያነቡም ፤ 27 ሚሊዮን ደግሞ ሥራ ለመቀጠር ፎርም እንኳን መሙላት አይችሉም፤ 30 ሚሊዮን ዐረፍተ ነገር ማንበብ እንደማይችሉ ተገልጿል። ይህም የኾነበት የተለያየ ምክንያት ይነገራል ። በልጅነታቸው መጠጥ ጠጪዎች ኾነው የሚቀሩ አሉ ፤ ብዙ ስደተኞች ጨርሶ ትምህርት አይማሩም ፤ በድህነት የሚኖሩ አፍሪካን አሜሪካን አይማሩም፤ ነጮቹም የማይማሩ አሉ።[217]


ይህ ኹሉ ሲታይ አንድ በእግዚአብሔር ሥር የሚተዳደር ሕዝብ (ONE NATION UNDER GOD)እንዲሁም የነጻነት አዋጁ ፥ ኹሉም የሰው ዘር የተፈጠረው በእኩልነት ነው የሚለው ,በሰው ተፈጥሮአዊነቱ እኩል ቢኾንም በሥራ ግን በተግባር ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነት አግኝቷል ማለት አስቸጋሪ ነው ።

ለትንሹም ለትልቁም ሽጉጥና ስለት የሚመዘዝበት ተፈራርቶ የሚኖርበት ነው። አስፈራርቶ የሚደረገው ቅሚያ አሜሪካንን ይህ አሜሪካ ነው! (ዚስ ኢዝ አሜሪካ!) የሚባለውን ስም አሰጥቷታል ። ይህም ማለት ክፉም አለ በጎውም (ነጻነት) አለ ለማለት ነው።

ካለው ውጣ ውረድ ፤ ከሚደረሰው ጭንቀት ፤ ፈተናና በኃጢአት መውደቅ የተነሳ ሕዝቡ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ፤ እግዚአብሔርን ፍለጋ እና ወደ እግዚአብሔር መማለድ ይፈልጋል ። ለዚህም የአምልኮት ቦታ የሚኾነውን ቤተ ክርስቲያን አቋቁማል ፤ እያቋቋመም ነው።

[217] ABC news .com Illiterate in America 26 February 2008

# ክፍል ኹለት



## የክርስትና እምነት በአሜሪካ

# ክፍል ኹለት

## የክርስትና እምነት በአሜሪካ

በዓለም ሦስት ታላላቅ የክርስትና የእምነት ቡድኖች (ዲኖምኔሽን) አሉ። እነዚህም ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት ናቸው ። እነዚህ ምሥራቅና ምዕራብ በመባል ተለይተዋል ። ምሥራቅ ተብሎ የሚጠራው ኦርቶዶክሱ ዓለም ሲኾን፤ ምዕራቡ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት በመባል ይጠራሉ። እነዚህ ኹሉ በአሜሪካ ተበደው የሰፈሩ የክርስትና እምነቶች ናቸው።

ከየአህጉራቱ ወደ አሜሪካ የተሰደደው ሕዝብ ከአገር የወጡ ካህናቱን፣ መምህራኑን፣ መሪዎቹን በመከተል ማኅበራዊ ኑሮውን ፣ ሐዘንም ኾነ ደስታ ፤ ሠርግ ይኹን ክርስትና የሚፈጽምበት ፤ ባህሉንና እምነቱን ፤ አምልኮቱን ለመፈጸም ከአምላኩ ጋር የሚገናኝበት ቤተ ክርስቲያኑን ያቋቁማል ። ቤተ ክርስቲያን ሲያቋቁም የአስተዳደር ችግር ፤ የሐሳብ ልዩነት እየተፈጠረ ጭቅጭቅና ንትርክ የማይቀር ነው። ይህም ችግር በኢትዮጵያኖችና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይኾን በኹሉም የክርስትና እምነት ውስጥ የተፈጠረ የኖረና ያለ የሚቀጥልም ችግር ነው።

ዋናው የመለያየት ችግሮች በአስተዳደርና በመሠረተ እምነት (ዶግማ) ልዩነት ነው ። ከአስተዳደር ችግር ይልቅ የሚከፋው በመሠረተ እምነት (ዶግማ) ልዩነት ሲፈጠር ነው ። ይህም ራሱን የቻለ የክርስትና የእምነት ዘርፍ እንዲፈጠር (ዲኖምኔሽን) ያደርገዋል ። በአስተዳደር የሚፈጠር ችግር የኾነ እንደኾነ ግን ጊዜ ጠብቆ አንድ እንደሚኾን የታወቀ ነው። የመለያያ ምክንያቶች ብዙ ናቸው፤ ግማሹ ኅብረተሰብ አገር ውስጥ ባለው አስተዳደር ለመመራት ሲያስብ ፤ ሌላው ደግሞ ሸሽቶት በአሳደደው ባለሥልጣናት አስገዳጅነት ሳይጨነቅ ነጻ መኾንን ይመርጣል። ሌላው ደግሞ ከሃይማኖቱ ጋራ በተያያዘ ፖለቲካ ልዩነቶች እየሰፉ ይኼዱና መለያየት ይመጣል ማለት ነው። •

በዚህ ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ አሜሪካ ሲደርሱ በአስተዳደር ፣ በፖለቲካ ወይም በመሠረተ እምነት አመለካከት በሌሎችም ምክንያቶች ይከፋፈላሉ።

# ምዕራፍ ፲፫

## ኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ

ኦርቶዶክስ ቃሉ የግሪክ ሲኾን ቀጥተኛ እምነት ማለት ነው ። ይህም የተወሰነው በኒቅያና በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ነው ። የእስክንድርያ መንበር፣ የቁስጥንጥንያ መንበር ፣ የሮም መንበር ፣ የኢየሩሳሌም መንበር እነዚህ አራቱ የጳጳሳት መንበር በአንድ ላይ እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አብረው ተጉዘው ነበር። በ431 በኤፌሶን ጉባኤ በንስጥሮስ ምክንያት የንስጥሮሶውያን ኦርቶዶክስ ተመሠረተ ። በ451 በኬልቄዶን ጉባኤ በምስጢረ ሥጋዌ ላይ የምሥራቃውያን ኦርቶዶክስ ልዩነት ተፈጠረ። በዚህም ሮም እና ቁስጥንጥንያ (ምሥራቅ ኦርቶዶክስ) አንድ ላይ በመኾን ከእስክንደርያ መንበር ጋር ባለመግባባት ተከፈሉ። ሮምን የተከተሉት የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ሲኾኑ ፤ እስክንድርያን የተከተሉት በኋላ ዘመን ኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ ተብለው ተሰየሙ ። ንስጥሮስን የተከተሉ ንስጥሮሳውያን ኦርቶዶክስ ተብለው ተለዩ።

ኦሪዬንታል የተባለበት ምክንያት ሞኖፊሳይት ተብሎ የተሳሳተ አመለካከት የእስክንድርያን መንበር በሚከተሉ በፀምስቱ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ይነገር ስለነበር ያንን የተሳሳተ ቃል ለማረም ኦሪዬንታል የሚል ስያሜ ተሰጠ። ነገር ግን የኹለቱም ትርጉም ምሥራቅ ነው። ስሙም ኦርቶዶክስ ወይም ቀጥተኛ መንገድ ማለት ነው ። የንስጥሮስ ተከታዮች በሶርያ ውስጥ እና በኢራቅ ውስጥ ያሉት ኦርቶዶክሳውያን መለያ ኾናቸው።

ከአራት እስከ አምስት ሚልዮን የሚደርሱ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ እና የኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ የክርስቲያን እምነት ተከታዮች በአሜሪካ ሲኖሩ።[218] በዓለም ላይ 300 ሚሊዮን የኦርቶዶክስ አማኞች አሉ ተብሎ ይገመታል ። የኦርቶዶክስ እምነት ለብዙ አሜሪካውያን ነዋሪዎች እስከ አኹን ድረስ እንግዳ ነው።

[218] Jackie Staddon., *p.,*



### (፩) ግብፅ (ቅብጥ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

በዚያ ቀን በግብፅ ምድር መካከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ ፥ በዳርቻዋም ለእግዚአብሔር ዓምድ ይኾናል። ይህም ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር በግብፅ ምድር ምልክት እና ምስክር ይኾናል" (ኢሳ. 19፥19 – 21)።

በኢሳይያስ ትንቢት በተነገረው መሠረት የእስክንድርያ (ቅፕት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሰባ ኹለቱ አርድዕት አንዱ በኾነው በወንጌላዊው በቅዱስ ማርቆስ በመጀመሪያው ዘመን ተመሠረተች ። ቅዱስ ማርቆስ ከአይሁዳውያን ቤተሰቦች በሊቢያ ተወልዶ በኋላ ከቤተሰቦቹ ጋራ ወደ ፍልስጥኤም የኼዱ ናቸው። የቅዱስ ማርቆስ ቤት ጌታ ሐዋርያቱን የሚሰበስብበት ቤት ነበር። መንፈስ ቅዱስ ሲወርድም ሐዋርያት የተሰበሰቡበት በዚሁ በማርቆስ እናት ቤት ነው።

ቅዱስ ማርቆስ ወንጌልንም በጥንት ዘመን ታላቅ ዕውቅና በነበራት የእስክንድርያ ከተማ መንገድ ላይ አስተማረ፤ ጣዖታትን አጠፋ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ተስፋፋች። ቅዱስ ማርቆስ በምትኩ በመንበሩ የሾመው አናንያስን ነው። ይህች የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን፤ በእስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትከፍታ በማስተማር ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ያፈራች ነች። በዓባይ ወንዝ ዳርቻ በሚገኙ በረሀማ ቦታዎች አባ እንጦንስ ፣ አባ ፓኩሚስ ፣ አባ መቃርስ እና አሞንዮስ አማካኝነት የምንኩስና ኑሮ ተመሠረተ ። በዓለም ለሚገኙ ገዳማት ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጭምር ሳይቀር የምንኩስና ሕይወት መሪ ኾነች ። የወንጌል መልእክተኞቿን በዓለም ስታስፋፋ ኖራለች ። ለዘመናት በእስልምና እምነት እየተጠቃች ያለች ቤተ ክርስቲያን ነች ፤ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር የበላይ ጠባቂ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ ሹኑዳ ናቸው።

በአኹኑ ጊዜ በአሜሪካ ምድር በዋሽንግተን ዲሲ በካሊፎርኒያ ቤተ ክርስቲያኗን አሰማርታ ከፍተኛ አገልግሎች እየሰጠች ነው ። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በካሊፎርንያ ግዛት ውስጥ ይገኛል። በዚያም ቁጥሩ ወደ 10 ይደርሳል። በኒው ጀርሲ 9 ሲኖሩ ፤ በኒው ዮርክ ደግሞ 8 አሏቸው። በአስተዳደር መንግሥቱ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከተማ ውስጥ ያላቸው 4 አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ናቸው ። ባጠቃላይ በአሜሪካ ግዛቶች ወደ 96 የሚደርሱ አብያተ ክርስቲያኖች አሏቸው።

## (፪) ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

እነሆ ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧም ኹሉ የሰለጠነ አንድ ኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ኼደ። ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር (የሐ. ሥራ. 8፥26)።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዐረገ በዓመቱ በ34 ዓ. ም. ጥምቀተ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ጃንደረባው ይዞ ገባ ። ይህ የንግሥት ሕንደኬ በጅሮንድ (ጃንደረባ) ኢየሩሳሌም ደርሶ በኦሪቱ ልማድ ፋሲካን አክብሮ ወደ ጋዛ በምትወስደው መንገድ በኩል አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ፊልጶስን አግኝቶት ስለ ጌታ ወደዚኽ ዓለም መምጣት፣ ስለ ሞቱ ፣ ስለ ትንሣኤው፣ ስለ ሥርዓተ ጥምቀት አስረድቶ፤ በክርስቶስ እንዲያምን አድርጎ አጠመቀው ። ጃንደረባውም ከፊልጶስ የተማረውን ትምህርት ዜና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሰማ። በ330 ፍሬምናጦስ ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አትናትዮስ ዘንድ ጵጵስና ተሹሞ ተመለሰ። ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ምድር መስፋፋት ጀመረች።

በታሪክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከኢየሩሳሌም በስተቀር ወደሌላ አህጉራት ወይም በዓለም የተለያዩ ቦታዎች የወንጌል መልእክተኞች ልካ ወይም ሚስዮን ኾና አላቋቋመችም፣ ወይም አልተቋቋመችም ፤ ሕዝቡም በቅኝ አገዛዝ አልተያዘም ። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ በእስልምና ሃይማኖት አገሮች ተከባ የምትኖር አገር ነች። ብዙ ጊዜ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ለስብከት እየገቡ ወጥተዋል። ኢትዮጵያውያን ከወራሪ ጠላት ጋራ ሃይማኖታቸው እምነታቸው እንዳትጠፋ ሲከላከሉ ኖረዋል ። ይህም ሃይማኖታቸው አንድ አድርጓቸው የውጭን ጠላትን ድል አድርገዋል ። ሌላው በግብፃውያን ሥር ለዘመናት ስትተዳደር በመቆየቷ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሳትፈቅድ ከኢትዮጵያ ወጭ ሃይማኖትን ማስፋፋት አልቻለችም ነበር።

ጣሊያን በሞሶሊኒ መሪነት ኢትዮጵያን በወረረበትና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዝ አገር ለመኖር እንደገቡ መነኰሳት የመድኃኔ ዓለምን ታቦት ይዘው ለዐምስት ዓመት ኖሩ። ከ1935 - 1940 (1928 ዓ.



ም. እስከ 1933 ዓ.ም.) የእንግሊዝ አገር ኑሮ ፈጽመው ወደ አገራቸው በመመለስ ቤተ ክርስቲያንን እና አገርን ያለሙ ጀመር።

በመቀጠልም የንጉሡ ጥረት በ1951 ዓ. ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፩ኛ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ኾነው ተሾሙ። ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ያህል በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ስትተዳደር የኖረችው ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ፓትርያርኳን አስመረጠች ። እስከ ዛሬ ድረስ በፓትርያርክነት የተመረጡት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ቀጥሎ

(፪ኛ) ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ (1963 ዓ. ም.)
(፫ኛ) ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት (1968 ዓ. ም.)
(፬ኛ) ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ (1980 ዓ. ም.)
(፭ኛ) ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ (1984 ዓ. ም.) ናቸው።

የመጀመሪያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ወዲያው ፓትርያርክ በመኾናቸው ቤተ ክርስቲያኒቷ ወደውጭ አህጉራት ላሉት ምእመናን የስብከተ ወንጌል ሥራዋን ጀመረች።

### (ሀ) ዌስት ኢንዲያን እና አፍሪካን አሜሪካ

ኹለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳለቀ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ ጥቁር ሕዝቦች በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በመፈለግ አባል እንዲኾኑ ጠየቁ። በጥያቄው መሠረት ተፈቅዶላቸው ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያ ሐዋርያ እንዲላክላቸው አደረጉ ። በኢትዮጵያ መንግሥት እና ከቤተ ክህነት ጋራ ሲጻጻፉ የነበሩ በአሜሪካ ፤ በዌስት ኢንዲያን፤ በእንግሊዝ ያሉ ጥቁር ሕዝቦች ነበሩ። እነዚህ ሕዝቦች ኢትዮጵያ የጥቁር አገር ናት፤ እኛም ጥቁሮች ነን፤ በዚህ አገር ስንኖር ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ የለንም እዚህ ተጥለን ነው የምንኖረው። ስለዚህ የእኛ ባህልና እምነት (ሃይማኖት) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትገለገለው መኾን አለበት በማለት ብዙዎች በአሜሪካ የሚኖሩ የካሪቢያን ተወላጆችና አፍሪካን አሜሪካን ለእንቅስቃሴው የመጀመሪያ መሪ ኾኑ።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በተለይ የማርቆስ ጋርቬይ ትንቢታዊ ንግግር አገራችን የት ነው? ታሪካችን የት ነው? ንጉሣችን የት ነው ? ቋንቋችን የት ነው? ቤተ ክርስቲያናችንስ የት ነች? አምባሳደሮቻችን

የት ናቸው? በማለት ለሚያነሳቸው አንገብጋቢ ጥያቄ ምላሹ ኢትዮጵያ ነው የሚል ነበር ። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኒው ዮርክ እንዲመሠረት ሐሳብ ቢኖረውም በእሱ ጊዜ ሳይፈጸም በኹለተኛው ትውልድ ተፈጻሚነትን አገኘ።

በመጀመሪያ በ1952 በቲሪንዳድና ብሪትሽ ጋያና ቀጥሎ በ1959 በኒው ዮርክ ከዚያም በ1974 በኢንግላንድ ለንደን ከተማ አብያተ ክር ስቲያናት ለመጀመሪያ ጊዜ ተመሠረቱ። አገረ ስብከት የተቋቋመው ትሪ ንዳድ ነበር ፤ በኋላ ግን የአገረ ስብከቱን መንበር በአሜሪካ ኒው ዮርክ ከተማ ላይ አድርጉ ። አንዱ ምክንያትም ዐዲስ አብያተ ክርስ ቲያናት እየተስፋፉ ስለመጡ ነው። ሀገረ ስብከቱ በዚህ ኹኔታ ከቆየ በኋላ ዌስት ኢንዲያን ፣ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካን፣ ካናዳን፣ ኢንግሊ ዝን፣ ቤርሙዳን በማጠቃለል ለአገረ ጵጵስና በቅቶ ሊቀ ጳጳስ መሾም ተጀመረ።[219]

በ1952 የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በትሪኒዳድና ጋያና አገሮች ስትቋቋም የመጀመሪያው ሐዋርያ በመኾን ያተላኩት በቀድሞ ስማቸው መምህር ገብረ ኢየሱስ መሸሻ ጳጳስና ከተቀበሉ በኋላ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ይባሉ የነበሩት ናቸው ። ከእሳቸው በፊት ግን ከአፍሪካ የአይቬሪኮስት ተወላጅ የኾነ ሉቃስ የሚባል በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲ ያን ቄስ የኾነ ሰው፣ በቲሪኒዳድና በጋያና እኔ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ጳጳስ ነኝ ብሎ ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ ለመንቀሳቀስ ሞክሮ ነበር። ይህ ሰው በኋላ ከኢትዮጵያ እንዳልኾነ ተከሠተበት ። ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ተልከው ሲኼዱ አብረዋቸው ለአገልግሎት የተላኩት አቶ አበራ ጀምበሬ ነበሩ። እነሱም ሉቃስ ያቋቋመውን በኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐትና መልክ እንዲይዝ አደረጉ።

አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረር ሊቀ ጳጳስ እና እንደራሴ በነበሩ ጊዜ በ1959 ከሩስያ ጉብኝት በኋላ ወደ ኒው ዮርክ ተጓዙ ። በዚያም በኪ ራይ ቤት አርፈው ሰነበቱ ። በመቀጠልም ወደ ትሪኒዳድ ኼደው ዲያ ቆናት ሾሙ ። አባ ገብረ እግዚአብሔር ደጉ የተባሉ ከሳቸው ጋር አብረው የተጓዙትን በትሪኒዳድ እንዲያገለግሉ ትተዋቸው ተመለሱ። አባ ገብረ እግዚአብሔር ቆየት ብሎ የመኪና አደጋ ስለደረሰባቸው ወደ ኒው ዮርክ ተመለሱ። ጥቅምት 25 ቀን 1959 ዓ. ም. ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የመጀመሪያ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በኒው ዮርክ እንዲገዛ

[219] **Arch Bishop Yesehaq** *The Ethiopian O. Tewahedo church., p., 191*



አደረጉ ። ቦታውም ብሩክሊን 726 ጌት አቨንዩ ሲኾን ፤ የቅዱስ ሚካ ኤል ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይታወቅ የነበረውን ሕንጻ ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በማለት የኢትዮ ጵያ ይዞታ እንዲኾን ተደረገ ። በዚሁ ቀን 275 አፍሪካን አሜሪካን ይበልጡን የዌስት ኢንዲያን ተወላጅ የኾኑ ተጠምቁ። ቤተ ክርስቲያኑ ንም የሚያገለግሉ ሦስት ካህናት አባ ገብረ እግዚአብሔር ደጉ (አቡነ ሳሙኤል) አባ ገብረ ኢየሱስ መሸሻ (አቡነ አትናቴዎስ) እና አባ ገብረ ሥላሴ ነበሩ። በግሪክ የቲዮሎጂ ተማሪ የነበሩ በኋላ የሜሪላንድ ደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም አስተዳዳሪ መልአከ ገነት ልሳነውርቅ ውቡ አቡነ ቴዎፍሎስ በዚያው ቆይተው ዐማርኛ ለአሜሪካውያኑ እንዲያስ ተምሩ ፈቀዱላቸው።[220]

በ1962 አባ ላእከ ማርያም ማንደፍሮ በኋላ ብፁዕ አቡነ ይስ ሐቅ እዚህ አገር ደረሰው በትምህርት እና በቤተ ክርስቲያን ሥራ ተሠ ማርተው ቆዩ። በቅስና ከመምህር ገብረ ኢየሱስ (አቡነ አትናቴዎስ) ጋራ አገልግለዋል ። በኋላም አቡነ አትናቴዎስ በ1976 በዐረፍተ ሞት ሲለዩ በእርሳቸው እግር አባ ላእከ ማርያም ተተክተው አገልግሎት መስጠት ጀመሩ ። በእንግሊዝ ለንደንም አባ አረጋዊ በኋላ አቡነ ዮሐንስ በ1975 ለአገልግሎት እና ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ተላኩ።

ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ገና አባ ለእከ ማርያም ማንደፍሮ ተብ ለው በሚታወቁበት ዘመን የታወቀውን ዘፋኝ ቦቢ ማርሊንን "ብርሃነ ሥላሴ" ብለው አጥምቀዋል። በዚህ ዘመን 45 ሺ የሚደርስ ሕዝብ አብዛኛው ጥቁር ሲያጠምቁ 12 የጃማይካ ተወላጆችን አስተምረው ስለ ነበረ ዲቁናና ቅስና ተሹመው ከኢትዮጵያውያን ቀሳውስት ድጋፍ ተላቀው ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገዋል ። በአኹኑ ጊዜ እነዚህ የውጭ አገር ተወላጆች ካህናትና ዲያቆናት በካናዳ፣ በዌስት ኢንዲያ (ጃማይካ) እና በአሜሪካዲቁና እና ቅስና ተሹመው ራሳቸውን ችለው አገልግሎት ይሰጣሉ።

በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲቋቋም አማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን በቁጥር ጥቂት ነበሩ ። ከእነሱም ውስጥ ለትምህርት የተላኩና ትምህርታቸውን ሲጨርሱ መጽሐፎቻቸ ውን ጠቅልለው ወደ አገራቸው የሚመለሱ ነበሩ። የተቀሩትም የኢትዮ ጵያ ኤምባሲ ሠራተኞች ነበሩ።

[220] *ብርሃኑ ብሥራት "ንቃመተ አብርሃም መጽሔት" ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ላይ የተወሰደ። (2004)*

በካሊፎርኒያ ሎሳ አንጀለስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተው
የጻድቁ የአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ነው። የተመሠረተበት
ዓመት የካቲት 27 ቀን 1973 ነው ። የተመሠረተው ኢትዮጵያን በሚወ
ዱና በሚናፍቁ በአንቶኒ ሀሚልተን የሚመራ ቡድን አማካኝነት ነው።
አንቶኒ ሀሚልተን በኋላ ዐምደ ጽዮን በመባል ተጠምቆ ቄስ ኾኖ
ነበር ። ከእሱም ጋራ አያሌ ዲያቆናት ክህነት ተሰጥቷቸው ያገለግሉ
ነበር።

## (ለ) በኢትዮጵያ የለውጥ ዘመን

ለመውደድ ጊዜ አለው፤ ለመጥላትም ጊዜ አለው ፤
ለጦርነት ጊዜ አለው፤ ለሰላምም ጊዜ አለው።.(መጽ. መክ. 3)

በ1975 ዓለምን በመዛመት ላይ የነበረው የሶሻሊዝም እና የኮሚኒዝም
ሥርዓት ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ይህ የሶሻሊዝም ፍልስፍና እርስ በእርስ
አፋጀ። አድኃሪ የተባሉት የኢትዮጵያ መሪዎች ወደ ወኅኒ ቤት ተወ
ስደው ታሠሩ፤ ብዙዎችም ተረሸኑ። የቤተ ክርስቲያኒቷ የበላይ ጠባቂ
(Defender of the Faith) ይባሉ የነበሩት ባለሥልጣን ንጉሠ ነገሥት
ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ከዙፋናቸው አውረደው አሠሩዋቸው።
የንጉሡ ከቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂነት አከተመ ። ይህም ለዛ
ሬው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዘበራረቅ ማዕከላዊነት
ማጣት አንዱ ምክንያት ነው ። የንጉሡ ፊቃድ ተጨምሮበት የተመረ
ጡት ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም የደረሱበት ሳይታ
ወቅ ኖሮ በኋላ ዘመን የኹለቱም አፅማቸው ታስሶ እና ተለቅም ተቀ
በሩ ። በእዚህ የመከራ ዘመን ውስጥ ብዙዎች ሥርዓቱን እየጠሉት
እንዲሁም በሐሳብ አለመግባባት እየተፈጠረ በመፍለስ ከአገር ውጭ
የመሰደድ ጊዜና የጦርነት ጊዜ ሲካኼድ ቆየ። ይህ ችግር የሶሻሊዝም
ፍልስፍና በተግባር እንተረጒማለን ባሉት አገሮች ኹሉ እንዲህ ያለ
ትግል ተፈጽሟል። በዚህ የተነሳ ሃይማኖትን ፣ ባህልን ይዞ ከአገር
እየወጡ ወደ ሰው አገር መሰደድ ተለመደ።

በአሜሪካ በአብዛኛው የስደት ማረፊያ የነበሩት ቦታዎች ዋሽን
ግተን ዲ.ሲ፣ ኒው ዮርክ፣ ሎሳ አንጀለስ ፣ ሲያትል ፣ አትላንታ የመ
ሳሰሉት ቦታዎች ናቸው ። በዚህ አስቸጋሪ የስደት ዘመን ቤተ ክርስ
ቲያን በኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች ምእመናን ከአገር ውጭ በየቦታው
መስፋፋት ጀመረች ። ይህንን ተከትሎ ዲያቆናት ፣ ቀሳውስት እና



ጳጳሳት ከአገር መውጣት ጀመሩ። በዋሽንግተን ከተማ ውስጥ ዘወትር
ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋም የሚተጉ ካህናትና ምእመናን ተነሱ ።
ከነዚህም ውስጥ አቶ ከሣሊ፣ ሊቀ ማእምራን ዶክተር አማረ ካሣዬ፣
ርዕሰ ደብር አብርሃም ሀብተ ሥላሴ፣ መልአከ ኪዳን ታደሰ ሲሳይ፣
ሊቀ ትጉሃን ዲያቆን ፍቅሬ እንዲሁም ሌሎችም ካህናት እና ምእመ
ናን በኒውተን መንገድ ላይ በሚገኘው ትንሽ ክፍል ይዘው አገልግሎት
ይሰጡ ጀመር ። ከዚያ በመነሳት ዛሬ ርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም
ቅድስት ማርያም በመባል ተስፋፍታ ትገኛለች።

በመቀጠልም የርዕሰ አድባራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
(ካቴድራል) ተቋቋመ። ከዚያም አባ መልአኩ ጌታነህ (አኹን አቡነ
ፋኑኤል) ወንጌልን በማስተማር ቀስ እያሉ ዕድገት አሳይተው የደብረ
ምሕረት ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያንን መሠረቱ ። ከዚያም አባ
መዓዛ ቅዱሳን በየነ የቅዱስ ገብርኤልን አቋቋሙ፤ ከአገር የወጡ
ሊቀ ጳጳሳት ካህናት እና ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ማቋቋማቸውን
ቀጠሉ። እንዲህ እያለ በምሥራቅ፣ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ቤተ
ክርስቲያን በአሜሪካ ክፍለ አገር በሊቃነ ጳጳሳት እና በቆሞሳት እየተባ
ረከች መስፋፋት ጀመረች።

## (ሐ) ፬ኛ ፓትርያትክ እና ቅዱስ ሲኖዶስ በአሜሪካ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ 4ኛው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ
መርቆሬዮስ ናቸው። እሳቸው 3ኛው ፓትርያርክ በፁዕ ወቅዱስ አቡነ
ተክለ ሃይማኖት ሲያርፉ በደርግ ሶሻሊስት ዘመነ መንግሥት የተመ
ረጡ ናቸው።

የሶሻሊዝም የደርግ መንግሥት ሥልጣኑን ሲለቅ ሌላው ተቃ
ራኒው የሶሻሊዝም መንፈስ የሚከተለው መንግሥት ሥልጣን ተረከበ።
ፓትርያርኩ ከዚህ ከዐዲሱ የመንግሥት ባለሥልጣን ጋር መግባባት እን
ደማይችሉ ታወቀ ። የሶሻሊዝም የደርግ ሥልጣን ሲያከትም በጊዜው
ሥልጣን ይዘው የነበሩት የሕዝብ ክፍል (ሰቪሉ) ኹሉ እንደወረዱ፤
ሌላውን መንፈሳዊውን ማውረድ አይቻልም ነበር። ኾኖም ግን በውስጥ
አሠራር የማይመቻቸው ኾኖ ያገኙት 4ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ
ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ በሕመም
ሥልጣኑን ለመልቀቅ ተገድጃለሁ አሉ። ቢቆዩም ጥሩ አይኾንም እና
መንበራቸውን ለቀው በአሜሪካ ከሌሎች አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት ጋር

ተሰደዱ ። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ምእመናን ባሉበት ቦታ በመኖ ራቸው ቤተ ክርስቲያን ማቋቋም ፣ መባረክ ፣ ቅስና ዲቁና ሥልጣነ ክህነት በመስጠት ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ከሌሎች አባቶች ጋር በመ ኾን ቀጠሉበት። ኑሯቸውንም በአትላንታ ጆርጂያ አደረጉ።

በኢትዮጵያ በምትካቸው 5ኛው ፓትርያርክ ተመረጡ። የተመረ ጡት ፓትርያርክ ከቅዱስ ሲኖዶ ጋር በመኾን ሥራቸውን ቀጠሉ ። በአሜሪካ እና በአውሮፓ የተሰደዱትን ሊቃነ ጳጳሳት የጵጵስና የማዕ ረግ ስማቸው ተወስዶ ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸው በመኾኑ እና እነ ሱም ከድተው በመኼዳቸው ለእነሱ አይገባም በሚል ለሚሾሙት እጩ ጳጳሳት ተሰጠ፤ አሜሪካ ያሉት ሊቃነ ጳጳሳት የበለጠ ተከፉ።

ይህም በአሜሪካ ያለው ሲኖዶስ ማቋቋሙንና እውነተኞቹ እኛ ነን ማለትን ገፋበት ። የአሜሪካ ሲኖዶስ ለ23ኛ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ተሰብስበዋል ፤ ብዙ ጊዜ መግለጫ አወጥተዋል ፤ ግንቦት 15 ቀን 19 95 ዓ. ም. የወጣው መግለጫ ነጸብራቅ መጽሔት እንደሚያስረዳው እንዲኽ የሚል ነበር።

> በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ 15ኛ መደበኛ ጉባኤ በዋ ሽንግተን ዲሲ ርዕሰ አድባራት ደብረ ኀይል ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተደረገ ሲኾን የሲኖ ዶስ ስብሰባ ላይ የወጣው የአቋም መግለጫ ።
>
> ቅዱስ ሲኖዶስ በስደት አገር ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተበተኑትን ለማሰባሰብ የተለያዩትን አንድ ለማድረግ ሲጥር መቆየቱ በጉባኤው ተወስቷል። አኹንም ያሉትን የአን ድነት መሰናክሎች በማስወገድ አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት ጥላ ሥር የማሰባሰቡ ጥረት መቀጠል እንዳለበት ጉባኤው አምኖበታል። ስለዚኽ አብያተ ክርስቲያናትን በኅብረትና በሥር ዓት ለመምራት የምእመናንን አንድነት ለመጠበቅ ዓቢይ ጉባ ኤው ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የሚከተለውን ወስኗል።

1. የራዲዮ ፕሮግራም እንዲጀመር ። ስሙም የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአንድነት ድምጽ ሬድዮ ተብሎ እንዲጠራ፤
2. በቂና አሳማኝ ባልኾነ ምክንያት ከቅዱስ ሲኖዶሱ አመራር ውጪ ነን ለሚሉ አብያተ ክርስቲያናት የውይይት በር እንዲ ከፈት፤



3. ካህናት ጥሪ እንዲደረግላቸው፤
4. ካህናት ስለ አንድነት እና ስለፍቅር እንዲያስተምሩ፤
5. ሥርዐተ ቤተክርስቲያን እንዲከበር፤ ምስጢረ ጥምቀት ፣ ምስ ጢረ ንስሐኝ በተመለከ፤
6. የመጽሔት ስርጭትን በተመለከተ፤
7. በአገራችን በኢትዮጵያ ስለደረሰው የድርቅ አደጋ፤
8. የሰንበት ትምህርት ቤት አደረጃጀት፤

በማጠቃለያ በውጪ አገር የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን ከላይ የተዘረዘ ሩትን በማዕከላዊነት በይበልጥ ስለማጠናከር በአሜሪካ የኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ሰጠ።[221]

## (መ) ፭ኛ ፓትርያርክ እና ቅዱስ ሲኖዶስ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመት ኹለት ጊዜ እየተሰባሰበ የቤተ ክርስቲያኒቷን አንድነት የሚጠብቅ ሕግና ትእዛዝ የሚያወጣ አካል ነው።

የቤተ ክርስቲያኒቷ ሕግ ሳይጠበቅ በመቅረቱ ፓትርያርክ በሕ ይወት እያለ ፓትርያርክ፤ ሊቀ ጳጳስ በሕይወት እያለ በላዩ ላይ ሊቀ ጳጳስ መሾም፣ የጵጵስና ስም ነጥቆ ዐዲስ ለሚሾሙት ጳጳሳት ማውረስ የተጀመረበት ከአቡነ ተክለሃይማኖት ጊዜ ጀምሮ ነበር። ይህ ባህልም ቀጠለ ።

5ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀደም ሲል የሶ ሻሊዝም ሥርዓተ መንግሥት ደርግ 7 ዓመት እስር ከፈታቸው በኋላ ወደ አሜሪካ ገቡ። በአሜሪካ በሚኖሩበት ጊዜ በፕሪስተን ዩንቨርስቲ ተምረው ባችለር ኦፍ ዲቪኒቲ በሚባለው የውጭ ትምህርት ዶክትሬት አገኙ። በአሜሪካንም በሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን ሲያስተ ዳድሩ በቀድሞ ጊዜ ከነበረው ሲኖዶስ ላለመቀላቀል ፤ ገለልተኛ ቤተ ክርስቲያን ነች በማለት ይመሩ ነበር። በኋላ ዐዲሱ የፌደራል መንግ ሥት ኢሕአደግ አገሪቷን ለመምራት ሲዘጋጅ ፥ እሳቸውም አብረው ገቡ ። በዚያም ለፓትርያርክነት ምርጫ ቀርበው በመመረጥ የኢትዮ ጵያ 5ኛ ፓትርያርክ ኾኑ።

[221] *ነጸብራቅ፤ በስደት አገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሔት መስከረም 1996 ዓ. ም. ቁ.8 ገጽ7*

በሰሜን አሜሪካ አገረ ስብከት የሚመሩት ሊቃነ ጳጳሳት የፓትርያርክነቱ ሹመት በፍትሐ ነገሥቱ መሠረት ከቤተ ክርስቲያን ሕግ ውጭ ነው ብለው ተቃውሟቸውን አሰሙ ። ብፁዕ አቡነ ይሥሐቅን ጨምሮ ሌሎቹም ጳጳሳት ከሹመታቸው እና ከአገረ ስብከታቸው ተሻሩ ። አቡነ ይሥሐቅ ቀደም ብለው በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በመኾን ለዘመናት አገረ ስብከቱን ይዘው የቆዩ ነበሩ ። እሳቸውን በመሻር በምትካቸው ከ1984 ዓ. ም. (1992) ጀምሮ ብፁዕ አቡነ ማትያስ በምፍራው ተመድበው እንዲያገለግሉ ተደረገ። ብፁዕ አቡነ ማትያስ 10 ዓመት በስደት ከኖሩ በኋላ የደርግ መንግሥት ሥልጣን ሲለቅ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የገቡ እና ከዚያም በአቡነ ይሥሐቅ ቦታ ለአሜሪካ አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመኾን የተመደቡ ናቸው። -

ብፁዕ አቡነ ማትያስ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ፓትርያርክ እያለ ፓትርያርክ መሾም የለበትም የሚለውን ቢያምኑበትም ይህ ሥርዓት ለኹለት ጊዜ መሻሩን በዜና ልደታ ጋዜጣ ገልጸው ነበር። አንዱ በኹለተኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የተደረገው ሲኾን፤ ኹለተኛው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ላይ የተደረገው ትክክል አለመኾኑን ይናገራሉ ። ይህ የኹለት ፓትርያርኮች በአንድ ዘመን መገኘት በአሜሪካ ላለው ቤተ ክርስቲያን አገረ ስብከት መከፋፈል ከፍተኛ ችግር የፈጠረ መኾኑን ተናግረዋል።[222]

5ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በየጊዜው ባልደረቦቻቸው እና ወንድሞቻቸው አባቶች ጥለዋቸው ሸሹ። አብሮ አደጋቸው ብፁዕ አቡነ ይሥሐቅም ወደማይቀርበት ዓለም በሞት ተለዩ ። የብፁዕነታቸው መቃብርም ሲለፉበት በኖሩበት አገረ ስብከታቸው ጃማይካ ተፈጸመ።

## (ሠ) የካህናት ማኅበር በአሜሪካ

ግንቦት 15 ቀን 1994 ዓ. ም. በዋሽንግተን ዲሲ እና በአካባቢው የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበረ ካህናት ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጋር በመተባበር የተዘጋጀው በአሜሪካ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ ያወጣው የአቋም መግለጫ ፦

> የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደረው በአንድ ቅዱስ ሲኖዶስ መንበር ስለኾነ ሲኖዶስ መኖር የሚገባው በአገራችን በኢትዮጵያ በዐዲስ አበባ ነው። ኾኖም በአባ ጳውሎስ ትእዛዝና ፈቃድ የሚመራው ሲኖዶስ በዘር ፖሊሲ ላይ የተመሠረተ መንፈሳዊነት የጎደለው የተዛባ አስተዳደር መዋቅር ስለኾነ ፤ እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያንን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለማገልገል የሾማችሁ መንጋውን ኹሉ እና ራሳችኹን ጠብቁ ተብሎ (ሐዋ. ሥራ. 20፥28-29) የተገለጸውን አምላካዊ ትእዛዝ ስለአልተከተለ ይኽን አስተዳደር አጥብቀን እንቃወማለን። ከአገራችን ከኢትዮጵያ ከዐዲስ አበባ ከመንበረ ፓትርያርክ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ እና ሥርዓት ውጭ በቅዱስ ሲኖዶስ ስም የተቋቋመው የተመሠረተው ድርጅት የሚያደርገው ስብሰባና የሚወስነው ውሳኔ አግባብ ስላልኾነ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

በማለት ዐምስት ጊዜ የተሰደደውን ቅዱስ አትናቴዎስን እንዲሁም ሌሎችን ምሳሌ በማድረግ ሲኖዶስ በውጭ እንዳይመሠረት ምእመናኑም ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነት ይህንን አቋም እንዲከተሉ እና በአሜሪካ የተቋቋመው ሲኖዶስን በተመለከተ በኅብረት ከካህናት ማኅበር ጋር መሥራት እንዲቻል በጊዜው ኮሚቴ አቋቁሞ ነበር ። ኾኖም የተገኘ መፍትኼ አልነበረም።

በጉባኤው በተጨማሪም በማኅበሩ የወደፊት ኃላፊነት ተረክቢውን ወጣት እና በገዳመ ተክለሃይማኖት አማካኝነት (1ኛ) ኅብረት እንዲጠናከር (2ኛ) በራዲዮ፤ በጋዜጣ ሥርዓተ ትምህርት እንዲጠናከር የሚያጠና ግብረ ኃይል እንዲቋቋም። (3ኛ) አሜሪካ አገር ከተቋቋሙ ሌሎች ማኅበራት ጋራ አብሮ በትብብር እንዲሠራ ግንቦት 15 ቀን 1994 ዓ. ም. በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው የካህናት ጉባኤ ስብሰባ

[222] ዜና ልደታ ጋዜጣ *ቃለ መጠይቅ ጥር 1997 ዓ. ም. (June, 2005) ገጽ5*

የአቋም መግለጫ ወጣ።[223] ይህ በእንዲህ እንዳለ ዓመታት ከተቆጠረ በኋላ ማኅበሩ እየተዳከመ መጥቶ ወደ መፍረስ ደረሰ፤ አባላቱ በሐሳብ ልዩነት ተከፋፈሉ።

## (ረ) የሰላም መልእክተኞች በአሜሪካ

የሚያስታርቁ ብፁዐን ናቸው። (ማቴ. 5)

ለብዙ ጊዜ በየአቅጣጫው ያሉውን መለያየት አንድ ለማድረግ ሰላ ምን ለማምጣት የታሰበ እና የተሞከረበት ጊዜ ነበር ። ከኢትዮጵያ ካለው ሲኖዶስ ጋር ለማስታረቅ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እና አባ ኤልያስ በታኅሣሥ ወር 1999 ዓ. ም. በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጠው ወደ አሜሪካ ተላከው የእርቅ ጥሪ አቀረቡ።

ቀደም ሲል አሜሪካ ኑሯቸውን አድርገው የነበሩ ጥቂት መነኩሳት ለውጥ ለማምጣት ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በመግባታቸው እና በ5ኛ ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የጵጵስና ማዕረግ መቀበላቸው ቅሬታን አስከተለ። አሜሪካ ያሉት መነኩሳት ይህን የሹመት ዕድል ባለማግኘታቸው ቅርታ እንደሚኖር የታወቀ ነው ። በኢትዮጵያም የገቡት መነኩሳት ጳጳስና በመሾም በአሜሪካ የአገረ ስብከት መንበር (ቦታ) ተሰጥቷቸው ተላኩ። ይህም በዚያ ያሉትን የካህናት ማኅበር እና በ4ኛው ፓትርያርክ የሚመራው የውጪ ሲኖዶስ እንዲሁም ምእመናንን አላስደሰታቸውም ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለሰላም ጥሪ ለማቅረብ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ልዑካኑ ከብፁዕ አብነ ገብርኤል ጋር በመገናኘት ወደ አገር ውስጥ ወዳለው ሲኖዶስ እንዲመለሱ ጠየቋቸው አባቶችም ፈቃደኛ ኾነው ተመለሱ ። እነዚህ ልዑካን ከ4ኛው ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ጋር ተገናኝተው ተነጋግረዋል። በቦታ ርቀት ያላገኟቸውንም ሊቃነ ጳጳሳት በስልክ አነጋግረዋል ፤ ነገር ግን በቀላሉ ውጤት ሳይመጣ ቀረ ። በዚሁ ጊዜ በዋሽንግተን እና በአካባቢው ያሉትን አብያተ ክርስቲያናትና ካህናት ጋር ተገናኝተው ስለሰላሙ ጉዳይ ተነጋግረዋል።

በ4ኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የሚመራው የውጭ ሲኖዶስ ዘጠኝ መነኩሳትን መርጠው የጵጵስና ማዕረግ

[223] ማኅተም፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መጽሔት ቅጽ1 ቁ.1 ሰኔ 15 ቀን 1994 ዓ. ም. (ጁን 22, 2002 ዩናይትድ እስቴት) ገጽ 2



ሰጡአቸው ። ይህ ሹመት እንደገና ሌላ ቅሬታ አስከተለ፤ ሲኖዶሱም መግለጫ አወጣ። በመግለጫቸው የእውነተኛው ፓትርያርክ የሾሙት ሹመት መኾኑ ተገለጸ ። ምክንያቱንም ሲገለጽ አቡነ መርቆሬዎስ በፍትሐ ነገሥቱ (በሕጉ) መሠረት በሞት በተለዩ ፓትርያርክ ላይ የተሾሙ ፓትርያርክ ናቸውና ፓትርክናቸው ትክክል ነው የሚል ነበር።

ለሽምግልና የተላኩት ሊቃነ ጳጳሳት በማጠቃለያቸው አኹንም ለዕርቅ እና ለሰላም በሩ ክፍት ነው፤ የመከፋፈል አዝማሚያው እንዳ ይቀጥል ፤ በማለት የሰላም ልዑካኑ መሪ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ በዜና ማሠራጫዎች ጥር 8 ቀን 1999 ዓ.ም ንግግር አድርገው ነበር።

በአሜሪካ ሲኖዶሱ ላይ በኢትዮጵያ ያለው ሲኖዶስ የውግዘት ቃል አስቀድሞ አሰማ ፤ የአሜሪካኑም ምላሽ ሰጠ። ከምእመናን እና ከካህናት በኩል ከመገረም በስተቀር በመወጋገዛቸው በያሉበት አባቶቻችን ናቸው እያለ እያከበረ ከመኖር በስተቀር ተወግዘዋል ብሎ ውግዘቱን ደግፈናል ያለ የለም። በተፈጠረ አለመግባባት ከመንፈሳዊ አባቶቻችን የታየው የማይጠበቅ ድክመት ግን ኹሉንም ኢሳዝኗል። አንዳንድ ምእመናን ጳጳሳቱ ተወጋግዘዋል እና ከወዴት ኼደን እንቁረብ ሲሉ ጠቡ በሃይማኖት ሳይኾን በወንበር ስለኾነ ባላችሁበት ጽኑ በማለት ቀሳውስት ልጆቻቸውን ማረጋጋት ቀጠሉ ።

## (ሰ) ካህናት እና ምእመናን ጉባኤ በአሜሪካ

ከላይ የተገለጸው የካህናት ጉባኤ ሲፈርስ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እና ምእመናን ጉባኤ ተቋቋመ።

ዐዲስ ስለተሾሙት ጳጳሳትም መግለጫ አወጡ ። 16 አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት በመኾን በሹመቱ አለመስማማታቸውን እና በተገነጠለ ሲኖዶስ የሚሰጠው ሹመት ተገቢ እንዳይደለም በማለት ተቃውሞ አሰሙ ፤ ይህንንም በኢንተርኔት አሠራጩ።

ይህ የካህናትና ምእመናን ጉባኤ ለሦስተኛ ጊዜ ኅዳር 19 ቀን 2ሺ ዓ. ም በታምፓ ፍሎሪዳ ዐዲስ ዓለም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የኹለት ቀን ጉባኤ አድርጎ የአቋም መግለጫ አውጥቷል ። የመግለጫውም የመጨረሻ ማጠቃለያ ሐሳብ እንዲህ የሚል ነው።

በአኹኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኒቱ መንበር ላይ የሚገኙት ፓትርያርክም ቀደም ሲል በአሜሪካ አገር በነበሩበት ዘመን በቆዩባ

ቸው አብያተ ክርስቲያናት ሕዝቡን ሲያስተዳድሩ የነበሩበት በቦርድ ሕግ (BY-LAW) ነበር ። ስለዚህ ገለልተኛ የሚለው ቃል የተፈጠረው ከሥር ከመሠረቱ የነበረው የውጭ አገር የቤተክርስቲያኒቱ አመሠራረት እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ራሱን «ስደተኛ» ብሎ በሰየመውና በቤተ ክርስቲያናችን ሲኖዶስ መካከል በተነሳው የሥልጣን ውዝግብ ምክንያት ጎራ ለይቶ ለመቆም ወይም ራሱን እንደ ሦስተኛ አካል አድርጎ ለመኖር የታሰበ አለመኾኑን ሰሚም ተመልካችም ኹሉ ሊገነዘበው ይገባል ። እስከ አኹን ድረስ ይህ የገለልተኛነት ጠባይ ሥር ሊሰድ የቻለው ወደፊትም ይህን ስሜት አለዝቦ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የተሻለ ውጤት እንዳይመጣ እንቅፋት ይኾናል ተብሎ የሚያሰጋው የሚከተሉትን ምክንያቶች የያዘው ችግር ነው።

- ቀደም በነበሩት አባቶች ዘመን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በኢየሩሳሌም፤ በካሪቢያን አገሮች ፤ በአፍሪካ ደግሞ በሱዳን ፣ በጅቡቲ እና በኬንያ የጀመረችው ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ ፍሬ ያሳየና የሚመሰገን ኾኖ ሳለ ከቅርብ ዘመናት ወዲህ ግን ወደ ተለያዩ አገሮች የፈለሱትን ልጆቿን እየተከታተለች በማስተማር እምነቷን እና ሥርዓቷን ለማስጠበቅ አለመቻሏን፤
- የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ቃለ አዋዲ አኹን ባለበት ኹኔታ ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚኖሩ ቅርንጫፍ አብያተ ክርስቲያን ኹሉ ሊሠራ የማይችል መኾኑ እየታወቀ በውጭው ዓለም ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያን ከያገሩ መንግሥት፦ ሕግ እና መመሪያ ጋር የሚጣጣም ደንብ አለማዘጋጀቷ ፤
- የጵጵስና ማዕረግ እየተሰጣቸው ከሚላኩ አበው አንዳንዶቹ በተለያየ የዕውቀት ፣ የአመለካከት ፣ የአኗኗር ደረጃ በስፋት የሚኖረውን ሕዝብ ለማስተማር ፤ ለማስተባበር ወደ ሰላም መንገድ ለመምራት የሚኖራቸው ኹለንተናዊ ብቃቱና አባታዊ ምሳሌነታቸው አጠያያቂ መኾኑ። እነዚህንም የመሰሉት እንደኾኑ ጉባኤው ተነጋግሮበታል።

ይህ ከጉባኤው ቃል በጥቂቱ የተወሰደ ነው ። በማጠቃለያም የሰላም መልእክት አስተላልፈው ነበር።



ለኹሉም ነገር መሠረቱ ሰላም ነው። ሥራ ኹሉ ፍሬያማ የሚኾነው ሰላም ሲኖርበት ነው። ስለዚህ በአመራር ደረጃ ላይ የምንገኝ አበውና መላው ካህናት በሚያልፍ ሥልጣን ፈተና ከመሸነፍ ይልቅ በእግዚአብሔር መንገድ መሸነፉ ይበልጥ ስማችንን ስለሚያድሰው ሰላም ለኩልክሙ እያልን ለሌሎች የምናውጀውን የሰላም አዋጅ በተግባር እንድንተረጉመው ጉባኤው ይማጸናል።[224]

በማለት ጉባኤው ስብሰባውን አጠናቀቀ ።

## (ሸ) ቀናው መንገድ

ከላይ እንደተገለጸው የጉባኤውን የሰላም ጥሪ የሚደገፍ ነው ። ቤተ ክርስቲያኒቷ የአስተዳደር ችግር የደረሰባት መኾኑ የታወቀ ነው ። ቀደም ሲል ጀምሮ ለመለያየት ምክንያት የኾኑ ብዙ ነገሮች አሉ ፤ ነገር ግን ጥፋት በጥፋት ላይ በየጊዜው እየተጨመረ ዝም ማለት እንዲሁ ጥፋት እየበረታ ሲኼድ ጥፋቱን ችላ ብሎ ማለፍ ሊፈርስ የማይችል ባህል ኾኖ እያደገ ለትውልድ የሚተላለፍ በሽታ ይኾናል። ለዚህ መድኀኒቱ ነገሮችን በቀና መንገድ ፤ በትእግሥት እና በይቅርታ መፍታት ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብፁዐን አባቶች ዘንድ የመሠረተ እምነት (ዶክትሪን) ችግርና ልዩነት አልደረሰም። ስለዚህም ይህ የአስተዳደር የሥልጣን ችግር ጊዜ ኺደት እንደሚፈታ ጥርጥር የለውም።

በመሠረተ እምነት ችግር ያምልኮቱ ሥርዓት መሠረታዊ እምነት ተናውጦ ሲታይ የሚከሰተው መወጋገዝ፤ ለምሳሌ፦ አርዮስ ወልድ ፍጡር ስላለ በሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት አውግዘውታል፤ መቅደንዮስ መንፈስ ቅዱስ ሕፁጽ ስላለ በመቶ ሃምሳ ሊቃውንት ተወግዟል። እንዲሁም ንስጥሮስ ቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ አይደለችም በማለት ወላዲተ ሰብ ስላለ በኤፌሶን ተወግዟል።

በዚህ አይነት የሃይማኖት መዛባት ቢኾን ኹሉም ወደ ምርጫው በመኼድ ካህናት እና ምእመናን ሊከፋፈሉ ችግሩም ሊከፋ

[224] www.dskmariam.org

ይችል ነበር ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባቶች መወጋገዝ ግን በተፈጠረ ጊዜያዊ የሥልጣን ችግር ነው ።

ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራም፤ እንደሚባለው አኹን ለቀረው የዕድሜ ዘመን ያለፈውን መወጋገዝ፣ መወቃቀስ፣ በጽርፈት ቃል በመናገርም ቢኾን ፤ በጽሑፍ በመተቻቸትም ቢኾን … በመተው ለሰላም ልዑክ እንደነበሩት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እንዳቀረቡት መግለጫ ለወደፊቱ ዕርቁ እንዲቀጥል ቢደረግ መልካም ነው ።ማንም ወቃሽ ተወቃሽ ሳይኾን ቀናው መንገድ ለሰላም እጅን መዘርጋት ነው።

በአንድ ወቅት በአሜሪካ ሜሪ ላንድ የደብረ ገነት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መልአከ ገነት ልሳነወርቅ ውቡ የካህናት ማኅበር ጉባኤ ስብሰባ ላይ የተናገሩት ቃል እንዲህ የሚል ነበር።

> ዓለም ሰፊ ነው፤ ኹለቱ ፓትርያርኮቻችን ወንድሜ ወንድሜ ተባብለው ፍጽምት በኾነች ፍቅር እርስ በርሳቸው ሰላም ተባብለው፤ ተከባብረው ቢታረቁ እና አንተ አሜሪካንን እኔ ደግሞ ኢትዮጵያን ተባብለው ተማክረው ቢመሩን ጤና እናገኝ ነበር። ለዚህ ግን አልታደልንም ። ይህንንም ሳናይ ዘመናችን እያለፈ ነው በማለት ሀዘናቸውን ገልጸዋል።

በእርግጥም እኝህ አረጋዊ አባት እንደተናገሩት ቀናው መንገድ ሰላምን ማድረግ ነው። ዕድሜ ልክ ሲበጣበጡ ኖሮ ከማለፍ፤ ብጥብጡን ለትውልድ ከማስተላለፍ ሰላም ቢደረግ ለኹሉም መልካም ነው ። ይህም የሰላም መንገድን ማድረግ ዓለምን ከማስደነቁ ሌላ ለኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች፥ ለሕዝቦች ጭምር ታላቅ ደስታ ፣ እፎይታ እና ታሪክ ይኾናል ። ለተለያየው ኹለት ሲኖዶስ መፍትኼው ወኪል መላክ ሳይኾን የኹለቱ ፓትርያርኮች ፊት ለፊት ተገናኝቶ መነጋገር ነው ። የሚናፈቀው ኹለቱ የኢትዮጵያ ፓትርያርኮች የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ አባቶች 4ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ እና 5ኛ ፓርትያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሌሎቹንም ጨምሮ ሲተቃቀፉ ማየት ነው።

ተቀራርቦ መወያየት፤ ውሳኔ ሰጥቶ ውግዘቶችን ማንሳት ያስፈልጋል።[225] ነገር ግን ይኼ ሳይኾን በትንግሊኢ፣ በልደት፣ በአጽዋማት እና በዘመን መለወጫ በራዲዮና በቴሌቪዥን ከኹለቱም አቅጣጫ ቃለ

[225] ብርሃኑ አድማስ (ዲያቆን) ሐመር ተዋሕዶ ልዩ እትም «ሲኖዶስ እና የቤተ ክርስቲያን አንድነት» ሚያዚያ 1999 ዓ.ም. ገጽ 42-45። የዚህ ጸሑፍ አቅራቢ ይደግፈዋል።



ምዕዳን እና የሰላም ጥሪ ማስተላለፍ ፤ ሰሚውን ጥያቄ እንዲያነሳ ያደርገዋል ፤ ሲያደርገውም ኖሯል። ሰላም በተግባር መታየት፤ በሥራ መተርጎም አለበት። መጣላት እንዳለ ኹሉ መታረቅ መኖር አለበት፤ የጦርነት ታሪክ እንዳለ ኹሉ ፥ የሰላም ታሪክም ይኑር።

ሚያዚያ 24 እስከ 26 ቀን 1999 ዓ. ም. በሎሳ አንጀለስ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተካኼደው የ23ኛ መደበኛ ጉባኤ የአቋም መግለጫው ስድስተኛው ቁጥር ውሳኔ እንዲህ የሚል ነበር።

> በአገራችን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው ችግር የቤተ ክርስቲያናችንንም ኾነ የአገራችንን ህልውና የሚፈታተን እየኾነ መጥቷል። ይህ አደጋ ከምድራችን መገፈፍ የሚችለው በግራም በቀኝም ያለነው በሙሉ ወደ ብሔራዊ እርቅ እና ሰላም ስናመጣ ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወን ኹለንተናዊ ብሔራዊ ዕርቅ ደግሞ ያለፈውን ይቅር በማለት ፤ ልዩነትን በማቻቻል ለውይይት ወደ መቅረብን የሚያመጣ መኾን አለበት። ቅዱስ ሲኖዶስ ባገሪቱ የፖለቲካም ኾነ የማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ወገኖች ኹሉ ልዩነታቸውን በዕርቅ በሰላም እንዲፈቱ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም ራሱን ለዕርቅ እና ለሰላም እንዲያመቻች መንፈሳዊ ጥሪ ያቀርባል፤ በማለት በዜና ማሰራጫ ተሰራጭቶ ነበር።
>
> ትእዛዜ ይህች ናት ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለም ። እኔ ያዘዝኳችኹን ኹሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችኹ (ዮሐ. 15፥13)።

ወደፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አይነት ያለመግባባት እና ያለስምምነት በአሜሪካ ፣ በአውሮፖ እና በቀሩት ዓለማት እንዲሁም በኢትዮጵያ ምድር ልትጓዝ አይገባትም ። ሊቀ ጳጳሳት፣ ካህናት እና ምእመናን ከአገር ውስጥም ከውጭም ያሉት ችግሮችን በይቅርታ እና በሰላም መፍታት አለባቸው ። የጥላቻን እና የመለያየትን መልእክት ማስተላለፍ መቆም አለበት ። ለአንዲት ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲባል ፍቅር፣ አንድነት፣ ሰላም ጊዜው ሳያልፍ ለነዚህ ኹሉም እጁን ይዘርጋ እንላለን ።

ቀናንቱ ካለ የጳጳሳት መሾም ለወንጌል መስፋፋት ጠቀሜታን ይሰጣል እንጂ ምንም ጉዳት የለውም፤ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት እና መስፋፋት ጥሩ ነው ። መንፈሳዊ ያልኾነውን ስርብትና (ፖለቲካ)

ተወት አድርጎ በቀና መንገድ ማየት ጥሩ ነው። ለወደፊቱ የከፋ ነገር እንዳይታይ ከአኹኑ ይታሰብበት ። ችግሮች ተወግደው አንድ ቀን የሰላም ድምጽ እንደሚሰማ ትውልዱም ሰላምን እንደሚረከብ እምነታችን የጸና ነው።

በዚህ አጋጣሚ በአሜሪካ ምንም እንኳን ብዙ ፈተና በየአቅጣጫው ቢኖር ፍጹም እና ጠንካራ ካህናት እንዲሁም ምእመናን ያሉባት አገር ነች። ካህናቱም ኹኑ ምእመናኑ በተቻላቸው አቅም በትጋት ቤተ ክርስቲያንን አስፋፍተዋል። ለምእመናን ተስፋ እና መጽናኛ በመኾን ቤተ ክርስቲያን ስትስፋፋ እና ስትቋቋም እየተዘዋወሩ የሚባርኩትን ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳትን፤ ቆሞሳት፣ ቀሳውስት ኢ.ቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በየግዛቱ እየተዘዋወሩ ቅዳሴ በመቀደስ ፣ በማስተማር ፣ መዝሙር በመዘመር አገልግሎት የሚሰጡትን ምእመናን እና ወጣቶችን ፤ ለሰላም እና ለአንድነት የሚጥሩትን የሚደክሙትን ፤ በድርጅት ተደራጅተው አገርን ፣ ወገንን በተለያየ መልኩ የሚረዱት ኹሉ ምስጋና ይገባቸዋል።

## (ቀ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ.ክ. ቁጥር በአሜሪካ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አድባራት በየዘመኑ የተመሠረቱ ሲኾኑ ስማቸውን እና ያሉበትን ግዛት ከነከተማው ሠፍሯል።

| ግዛት | ዋና ከተማው |
|---|---|
| 1. ዋሽንግተን፤ | ዲ.ሲ. |
| ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም | |
| ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል | |
| ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል | |
| ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል እና መጥምቁ ዮሐንስ | |
| መካነ ሕይወት መድኃኔዓለም | |
| መካነ ብርሃን ዑራኤል ወሩፋኤል | |
| 2. አላባማ | ሞንትጎሞሪ |
| 3. አላስካ | ጁንኦ |
| 4. አሪዞና | ፊኒክስ |
| ቅድስት ሥላሴ፤ | |
| ቅድስት ማርያም (ልደታ ማርያም) | |
| ደብረ መዊዕ ቅዱስ እስጢፋኖስ (ፊኒክስ) | |



| ግዛት | ዋና ከተማው |
|---|---|
| 5. አርካንሳስ | ሊትል ሮክ |
| 6. ካሊፎርንያ | ሳክራሜንቶ |
| ጽዮን ቅድስት ማርያም ፣ (ሎስ ንጀለስ) | |
| ቅድስት ማርያም (ሎስ ንጀለስ) | |
| ቅድስት ማርያም ፣ (ቤቨርሊ ሂል) | |
| ቅድስት ሥላሴ (ሎስ ንጀለስ) | |
| ብሥራተ ገብርኤል፣ (ሳንዲያጎ) | |
| ቅዱስ ገብርኤል (ሳን ሆሴ) | |
| ደብረ ይባቤ ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል (ሳን ሆሴ) | |
| መካነ ሰላም መድኃኔዓለም (ቤርክሌይ) | |
| መድኃኔዓለም (ፍሬስኖ) | |
| ተክለሃይማኖት (ሎስ ንጀለስ) | |
| ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል (ኦክላንድ) | |
| 7. ኮሎራዶ | ዴንቨር |
| ዳግማዊት ጊሸን ቅድስት ማርያም (ዴንቨር) | |
| ኪዳነ ምሕረት (ዴንቨር) | |
| 8. ኮነክቲኬት | ሀርትፎርድ |
| 9. ደላዌር | ዶቨር |
| 10. ፍሎሪዳ | ታለሀሲ |
| አዳስ ዓለም ማርያም (ቴምፓ) | |
| ቅድስት ሥላሴ (ጃክሰንቪል) | |
| መካነ ፀሐይ መድኃኔዓለም (ሚያሚ) | |
| 11. ጆርጂያ | አትላንታ |
| ሰአሊተ ምሕረት ቅዱስት ማርያም (ዴኩቱር) | |
| ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም | |
| ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል | |
| መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል | |
| ብሥራተ ገብርኤል | |
| 12. ሀዋይ | ሆኖሉሉ |
| 13. ኢዳሆ | ቦይዚ |
| 14. ኢሊኖይስ | እስፕሪንግ ፊልድ |
| መድኃኔዓለም (ቺካጎ) | |
| ቅድስት ማርያም (ሴንት ልዊስ) | |
| 15. ኢንዲያና | ኢንዲያናፖሊስ |
| ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል | |
| 16. አዮዋ | ደሞኝ |
| 17. ካንሳስ | ቶፒካ |
| ደብረ ብርሃን ኪዳነምሕረት | |

| | |
|---|---|
| 18. ኬንታኪ | ፍራንክፈርት |
| 19. ሉዊዚያና | ባተንሩዥ |
| 20. ማሳቹሴትስ | ቦስተን |
| መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል | |
| መካነ ሕይወት ቅዱስ ሚካኤል | |
| ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም | |
| 21. ሜይን | ኦገስታ |
| 22. ሜሪ ላንድ | አናፖሊስ |
| ደብረ ገነት መድኃኔዓለም | |
| መካነ ሰላም ኢየሱስ (ቦልቲሞር) | |
| ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ (ቦልቲሞር) | |
| ደብረ ገሊላ አማኑኤል (ሲልቨር እስፐሪንግ) | |
| 23. ሚቺጋን | ላንሲንግ |
| ደብረ ገነት ተክለሃይማኖት | |
| አቡነ ተክለሃይማኖት | |
| 24. ሚኒሶታ | ሴንት ፖል |
| መድኃኒዓለም | |
| አቢሲኒያ ካቴድራል ቅዱስ ፊልጶስ (ዲትሮይት) | |
| 25. ሚሲሲፒ | ጃክሰን |
| 26. ሚዙሪ | ጀፈርሰን ሲቲ |
| ቅድስት ማርያም (ሴንት ሊዊስ) | |
| ቅዱስ ገብርኤል | |
| 27. ሞንታና | ሄሌና |
| 28. ነብራስካ | ሊንከን |
| 29. ኔቫዳ | ካርሶን ሲቲ |
| ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል (ላስ ቬጋስ) | |
| ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ወ ቅዱስ ሚካኤል (ላስ ቬጋስ) | |
| 30. ኒው ሀምፕሸር | ኮንኮርድ |
| 31. ኒው ጀርሲ | ተረንተን |
| ቅድስት ሥላሴ | |
| 32. ኒው ሜክሲኮ | ሳንታፌ |
| 33. ኒው ዮርክ | ባፋሎ |
| ጽዮን ማርያም (ኒው ዮርክ) | |
| ደብረ ሣህል በእታ ማርያም (ኒው ዮርክ) | |
| ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም (ማንሀታን) | |
| ኪዳነ ምሕረት (ሮቸስተር) | |
| መድኃኔዓለም (ባፋሎ) | |
| ቅድስት ሥላሴ (ብሮንክስ) | |



| | |
|---|---|
| 34. ኖርዝ ካሮላይና | ራሌየህ |
| መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ (ቻርለት) | |
| ደብረ ታቦር እግዚአብሔር አብ (ራሊ) | |
| 35. ኖርዝ ዳኮታ | ቢስማርክ |
| 36. ኦሃዮ | ኮሎምቦስ ሲንሲናቲ |
| መካነ ሰላም ኪዳነምሕረት (ሲንሲናቲ) | |
| መድኃኔዓለም (ኮሎምቦስ) | |
| ቅድስ ሥላሴ | |
| ቅዱስ ገብርኤል | |
| 37. ኦክላሆማ | ኦክላሆማ ሲቲ |
| 38. ኦሬጉን | ሳሌም |
| ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም | |
| 39. ፔንሲልቫንያ | ሀሪስበርግ |
| ቅዱስ ዐማኑኤል (ፊላዴልፍያ) | |
| 40. ሮዴ አይላንድ | ፕሮቪደንስ |
| 41. ሳውዝ ካሮላይና | ኮሎምቢያ |
| 42. ሳውዝ ዳኮታ | ፒየሬ |
| ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት (ሲዮክስ) | |
| 43. ቴነሲ | ናሽቪል |
| ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም | |
| 44. ቴክሳስ | ሂዩስተን |
| ርእሰ አድባራት ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል (ዳላስ) | |
| ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም (ዩስተን) | |
| ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም (ዳላስ) | |
| ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል (ሒውስተን I ማኖር) | |
| ተክለ ሃይማኖት (ሒውስተን) | |
| ኪዳነ ምሕረት (ዩስተን) | |
| ቀሴ ገዳም ገብርኤል (ዳላስ) | |
| ደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ (ዳላስ) | |
| 45. ዩታህ | ሶልት ሌክ ሲቲ |
| ደብረ ብርሃን አማኑኤል (ሶለት ሌክ ሲቲ) | |
| 46. ቬርሞንት | ሞንትፒሊር |

| | |
|---|---|
| 47. ቨርጂንያ | ሪችመንድ |
| ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት (አሌክሳንደርያ) | |
| ማሕደረ ስብሐት ልደታ (አሌክሳንደርያ) | |
| ፍኖተ ጽድቅ ቅዱስ ጊዮርጊስ (አሌክሳንደርያ) | |
| ደብረ መንክራት ልደታ (ሪችመንድ) | |
| ቅድስት ሥላሴ (አሌክሳንደርያ) | |
| መካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | |
| አቡነ አረጋዊ እና ገብረ ክርስቶስ (አሌክሳንደርያ) | |
| 48. ዋሽንግተን | አሉምፒያ |
| ቅዱስ ገብርኤል (ሲያትል) | |
| ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል (ሲያትል) | |
| 49. ዌስት ቨርጂንያ | ቻረልስ ታዎን |
| 50. ዊስኮንሰን | ማዲሰን |
| 51 ዋዮሚንግ | ቼየኒ |

## (፫) አርሜንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

የአርሜንያ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የተመሠረተውና የተሰበከው በሐዋርያው ታዴዎስ ነው (የሐ. 14፥22-24)። በተጨማሪ በሐዋርያው በርቶሎሜዎስ (ናትናኤል) (የሐ.1፥43-51) ተሰብኳል ። ከዚያም ቅዱስ ጎርጎሪዮስ ከሣቴ ብርሃን (Illuminator) ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን በ314 ጀምሮ በግልጽ የአርሜንያ ቤተ ክርስቲያን ክርስትና በማቋቋም ጭምር ሰበከተ ወንጌልን አስፋፋ።

የአርሜንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚመራው እና የሚተዳደረው በካቶሊኮሱ (የኹሉም የበላይ) በሊቀ ጳጳሱ ሥር ነው። ሊቀ ጳጳሱ ነዋሪነቱ በአርማንያ ነው ። በሊቀ ጳጳሱ በሥሩ የሚተዳደሩት አብያተ ክርስቲያናት ከአርሜንያ ውጭ ከ30 አገሮች በላይ ይደርሳሉ።

ከአርሜንያ በመጀመሪያ አሜሪካ ምድር የደረሱት ስደተኞች በ1834 ነበር። ዋናው የስደት ጉዟቸው ምክንያት የነበረው የከፍተኛ ትምህርት ለመማር በመፈለግ ነው ። በጣም ብዙ አርሜንያን በ1880 እና በ1890 ከዚያም እስከ በ1915 በኦቶማን ቱርክ ጦርነት ስቃይ ደርሶባቸው ሸሽተው በአሜሪካ የገቡት ቁጥር 200,000ሺ የሚደርስ በኒውዮርክ ከተማ፣ ዲትሮይት፣ ቦስተን፣ ፊላዳልፊያ ፣ ኒው ጀርሲና ካሊፎ



ርንያ በብዛት ይገኛሉ ። ዐዳዲስ የመጡ ስደተኞች በካንሳስ በሌሎችም ግዛቶች ይገኛሉ ።

በአሜሪካ ያለው የአርሜንያ አብያተ ክርስቲያናት በምእመናን ብዛት በሌሎቹ አኀቱ-ራት ካሉት ምእመናን ትልቁን ቦታ ይዞ ይገኛል። 750, 000 ሺ አሜሪካውያን የኾኑ የአርሜንያ ምእመናን አሉ። ይህች ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ አገር የምሥራቅ እና የምዕራብ በማለት ተከፍለው በኹለት አገረ ስብከት ተለይቷል ። በምሥራቁ አገረ ስብከት በኒው ሜክሲኮ የሚገኘው የበላይ አስተዳደር የሚመራው በሊቀ ጳጳስ ከሀጃግ በረሳሚአን ነው ። በምዕራቡ በሊቀ ጳጳስ ኾቨናን ዴርዴሪያን በካናዳ ኩይቤክ ግዛት ውስጥ በመኾን የሚመራ ነው። በካሊፎርንያ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። በካሊፎርኒያ ግዛት 180 የሚደርሱ የስበካ ክልል ይገኛሉ ። ነገር ግን በፖለቲካ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያኒቱ አማንያን ለኹለት ተከፍለዋል።

## (፬) ሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

የሶርያ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በቅዱስ ጴጥሮስ፤ ቀጥሎም በቅዱስ አግናጥዮስ ተመሠረተ ። ሶርያ ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ ክርስቲያኖች ከኢየሩሳሌም ተሰደው የሸሹባት፤ የአይሁዳውያን እና የአሕዛብ የመጀመሪያዋ የክርስትና እምነት አማንያን በአንድነት የተሰባሰቡባት፤ ዐርድዕት እና ደቀመዛሙርት በመጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን የተባሉበት ቦታ ነች። ይህ የኾነበት ዘመን በ36 ዓ. ም. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዐረገ በሦስትኛ ዓመት ነው (የሐ. ሥራ. 11፥26)።

የሶርያ ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶንን የኹለት ባሕርይ ውሳኔ የተቃወመውን የአንጾኪያው መንበረ ፓትርያርክ ተከታይ ናት። ይህች ቤተ ክርስቲያን ጌታ ወንጌልን የሰበከባት የሮማይስጥ (አርማይክ) ቋንቋ ባለቤት ነች ። በአኹኑ ጊዜ ይህ ቋንቋ የአዲስያ ቋንቋ ነው ። ዛሬ ይህ ቋንቋ በደቡብ ምሥራቅ ቱርክ ውስጥ ዑርፋ በምትባል ቦታ ይነገራል። ሶርያዊ ቅዱስ ኤፍሬም በ373 ዓ. ም. በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በዓለም የሚደነቀውን ምስጢረ ሥጋዌን የሚናገረውን የውዳሴ ማርያም ጸሎት የደረሰበት ቦታ ነች።

በአኹኑ ጊዜ ማዕከላዊ አስተዳደሩ ያለው በደማስቆ ነው ። የሚመራው በፓትርያርክ ቅዱስ ሞራን ሞር አግናጥዮስ ዘካካ ነው።

በዓለም በብዙ ቦታ ምእመናን ተሰራጭተዋል ለምሳሌ ሶርያ፣ ኢራቅ፣ ሊባኖስ፣ ፍልስጥኤም፣ ዮርዳኖስ ፣ ቱርክ፣ ሕንድ፣ ካናዳ፣ አውስትራልያ፣ ብራዚል፣ አውሮፓ፣ አሜሪካ ።

በአሜሪካ ይህች ቤተ ክርስቲያን በ1960 አካባቢ ተመሥርታ ዛሬ በአሜሪካ ግዛቶች በሰፋት አገልግሎት በመስጠት ላይ ትገኛለች።

## (፩) ሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

የሕንድ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የተሰበከው በሐዋርያው ቶማስ ነው። ሐዋርያው ቶማስ ስብከቱን የጀመረው በሕንድ ባሕር ጠረፍ አካባቢ ነው ። በዚህ ወቅት ብዙ ሕንዳውያን ወደ ክርስትና እምነት ተለወጡ። ጊዜውም 52 ዓ. ም. ነው። ከሐዋርያው ቶማስ ቀጥሎ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ተጀመረ።

በሕንድ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የምዕራባውያን ሰባኪዎች ብቅ አሉ ። ከዚያም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፖርቹጋል የካቶሊክ ሰባክያን ብቅ በማለት ለመስበክ ሞክረዋል።

የሕንድ ቅዱስ ቶማስ ቤተ ክርስቲያን ከሶርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የቀረበ ግንኙነት አላቸው ። በአኹኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኗ የበላይ ጠባቂ ፤ ፓትርያርክ ቅዱስ ሞራን ማር ባስልዮስ ማር ቶማ ኹለተኛ ማቴዎስ ይባላሉ ። ዛሬ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን 3 ሚሊዮን አባላት አሏት። በካናዳ፣ በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በእስያ፣ በአውስትራልያ፣ በአውሮፓ እንዲኹም በአሜሪካ ቤተ ክርስቲያኖች ተስፋፍተዋል።

በአሜሪካ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በኒው ዮርክ ከተማ የበላይ አስተዳደር በኾነው በሜትሮፖሊታን (ሊቀ ጳጳስ) ማር ባርናባስ ይመራል ። በዋሽንግተን ዲሲ የመንግሥት አስተዳደር ከተማ ውስጥ በ1982 የቅዱስ ጊዮርጊስ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ተመሠረተ ። ከዚያም በሌሎችም ግዛቶች (እስቴቶች) እየተስፋፋ ተመሥርተዋል ።



# ምዕራፍ ፲፩
# ምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

የኦርቶዶክስ ዓለም ለኹለት የተከፈለ ነው። አንዱ ከላይ የተገለጹት የኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ ሲባል ። ኹለተኛው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ በመባል ይታወቃል ። የኦርቶዶክስ እምነት ከካቶሊክ እምነት የሚለይበት በዶክትሪን (የእምነት መመሪያ) እና የአምልኮት ሥርዓት ልዩነት ጭምር ነው።

## (፩) ግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም ፤ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም እዳ አለብኝ (ሮሜ. 1፥14) ።

ቅዱስ ጳውሎስ የግሪክ ቋንቋ በሰፋት ይነገርበት በነበረ ዘመን ስብከቱን ለግሪክ ቋንቋ ተናጋሪዎች መስበክ ጀመረ ። ከዚያም ግሪካዊውን ጢሞቴዎስን ገርዞ አስከተለው (የሐ. ሥራ. 16፥1) በግሪክም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከግሪክ ውጭ በዓለም በብዙ ቦታ ተመሥርታለች።

በአሜሪካ በ1768 የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያኖች አማኝ የኾኑ ነጋዴዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በፍሎሪዳ ዳርቻ ይኖሩ ነበር ። ከዚያም በ1864 እነዚሁ ጥቂት የኾኑ ግሪካውያን ነጋዴዎች ተሰባስበው በኒው ኦርሊን ሉዊዝያና የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሠሩ። ከ1890 እስከ 1920 ባለው ጊዜ ውስጥ በግሪክ በነበረው ሕዝባዊ የእርስ በእርስ ጦርነት ከግሪክ ወደ አሜሪካ የሚገባው የስደተኛ ቁጥር እየበረከተ ኼደ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ በምዕራብና በምሥራቅ የአሜሪካ ክፍል ተስፋፋ።

በ1921 በኒው ዮርክ ከተማ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ አስተዳደር ተመሥርቶ እነዚህ እያደጉ እና እየተስፋፉ የመጡትን አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት አዋሕዶ ለማጠናከር እንቅስቃሴው ተጀመረ ። ዛሬ ድረስ የአገረ ስብከቱ ማዕከላዊ አስተዳደር እና የሊቀ ጳጳሱ መኖሪያ በኒው ዮርክ ቅድስት ሥላሴ ይገኛል።

የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ባለው ዘመን በአሜሪካ አገልግሎት የሚሰጥ የነበረው ለግሪካውያን ዜጎች ምእመናን ብቻ ሳይኾን ለሰርቢያን፣ ለሩስያን፣ ለአልባንያን፣ ለሩማንያ፣ ለቡልጋርያ ፣ ለዩክሬ

ይን እና ለሶርያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኖች ጭምር ነበር ። እነዚህ ሕዝቦች በቋንቋ በጎሳ ይለያዩ እንጂ በቲዮሎጂ (በዶክትሪን) ወይም በአምልኮት (በግልጋሎት) ልዩነት የላቸውም ። ዛሬ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ግሪክ ራይት የሚባል ስም ተሰጥቷቸው ለብቻቸው አገልግሎት እያገኙ ነው ። በአኹኑ ጊዜ በአሜሪካ በአብዛኛው የግሪክ አብያቱ ክርስቲያናት አገልግሎት የሚሰጠው በግሪክኛ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ነው።

በአሜሪካ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ካቴድራሎች"እና አብያተ ክርስቲያናት በግዛቶች፤ በትላልቅ ከተሞች፤ በአነስተኛ ከተሞች እና መንደሮች ተስፋፍተው ይገኛሉ ። በአጠቃላይ በአሜሪካ የሚገኘው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኹለት ሚሊዮን የሚደርስ ምእመናን አሏት። እንደዚሁም ደግሞ 21 ገዳማት ቢኖሩዋት፤ ዋናውና ትልቁ ገዳም በአሪዞና ግዛት በፍሎሬንስ የሚገኘው የቅዱስ እንጦንስ ገዳም ነው።

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናትን ማሠልጠኛ ኮሌጆች በማሣቹሴትስ ፤ በብሩክሊን ከተሞች ተቋቁመው ብዙ ካህናትን በማስመረቅ ላይ ይገኛሉ።

## (፪) የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

አሜሪካ በሩስያውያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከተያዘች ብዙ ዘመን አስቆጥራለች ። በመጀመሪያ ስምንት መነኩሳት ኾነው በ1794 በአላስካ ኮዲያክ ደሴት ገብተው የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን እና ገዳም መሠረቱ ። ከዚያም የሰደተኛው ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ ወደ ካሊፎርኒያ ግዛት ሳንፍራንሲስኮ ከተማ በመኼድ ቤተ ክርስተያን ማቋቋሙን ተያያዙት።

በምሥራቁ የአሜሪካ ክፍል በኒው ዮርክ በ1902 ጀምሮ ብዛት ያላቸው የሩስያ ዜጎች ገቡ። የሞስኮው ፓትርያርክ አላስካ የነበረውን የአስተዳደሩን ቦታ ወደ ኒው ዮርክ አዞሩት ። በኒው ዮርክም የቅዱስ ኒኮላስ የካቴድራል ሕንጻ ቆነጸ ። ከዚያም በአሜሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ጳጳስ በ1905 ተሾመ ። እንዲሁም በኒው ዮርክ የቅዱስ ብላድሚር የነገረ መለኮት የካህናት ማሠልጠኛ ኮሌጅ ተቋቋመ። በኮሌጁ ብዙ ኦርቶዶክሳውያን ካህናት በነገረ መለኮት ትምህርት እና በተለያየ ሙያ ለዘመናት ሲመረቁበት ኖረዋል ።



በ1917 እስከ 1943 ሩስያ ውስጥ በነበረው የቦልሸቪክ ፓርቲ የሶሻሊዝም እንቅስቃሴ የሩስያን ቤተ ክርስቲያን እንዳትስፋፋና ወንጌል እንዳይሰበክ አደረገ ። በዚህ የተነሳ ብዙ የሩስያ ተወላጆች ወደ አሜሪካ ይሰደዱ ጀመር ። ይህ የሶሻሊዚም ሥርዓት በኦርቶዶክስ ላይ በሚያደርሰው ጥላቻ የተነሳ በ1920 የሩስያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ቲኮ የተባሉት ከሩስያ ውጭ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ ትተዳደር በማለት አዘዙ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከዋናዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት ተቋረጠ ። የራሽያ የሶሻሊስት መንግሥት ፓትርያርክ የኾኑት ቲኮ የተባሉት ታሠሩ ። በአሜሪካ በየግዛቱ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ያስማዕከላዊው አስተዳደር ሥልጣን ተመሠረተ።

በ1880 እስከ 1920 ከላይ እንደተገለጸው የአርሜንያ እና የዩክሬይን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በአሜሪካ በሰሜኑ ክፍል እና በደቡቡ ክፍል ተሰደው ተስፋፉ። በዚህ ዘመን ውስጥ ከበፊቱ የበለጠ ከፍተኛ የስደተኛ ቁጥር ዕድገት የታየበት ጊዜ ነበር።

ቀደም ባሉት ዘመናት የራሳቸውን ሥርዓት አኗኗር በሚመሩበት ጊዜ የአሜሪካንን ባህል ስላልተከተሉ በአሜሪካውያን ዘንድ ጥላቻ እና ጥርጣሬን አሳድሮባቸው ነበር ። ይህ አይነቱ ጥላቻ በሌሎችም ቀደም ብለው በተሰደዱት በአየርላንድ ካቶሊክ እና በጀርመን እናባፕቲስት ይታየ እንደነበረው ነው ። በኋላ ግን ቀስ እየተባለ ልጆቻቸው በአሜሪካ የሕዝብ ትምህርት ቤት ሲገቡ የእንግሊዘኛ ቋንቋውን ሲናገሩ የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስም በመለወጥ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ የሚል ስያሜ ሰጥተው ይኖሩም ነበር ። ወደ እናት አገር ወደኋላ መመልከት ቀርቶ አሜሪካንን ቤቴ ማለት ቀጠለ።

ከእናት ቤተ ክርስቲያን የተለዩት እነዚሁ የሩስያ አብያተ ክርስቲያናት በ1960 እንደገና ለመዋሐድ ሞክረው ነበር።

በቅርቡ የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በአሜሪካ ይመሩ የነበሩት ሜትሮፖሊታን ቴዎዶስዮስ ነበሩ። እኝህ ሰው በ1977 እስከ 2002 አስተዳደር ላይ ተቀምጠው ነበር። ሜትሮፖሊታን ቴዎዶስዮስ ከልጅነታቸው ጀምሮ የኖሩት በአሜሪካ ሲኾን የተማሩት እና ድግሪያቸውን ያገኙት ዋሽንግተን እና ጄፈርሰን ኮሌጅ ነው ። በመጀመሪያ ሥልጣነ ክህነት ከተቀበሉ በኋላ የአላስካ አገረ ስብከት ጳጳስ ኾነው እንዲሠሩ ተደረገ።

በአሜሪካ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያኗ በራሷ እንድትተዳደርና ነጻ እንድትኾን በማድረግ ለወጡት ። ይህም ነጻ የመ

ኹን ስም ኦውቶሲፍሎስ (AUTOCEPHALOUS) ይባላል።[226] በአኹኑ ጊዜ የራሽያ ቤተ ክርስቲያን በ12 አገረ ስብከት በአሜሪካ ተከፍላ ትገኛለች። በየግዛቱ ካቴድራሎችና አብያተ ክርስቲያናት ተስፋፍተዋል። አማንያኑም ወደ ኹለት ሚልዮን በላይ ይጠጋል ተብሎ ይገመታል።

በኦርቶዶክስ የክርስትና እምነት 7ቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀት፣ ቊርባን፣ ንስሐ፣ሜሮን፣ ክህነት ፣ ተክሊል እና የቀንዲል ሥርዓት ይፈጸማል። ዋናው መሠረተ እምነቱ (ደግሞ) ዐምስቱ አዕማደ ምስጢር፤ ምስጢረ ሥላሴ ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ምስጢረ ጥምቀት ፣ ምስጢረ ቊርባን እና ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ላይ የተመሠረተ ነው።

ከነዚህ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን ያለቤተ ክርስቲያን ታሪክ በቂ ስለማይኾን የቅዱሳን ገድል (ታሪክ) ፣ ጻድቃን ፣ ሰማዕታት እና መላእክት አማላጅነታቸው የሚታመን ነው።[227]

# ምዕራፍ ፲፩
# ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

ከ451 ጀምሮ የሮም መንበርና የቈስጥንጥንያው (የግሪክ) መንበር አንድ ላይ ኦርቶዶክስ በመባል ተጉዘው ነበር ። በ700 ጀምሮ እስከ 1054 ድረስ በማዕረግና በወንበር ሥልጣን እንዲኹ በምስጢረ ሥላሴ ሥርጸት ጠብ ተፈጠረ። ካቶሊክ የኒቅያ ውሳኔ የነበረውን መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሠርጻል የሚለውን ከአብም ከወልድም ይሠርጻል (ይወጣል) በማለታቸው የመለያየት አንዱ ምክንያት ኾነ።

ቈስጥንጥንያ መንበር የግሪክ ቋንቋ ስለሚነገርባት ሐዲስ ኪዳንም በግሪክ የተጻፈ ስለኾነ መንበሩ እዚህ ይኹን አሉ ። የሮም መንበር የጴጥሮስ መንበር ስለኾነ አመራሩ ከዚህ መውጣት አለበት ሲል አለመግባባት ተፈጠረ። የቀድሞው ስም የሮማ ኦርቶዶክስ ነበር። ካቶሊክ ስሙ የመጣው ከግሪክ ቅጽል ካቶሊኮስ በላቲን ካቶሊክ ከሚለው ነው። ይህም ማለት "አጠቃላይ" ኹሉንም በበላይነት የሚመራ (Universal) ብለው መጥራት ጀመሩ። የሮሙ መንበር ከቈስጥንጥንያ የጵጵስና መንበር ተጣልተው ተለያዩ ። ካቶሊካውያኑ የበላይ የሸቲ

---

[226] Autocephalous, Self–governing; used in reference to Orthodox Churches in different nations.

[227] ሰፋ ያለ የነገረ መለኮት ትንታኔ እና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በ "ፍኖተ ኦርቶዶክስ ዘተዋሕዶ " መጽሐፍ ተከትሎ በሚቀጥለው ይቀርባል።



ካን መንበር መኾን አለበት አሉ። ፖፕ ማለት በጣሊያን ቋንቋ አባባ ማለት ስለኾነ የበላይ ጠባቂ በክርስቶስ ቦታ ያለ ነው በማለት ወሰኑ። ይህም አንዱ ለቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ምክንያት የኾነ ነው።

## (ሀ) የካቶሊክ እምነት በአሜሪካ

በአሜሪካ የካቶሊክ እምነት ከቀድሞ ጊዜ ጀምሮ የነበረው ችግር የቋንቋ ልዩነት ነው ። በአንድ ጥላ ሥር መሰባሰቡ አብሮ መጸለዩ ስለ ካቶሊክ ሃይማኖት ጠለቅ ብሎ ለመነጋገር የቋንቋ ልዩነት አያግባባቸውም ነበር። ሲለዚህ ካቶሊክ መብት እና ፈቃድ (ካቶሊክ ራይት) በማለት ለያዩት።

ዛሬ ካቶሊክ ራይት በማለት ወደ 22 የሚደርሱ የምሥራቅ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት አሉ ። እነዚህ ኹሉ አሜሪካ ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዷ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት። "ካቶሊክ ራይት" የሚለው ስም ተሰጥቷታል። ይህም ማለት በራሷ የአገር ባህል እንድትጠቀም የተሰጠ መብት ነው ። ይህቺ የኢትዮጵያ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ በዋሽንግተን ከተማም ተቋቁማለች።

ሌሎችም በተሰጠው መብት መሠረት ፖላንድ ዜጋ የኾነ (የፖላንድ ናሽናል) ካቶሊክ ቄስ እንዲያገባ ተፈቅዶለት ሚስት አግብቶ የሚቀድስም አለ ። የፖላንድ ካቶሊክ ከቀድሞ ጀምሮ በአሜሪካ በጣም ተስፋፍተው ከሚገኙት አንዱ ቡድን ነው። በአኹኑ ጊዜ ግን በአንዳንድ ቦታዎች የምእመናን ቊጥራቸው እየቀነሰ ይገኛል። ይህም የኾነበት ምክንያት ትውልዱ አሜሪካዊ እየኾነ ባህሉ እየተለወጠ በመኼዱ ነው።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ ውስጥ ከባፕቲስት ፕሮቴስታንት ቀጥሎ በኹለተኛነት ደረጃ የሚመራው ነው ። በሰሜኑ መካከለኛ ምሥራቅ ብዙ ተከታዮች አሏት፤ ከአውሮፓ ተሰደው በብዛት የገቡበትም በ19ኛውና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ነው። በ1995 እንደተጠናው ባጠቃላይ ከ60 ሚልዮን የሚደርሱ ካቶሊክ የእምነቱ ተከታዮች ሲኖሩ ፤ 20,000 ሺ አብያተ ክርስቲያናት በ50ው ግዛቶች አሏቸው። ሜሪ ላንድ በታሪክ በሰሜን ምሥራቁ የአሜሪካ ክፍል የመጀመሪያ የካቶሊክ አገር ናት። በዚህች ግዛት የመጀመሪያው ጳጳስ ጆን ካሮል በአሜሪካ የካቶሊክ ሃይማኖት ማዕከላዊ (Headquarter) የአስተዳደር ቦታ የመሠረተ ነው ። ይህ የማዕከላዊነት ቦታ የተመሠረተበት ጊዜም በ1790 ሲኾን አብዛኛዎቹ የነበሩት አየርላንዶች፣ ፖላን

ዶች ፣ ጣሊያኖች፣ ጀርመኖች እና እንግሊዞች ነበሩ። በይበልጥ ማሣቹሰትስ እና ሮዴ አይላንድ ብዛት ያላቸው የካቶሊክ አማንያን ይኖራሉ። የአየርላንድ ካቶሊኮች በመጀመሪያ በስደት የገቡበት ቦታ በታላላቅ ከተሞች ውስጥ ነው። በተለይ በኒው ዮርክ ግዛት እና በኒው ዮርክ ከተማ በብዛት ይገኛሉ።

ካቶሊኮች የቅዱስ ፓትሪክን ቀን በየዓመቱ መጋቢት 17 ቀን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አማንያን በመሰባሰብ ያከብሩታል ። በተለይም በኒው ዮርክ ከተማ የአየርላንድን ባንዲራና የአሜሪካንን ባንዲራ በአንድነት በመያዝ ተሰልፈው እየዘመሩ በጐዳና ላይ ያልፋሉ ። ይህ ቅዱስ ፓትሪክ የተባለ ሰው በ432 እንግሊዛዊ ክርስቲያን የነበረ ሲኾን ከእንግሊዝ ተጉዞ ወደ አየርላንድ በመኼድ ክርስትናን ለአይሪሾች የሰበከ ስለኾነ ቅዱስ እና ታላቅ ሰው ነው በማለት ያከብሩለታል።[228] ከዚህ በተጨማሪ አየርላንድ በእባብ የተሞላች አገር ነበረች፤ ቅዱስ ፓትሪክ እባቡን ከደሴቲቱ ለቆ እንዲወጣ ባዘዘው መሠረት ስለወጣ ይህንን ተአምር አድርጓል በማለት ያከብሩታል ።

በአሜሪካ የካቶሊክ የመጀመሪያው ጳጳስ ጆን ካሮል በ1791 ጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲን መሠረቱ ። እንደገና ማውንት ሴንት ሜሪ ኮሌጅ እና ሴንት ሜሪ ሴሚናሪ በ1880 መሠረቱ ። ኹሉም የተመሠረቱት በሜሪላንድ ግዛት ነው ። በአኹኑ ጊዜ የሮማ ካቶሊክ የአስተዳደር ቦታ እና የጳጳሱ መኖሪያ እንዲኹም ካቴድራሉ የሚገኘው በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ነው።

ከ1990 ጀምሮ እስከ 2000 ድረስ ወደ 35 ሚሊዮን የሚደርሱ የእስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከትውልድ አገራቸው ከደቡብ አሜሪካ እና ከሜክሲኮ እየተሰደዱ አሜሪካ በብዛት ገቡ ። እነዚህ ስደተኞች በአኹኑ ወቅት ከእንግሊዘኛው ተናጋሪ ይልቅ የእስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪው የእምነቱ ተከታዮች 40 በመቶ ጨምሮ ይታያል ። እነዚህም ዜጎች አብዛኛዎቹ በቋሚነት በየሳምንቱ ይከታተላሉ። በአሜሪካ የካቶሊክ ምእመናን ልጆቻቸው ጠንካራ እማኝ እንዲኾኑ በካቶሊክ ትምህርት ቤት እንዲማሩ ያደርጓቸዋል ። በ1999 በአሜሪካ ግዛት (እስቴት) 6,721 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 2 ሚልዮን ተማሪዎች ነበሩ። የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች 1,300 ሲኖሩ በዚህም 600,000 ሺ

[228] Shamrock (♣) = St. Patrick is said to have used one to illustrate the doctrine of the Holy Trinity, and it was made the national badge of Irish people wear shamrocks on St. Patrick's Day, 17 March.



ተማሪዎች ነበሩ ። ይህ የካቶሊክ የትምህርት አሰጣጥ በጣም የተመረጠና የተሻሻለ ስለኾነ ብዙዎች ወላጆች ልጆቻቸው በዚያ እንዲማሩ ያደርጋሉ። ዩኒቨርሲቲያቸውም በየቦታው በብዛት ይገኛሉ። ብዙዎቹም የሚመሩት በመነኩሳቶቻቸው በቀሳውስት፣ በጀስዊት፣ በፍራንሲስካን፣ በዶሚኒካን እንዲኹም በካረሜላይት መነኩሳት ነው ። እነዚህ መነኩሳት በቫቲካን ቁጥጥር ሥር አይደሉም።

በአሜሪካ በመቶዎች የሚቆጠሩ የካቶሊክ ሆስፒታሎች በየግዛቱ ተሠርተዋል። በኒው ዮርክ ብቻ 38 ሆስፒታሎች አሉ። እንዲሁም የርዳታ ክፍል ድሀን መረዳት እና በተፈጥሮ አደጋ ለሚቸገሩት፤ ለስደተኛ አፋጣኝ ዕርዳታ ያደርጋሉ።

በአኹኑ ዘመን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ብዙ ፈተናዎች እየገጠሟት ነው። ምእመናኖቹ ለኹለት ተከፍለው ሊበራል እና ኮንሰርቫቲቭ በመባል ይጠራሉ ። ኮንሰርቫቲቭ የሚባለው ከዋናው ክፍል ከቫቲካን ያለው ነው። ይህም የወሊድ ቁጥጥርን ፣ በማሕጸን ያለ ፅንስ ማስወረድን፣ የሴት ቅስናን የሚቃወም ክፍል ነው። ይህን የሚነቅፉት ደግሞ ሊበራል ይባላሉ በዚህ የተነሳ አልተግባቡም።[229]

የካቶሊክ ቀሳውስት ከ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ትዳር ሳይዙ ሳያገቡ በምንኩስና እንዲቀድሱ (ሰለበሲ) ተደረገ ። ዛሬ ለካቶሊክ እምነት ከፍተኛ ውድቀት የኾነው ቀሳውስቶች ቃል ኪዳናቸውን በመጣስ በዝሙት ሕጻናትን በማባለግ (Pedophile) ክስ እየተከሰሱ ፍርድ ቤት መቅረባቸው ነው። በዜና ማሠራጫዎች በሚቀርበው የክስ አይነት አማንያን ኹሉ እያሳፈረ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጓዘው ምእመን በጣም እየቀነሰ ነው ። የገቢም ክስረት አድርሷል ። ስለዚህም በአሜሪካ የላቲን አሜሪካ ዜጎች አማንያን ብቻ በዝተው ሲታዩ እንግሊዘኛ ተናጋሪው ቀንሶ ይታያል። ከብዙ በጥቂቱ በአሜሪካ ያለው የካቶሊክ እምነት ለአሜሪካ የኑሮ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የካቶሊክ ፖፕ ጆን ፖል 4ኛ በ84 ዓመታቸው 2005 ዐርፈው በምትካቸው ጀርመናዊው ቤነዲክት 16ኛ ተሾሙ ። ጀርመናዊው ፖፕ ቤነዲክት ሚያዚያ 8 ቀን 2008 አሜሪካንን ጎበኙ። በዚህም ጊዜ ዋሽንግተንን ከተማን ፣ ቦልቲሞርን እና ኒው ዮርክን ጎብኝተዋል።

[229] David Mauk and John Oakland *American Civilization an introduction , p. 63,-85, 368*

# ምዕራፍ ፲፯

## ፕሮቴስታንት 1517

ፕሮቴስታንት ኮለምቦስ አሜሪካንን ካገኘ በኋላ በ1500 ጀምሮ የተመሠረተ ነው። የፕሮቴስታንት መሥራቾቹን በጥቂቱ በመጀመሪያው ክፍል ተገልጿል።


ፕሮቴስታንት - የካቶሊክ እምነት መሻሻል አለበት ብሎ በተነሳው በሉትር መክንያት በ1529 አካባቢ በካቶሊካውያን የተሰየመ ነው። ፕሮቴስታንት ማለት በላቲትን ቋንቋ ተቃዋሚ፤ በግሪክኛ ሰይጣን፤ በዕብራይስጥ ደግሞ ዲያብሎስ የእግዚአብሔር ተጻራሪ ማለት ነው። የተሰባሰቡ የሉተር ተከታዮችና የጀርመን ግዛት ልዑላን የአገሪቱ ሃይማኖት ካቶሊክ ወይስ ፕሮቴስታንት ሲባሉ ሉተርን ለመደገፍ የግዛታችን እምነት የሉተር ነው ብለው አወጁ። ካቶሊኮቹም ፕሮቴስታንት ናችሁ አሏቸው ። ዛሬ ኹሉም ይህንን ስም በማወቅም ይኹን ባለማወቅ የጋራ መጠሪያው ኾኗል።

ቀደም ሲል ጀምሮ የሉተር እና የካልቪን ተከታዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መሰላቸው የመተርጐም መብት በመስጠቱ በጣሙን ከፋፈላቸው። ማንኛውም ሰው ቅዱስ መጽሐፍን እንደፈለገው የመተርጐም መብት ነበረው ። እንደኛው ወገን የእኔ የተሻለ ነው ሲል ሌላው እኔ ነኝ በመባባል በመለያየት በሰሜን አሜሪካ ተጉዘው በብዛት ሰፈሩ።

እነዚህ የተለያዩ የፕሮቴስታንት ቡድኖች በስብከት ኃይል ሌሎችን ከቀድሞ እምነታቸው ለማስለወጥ ጥረዋል ። ለፕሮቴስታንት እምነት ዐዳዲስ የኾኑ ሰዎችን ወደ እምነታቸው ለማስገባትና ለመለወጥ የሚያደርጉት ታላላቅ የጉባኤ ስብሰባና ቅስቀሳ (ቴንት ሚቲንግ) በየዘመናቱ ተደርጓል ። በዚህም ብዙ የተከፋፈሉ የክርስትና ቡድኖች ተፈጥረዋል ። የተለያዩ የፕሮቴስታንት ቡድን ሰባክያን በሬዲዮን እና በቴሌቪዥን መልእክታቸውን ያስተላልፋሉ። በአኹኑ ጊዜ ወደ 1,300 የሚጠጋ የሬዲዮን ፕሮግራም እና የቴለቪዥን የፕሮግራም ጣቢያዎች በአሜሪካ ምድር አሏቸው።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ከኦርቶዶክስ እና ከካቶሊክ ቀጥሎ ዛሬ በዓለም የተስፋፋቱት የፕሮቴስታንት ዘርፎች የሚገልጽ ነው።






ዋናው የመለያያ አንዱ ምክንያት በቅዱስ ቁርባን ላይ ያለው እመለካከት ሲኾን ሌላው ደግሞ መሥራቹ ሉተር በላቲን ቋንቋ ሶላ (ብቻ) በማለት (1) ክርስቶስ ብቻ (2) መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ (3) እምነት ብቻ (4) ጸጋ ብቻ (5) ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ በማለቱ ብዙ ልዩነት ተፈጥ

ሯል። በዚህ ልዩነት የተነሳ በየጊዜው ስማቸው እየበረከተ ብዙ የፕሮቴስታንት ቡድኖች በከፍተኛ ቁጥር በአሜሪካ ተመሥርተው ይገኛሉ። ይህም ተከፋፍሎ የተመሠረተው የእምነት ቡድን ወደ አፍሪካ (በተለይ ሦስተኛው ዓለም ብለው በሚጠሩት አገሮች) እና ወደሌሎች አህጉራት በብዛት እና በአይነት መልኩን ለዋውጦ እየተላከ (Export) ይገኛል።

## (፩) ሉተራውያን በአሜሪካ

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሉተራውያን ከካቶሊክ በተገነጠለው በጀርመኑ ሉተር መጠሪያ ስም የተሰየመ ነው ። ሉተር ከካቶሊክ የሚለይበትን 95 የሚኾኑ ነጥቦችን ጽፎ በዊትንበርግ ዩንቨርሲቲው ቤተ ክርስቲያን በር ላይ የሚገቡ እና የሚወጡት እንዲያዩቲ ግልጽ በማድረግ ለጠፈ። ይህም እምነቱ በአውሮፓ ውስጥ በዴንማርክ ፣ በፊንላንድ፣ በኖረዌይ ተስፋፋ።

በ1730 ጀምሮ አውሮፓ ውስጥ የተስቦ በሽታ በመነሳቱ በዙ ሕዝብ ማለቅ ጀመረ በዚህ የተነሳ ጀርመናውያን የሉተር ተከታዮች እንደማንኛውም ስደተኛ ወደ አሜሪካ ሃይማኖታቸውን ይዘው ገቡ።

የኖሮዌይ ሕዝቦችም በተለያየ ዘመናት በችግር እና በረሀብ የሉተርን እምነት ይዘው ወደ አሜሪካ ተሰደዱ። በአሜሪካ ቤተ ክርስቲያንን ማነጽ፤ ሆስፒታል መሥራት፣ ኮሌጅ እና ትምህርት ቤት መመሥረት ቀጠሉ።

በአሜሪካ በ1885 **ኢቫንጀሊካል ኮሽናንት ሉተራን** በዐዲስ መልክ ተመሠረተ ። ዛሬ በአሜሪካ ካሉት ሌሎች የፕሮቴስታንት እ ምነት **ኢቫንጀሊካል** ኮሽናንት ሉተራን ትልቁን ቦታ ይዞ የሚገኘው ነው ። 150 የሚደርሱ የተለያዩ የሉተራውያን የክርስትና እምነት ድርጅቶች ‹‹ተለያየ አመለካከት ተስፋፍተዋል ይገኛሉ ። ካለፉት 20 ዓመታት ወዲህ ወደ አንድነት እንምጣ በማለት ልዩነታቸውን ለማስወገድ እየሞከሩ ነው። በ1988 ይህ **ኢቫንጀሊካል ኮሽናንት ሉተራን** የሚለውን ስም የአንድነት ስማቸው አደረጉት ። በ1950 **ኢቫንጀሊካል** ፍሪ እና ሌሎች ተቋቁመዋል።

## (ሀ) ሚዙሪ ሉተራን ቤ. ክ ሲኖዶስ

ይህ የሉተራን የእምነት ዘርፍ የቀድሞውን ሥርዓት እጠብቃለኹ የሚል ቡድን ነው። ቀደም ባሉት ዘመን በስደት ከጀርመን የመጡት



በሚዙሪ ግዛት (እስቴት) የተቋቋሙት በየቦታው በጣም ተስፋፍተው ነበር። አብዛኛዎቹ ኦሀዮ፣ ኢንዲያና እና ሚቺጋን በብዛት ይገኛሉ ። እስከ 1930 ድረስ አገልግሎት የሚሰጡበት ቋንቋ በጀርመንኛ ነበር። ይህም መሥራቹ ሉተር የመሠረተበት ቋንቋ ስለኾነ ነው።

ሉተራውያን ብዙ የማስተማሪያ፣ የማሠልጠኛ እንዲሁም የመቀሰቀኛ መለስተኛ መጻሕፍት በማሳተም ታዋቂ ናቸው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በየቦታው አቋቁመዋል። በዚህ የትምህርት ቤት ማቋቋም በአሜሪካ ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቀጥሎ በኹለተኛ ደረጃነት እየተከተሉ ነው። የዚህ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሚዙሪ ሲኖዶስ የአባላት ቁጥር 2.6 ሚሊዮን ደርሷል።

## (ለ) ዊስኮንሲን ኢቫንጀሊካል ሉተራውያን ሲኖዶስ

ይህ ደግሞ ሌላው የተለየ ሉተራውያን እምነት ክፍል ተከታዮች መጠሪያ ስም ሲኾን ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ አባላት አሉበት። እነዚህም በጣም ጥብቅ በመኾናቸው ፤ የጋብቻ ፍችን ፣ የጽንስ ውርጃን ፣ ግብረ ሰዶምን እና መጥፎ የኾኑትን የሆሊውድ ፊልሞችን የሚቃወሙ ናቸው።

ሉተር ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ዐምስቱን አስፈላጊ አይደሉም በማለቱ ምስጢረ ክህነትን (ቅስና) አይቀበልም፤ በዚህ ምትክ ፓስተር (ጠባቂ) የሚለውን መረጠ ። የሚቀበላቸው ኹለቱን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ነው። እነዚህም ጥምቀትን እና ቁርባንን ሲኾን ቁርባንን ምሳሌ ነው እንጂ የክርስቶስ ሥጋና ደም አይደለም የሚለውን ሐሳብ አለው። ሰው ያለ ምግባር በእምነት ይድናል የሚል ፍልስፍናውን ሌላው ሐሳቡ ነው።

ይህም የአብዛኛው የፕሮቴስታንት ቡድን የሚቀበለው ነው ። ነገር ግን ቀደም ብሎ እንደተገለጸ ፤ እምነት እና ምግባር መለያየት እንደሌለባቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር

ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ኹሉ መንግሥተ ሰማይት ሊገባ አይችልም።

(ማቴ. 7፥21፤ ያዕቆ. 2፥20)

ይህ የሉተር አመለካከት እና አተረጓጎም እንደተገለጸው በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

ባጠቃላይ በአሜሪካ ውስጥ ሉተራውያን የክርስትና እምነት ተከታዮች 8.4 ሚሊዮን ይደርሳሉ ተብሎ ይገመታል። በሉተራን ሥር በጣም ብዙ ዘርፎች በዓለም ላይ ተሰማርተዋል። በአፍሪካ ለአፍሪካውያንም በሰባኬ ወንጌል ስም (በሚሽንነት) የተላኩት ቸርች አፍ ዘሉተራን ኮንፌሽን የሚባለውን ስም ይዘው የሚስፋፉም አሉ። ባጠቃላይ የሉተራውያን ቅርንጫፎች ወደ ኹለት መቶ ይደርሳሉ ተብሎ ይገመታል ።

## (፪) አንግሊካን በአሜሪካ

የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው ከ1530- 1534 ባለው ጊዜ ነው ። አመሠራረቱም በንጉሡ ሄነሪ 8ኛ አማካኝነት ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ በመውጣት ነው ። የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ በቨርጂንያ በቅኝ ገዢው ክፍል አንዱ ነበር። በበላይነት የሚመራው በካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ አስተዳደር ሥር ሲኾን የሊቀ ጳጳሱም መንበር በብሪታንያ ለንደን ውስጥ ነው።

በ1549 የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጳጳሱ በቶማስ ክራንሜር የተዘጋጀ የጋራ የጸሎት መጽሐፍ "ኮመን ፕሬየር" የሚባል አላቸው።[230] በዚህ የጸሎት መጽሐፍ ለዘመናት ሲጠቀሙበት ኖረዋል ። በአኹኑ ጊዜም ይህ መጽሐፍ የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን አንድ ካደረጋቸው አንዱ ነው።

አንግሊካን ኹለት የተለያዩ ክፍሎች አሉት ፤ አንዱ "ሀይ ቸርች"[231] ሲኾን ይህም የካቶሊክን የጥንቱን ባህል አልለቅም በማለት መዝሙሩን፣ የጸሎት ሥርዓቱን ባለመልቀቅ የላቲንን ዜማ ሥርዓት የሚያዜሙ ፤ በመንበር ላይ ሻማ የሚያበሩ እና ከካቶሊክ ሲወርድ የመጣውን ባህል የሚጠብቁት ናቸው ። እነዚህ የካቶሊክን ሥርዓት የተከተሉ አንግሊዞች በጥንት ጊዜ ጰሚዎችም ነበሩ።

ኹለተኛው ሎው ቸርች[232] የተባለው ሲኾን ይህ ቡድን በመንበሩ ላይ መብራት የማያበራ፣ መዝሙሩ ኹሉ በዘመናዊ መሣሪያ የታጀበ ወደ ፕሮቴስታንት የሚያደላ ዘመናዊ ነኝ የሚል ነው ። ቀደም ባለው ጊዜ መጠጥ መጠጣት ክልክል ነው በማለት ምእመናኖቹ የማይጠጡ ሲኾኑ እንደ ካቶሊክ ሥርዓት እና ባህል ተከታዩ "ሀይ ቸርች"

[230] Book of Common Prayer
[231] High Church or Liturgical worship
[232] Low Church or Free worship



ግን ጾምን አይጾሙም ነበር፤ በአኹኑ ጊዜ ግን ኹሉም በዚያ ሥርዓት መቀጠሉ እያጠራጠረ ነው።

የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን በየ10 ዓመቱ ከየአገሩ ያሉ ጳጳሳት እና ሊቃነ ጳጳሳቶቻቸው የሚሳተፉበት ዓለም አቀፍ የሲኖዶስ ስብሰባ ያደርጋሉ ። ይህም ስብሰባ የሚካኼደው በለንደን ከተማ በላምባዝ ቤተ መንግሥት (ቤተ ክህነት) ነው። ባለፉት አራት ስብሰባዎች ላይ ብዙ ውሳኔ አሳልፈዋል ። በአንዳንድ ውሳኔዎቻቸው ከቀድሞ ተያይዞ የመጣውን ሥርዓት እየሻሩ በዐዲስ ሥርዓት ለውጠዋል። ይህም ዐዲስ ሥርዓት ማምጣት ቀደምት የኾኑትን ቤተ ክርስቲያንን ያስደነገጠ ነበር ። በመጀመሪያ ሴቶች በዲቁና እንዲያገለግሉ ክህነት ይሰጣቸው ብለው አጸደቁ ። ይህም የክህነት አሰጣጥ በተፈጸመ ጊዜ ከፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በስተቀር ፤ የካቶሊክንና የኦርቶዶክሱን ዓለም አስደነገጠ ። በመቀጠልም እንደገና በ1992 ሴቶች የቅስና ክህነት እንዲሰጣቸው ተደረገ። በዚህም የተነሳ የእንግሊዝ ካህናትና ምእመናን ተከፋፈሉ ። ብዙ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትና ምእመናን ወደ ካቶሊክና ወደ ኦርቶዶክስ የክርስትና እምነት ገቡ። በክርስትናው ዓለም ታላቅ ሁከት ተነሳ ። በነዚህ ምክንያት የተነሳ የምእመናኑም እምነት ቀዘቀዘ።

በአኹኑ ጊዜ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አማንያን ወደ ቤተክርስቲያን በመኼድ ጸሎት የሚያደርጉበት ጊዜ በጣም ውሱን ነው ። ጨርሶ ከመሄድ አቋርጠዋል ማለት ሳይሻል አይቀርም ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ጎልተው የሚታዩት ለገና (ክሪስማርስ) በዓል ሲደርስ ወይም የተወሰኑ ቤተሰቦች ብቻ ለክርስትና ጥምቀት እና ለጋብቻ ብቻ ነው ። በሌላ ጊዜ በጣም ቁጥሩ ጥቂት የኾነ ምእመን ያውም ጥቂት ሽማግሌዎች ብቻ በቤተ ክርስቲያኑ ሲገኙ ወጣቱ ግን ጨርሶ ርቋል ። የእሑድ ሰንበት አምላኩ እና ቤተ ክርስቲያኑ የኳስ ጫዋታ ሜዳ እና የቡድን ደጋፊነት ሱስ ነው። ይህም አምላኩ ኾኗል ማለት ይቻላል።

## (ሀ) ኤጲስኮፓል

ኤጲስኮፓል ከግሪክ የተወሰደ ቃል ሲኾን፣ ኤጲስቆጶስ ማለት ነው። አንግሊካን ወይም የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ እና በእስኮትላንድ አንግሊካን ተብሎ ላለመጠራት ፕሮቴስታንት ኤጲስኮፓል ቸርች ተብሎ እንዲጠራ ኾን ተብሎ የተደረገ ነው። ኾኖም ግን ከአንግሊካን

ጋር ከአስተዳደር በስተቀር ብዙ ልዩነት የላቸውም። መልኩን ለወጥ ያደረገ አንግሊካን ነው ማለት ይቻላል።

የዚህ ኤጲስኮፓል እና የአንግሊካን አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ መግቢያ በሩ ቀይ ቀለም የተቀባ ነው ። ይህም ምልክት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምልክት ነው ብለው ያምናሉ ። የእንግሊዝ ተወላጅ የኾነው ኹሉ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተጠሪያችን ነው በማለት በእጁ ዘንግ (መጻር) ነጭ ጨርቅ ላይ ቀይ መስቀል ምልክት አስጨብጠው ስለውት ይታያል ። ይህም የእንግሊዞች ብሔራዊ ባንዲራቸው ነው። በተለይም ሚያዚያ 23 ቀን ለአንድ ሳምንት በፀል አድርገው ያከብሩታል።

ለኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ ሊቀ ጳጳስ ከእንግሊዝ አገር ተልኮ መመሪያ በመስጠት አሜሪካ ያለውን ኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያንን አያስተዳድርም። የወንጌል ስብከት ለማስፋፋት የገንዘብ ዕርዳታም ከአንግሊካን ቤተ ክርስትቲያን አስተዳደር አይደረግም። ይህም ምክንያቱ ከላይ እንደተገለጸው የአሜሪካ ሕዝብ እንደገና እንግሊዝ የበላይነቱን እንዳይዝ በመፍራት የተደረገ ነው ። ነገር ግን መሠረተ እምነቱ (ዶክትሪኑ) ባህሉና የአምልኮት ሥርዓት አቀራረቡ አንድ ነው።

አሜሪካኖች ከቅኝ አገዛዝ ነጻ ከወጡ በኋላ፥ በራሱ አስተዳደር የሚመራ ቤተ ክርስቲያን ኾኖ ኤጲስኮፓል ተባለ ። በከንክቲኬት ጳጳስ የሚመረጠው ቀሳውስት እና ምእመናን ተሰብስበው ነው። ከ1967 ጀምሮ ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድነት በለንደን ላምባዝ ቤተ መንግሥት (ቤተ ክህነት) ተገናኝቶ ጉባኤ ማድረግ እና መነጋገር ተጀመረ። በዚሁ የኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን በ1989 የመጀመሪያዋ የሴት ጳጳስ በመመረጧ ከላይ እንደተገለጸው ብዙ ውዝግብ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ አስከትሎ ነበር ። በኋላም በቦስተን የኤጲስቆፓል ጉባኤ (ኮንግርጌሽናሊስት) 11 የሴት ጳጳሳት በምእመናኑ ተመርጠው ተሾሙ።

በ1998 የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ ማለትም የወንድ ለወንድ ፤ የሴት ለሴት ጋብቻ በግልጽ ተፈቀደ ። አፍሪካውያን የአንግሊካን ጳጳሳት እና ምእመናን ተቃውሟቸውን አሰሙ። ነገር ግን ውጤት አላመጣም። በአሜሪካ አንዳንድ ቄሶች በቤተ ክርስቲያናቸው አንድ አይነት ጾታዎችን ጋብቻ ነው በማለት መባረክ ጀመሩ። ነገር ግን ብዙዎች በእምነቱ ውስጥ ያልኾኑትን ሳይቀር ጋብቻ ተብሎ መጠራት የለበትም በማለት ተቃወሞ አሰሙ ። ያም አልበቃ ብሎ በ2003 ላይ ጀነራል



ኮንቬንሽን የኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን የኹለት ሴቶች ልጆች አባት ቄስ ሚስቱን ፈትቶ ሰዶማዊ በመኾኑ ኹሉን አስደነገጠ። ይህ ሰዶማዊ ሰው ሪቨረንድ ጅን ሮቢንሰን እንደገና በ2003 የኒው ሀምፕሸር አገረ ስብከት ጳጳስ እንዲኾን መረጡት። ዓለምን ለአንድ ሰሞን አስደነገጠ፤ ወሬው ክርስቲያኑን ዓለም አናጋው ። ብዙ የእንግሊዝ እና የክርስቲያኑን ዓለም አብያተ ክርስቲያን ጉዳዩ አነታረካቸው።[233]

የአንግሊካንና የኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ እምነት እና ሥርዓት በጣም በመራቃቸው ብዙዎች በአገልግሎት ላይ የነበሩ ቀሳውስት እና ምእመናኖቻቸው ሳይቀር ጥለዋቸው ሸሽተዋል። ይህም የኾነበት ዋናው ምክንያት ፤ ከላይ እንደተጠቀሰው የሴት ቅስና፣ ለሰዶማዊ ሰው ክህነት መስጠታቸው እንዲሁም ሰዶማዊ ጋብቻ ጋብቻ ነው ብለው በመባረካቸው ነው ። ይህም ለአንግሊካንና ለኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ታላቅ ውድቀት ኾኗል።

ዛሬ በአሜሪካ ከ3.4 ሚሊዮን የሚጠጉት ነዋሪ አሜሪካውያን የኤጲስኮፓል አባል ወይም የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን አባላት ነን ብለው ያምናሉ።

አብዛኞዎቹ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ኾነው የነበሩት ከሌሎቹ እምነቶች የበለጠ የኤጲስቆፓል ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ናቸው ። በዋሽንግተን ዲሲ ያለው ብሔራዊ ካቴድራልም የዚሁ የኤጲስኮፓል ቤተ ክርስቲያን ነው። ይህ ካቴድራል በዓለም ካሉት የታወቁ ካቴድራሎች ውስጥ ስድስተኛ ቦታን የያዘ ነው ። የኤጲስኮፓል ቤተክርስቲያን ለአሜሪካ ብዙ ኮሌጆችን መሥርቷል ። በአሜሪካ ፖለቲካ ውስጥ ብዙ እንቅስቃሴ ያደረገ ነው ። በአሜሪካ ከኤጲስኮፓል ሌላ አንግሊካን ኮሙንዮን የሚባለው እና ሌሎችም ብዙ የተከፋፈሉ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ዘርፎችም አሉ።

## (፫) የእስኮትላንዱ ፕሬስቤተርያን (ተሐድሶ)

ከላይ እንደተገለጸው ዋናዎቹ የተሐድሶ መሪዎች እንደተገለጸው ማርቲን ሉተር እና ጆን ካልቪን ናቸው ። እነዚህ ኹለቱ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንድትከፋፈል ምክንያት ኾነዋል። ሉትር ከጀርመን ሲኾን ካልቪን እና ዝውንግሊን ከስዊዝ (ጄነቫ) ናቸው። ይህ እየተገነጣጠለ የመ

[233] **TIME** *The Year In Review 96*

ማው የተሐድሶ (የሪፎርምድ) ባህል፤ ቸርች ኦፍ ክራይስት እና ፕሬስቤ
ቴርያንን ያጠቃልላል።

ፕርስቤተርያን የተመሠረተው በ1536 ነው። ይህም ማለት ሽማ
ግሌዎች ታላላቆች ለማለት ነው ። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ለማ
ለት የታሰበ ነው ። እምነቱ ከካልቪን ተሐድሶ ጋር የተያያዘ ነው።

ሪፎርምድ ፕርስቤተርያን ቤተ ክርስቲያን ጥቂት የኾኑ እስኮት
ላንዳውያን ስዊዝ ውስጥ ካልቪን የመሠረተው ኮሌጅ ቅምረው ሲመ
ለሱ በእስኮትላንድ በ1690 ፕሬስቤተርያን በማለት ማስፋፋት ጀመሩ።
እንደገና በ1743 በደምብ ተደራጁ ። ይህ የፕሮቴስታንት የክርስትና
እምነት አሜሪካ የገባው በእስኮትላንዳውያን እና በእስኮትሽ አይርሽ
ከአየርላንድ ነው። አብዛኛው ግን ከእስኮትላንድ የመጡ ሲኾኑ እስኮ
ትሽ አይርሽ የሚባል ስም አላቸው። እነዚህ ኹሉ በአሜሪካ ተስፋፍ
ተዋል።

ፕሬስቤተርያን በቀድሞ ጊዜ በኒው ዮርክ እና በጆርጂያ ሠፍረ
ዋል። የተለያየ ቡድን በውስጡ አለ ። ይህም ክፍፍል በቀድሞ ጊዜ
የደቡብ እና የሰሜን ክፍል ተብለው የሚለዩ አማኞች ነበሩበት ።
በኋላ በባርያ ሥርዓት የተነሳ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ተመርተው
መለያየቱ ቀጥሎ ይኖሩ ነበር ። በ1983 እንደ ገና አንድ ለመኾን ሞከ
ረው የአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን በማለት ተዋሐዱ።[234] ፕሬስቤተርያን
ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ የተከፋፈለ ቡድን ነው ። በ1970 ናሽናል
ቸርች እና ወርልድ ካውንስል ቸርችን መሠረቱ ። በአጠቃላይ ቁጥራ
ቸው በአሜሪካ 4.3 ሚሊዮን ይደርሳሉ ተብሎ ይገመታል።

## (ሀ) ዳች ተሐድሶ (ሪፎርምድ)

ዳች ሪፎርምድ እንደ ፕሬስቤተርያን መሠረቱ ጆን ካልቪን ነው። ይህን
ንም የዳች ሪፎርምድ ቤተክርስቲያን ጊጀስቤርት ሀን የተባለው ሆላን
ዳዊ ዜጋ ቋቋመው። የሆላንድ (ኔዘርላንድ) ተወላጆች የኾኑ ተሐድሶ
እምነት በቅኝ ገዢው ዘመን በኒው ዮርክ ማንሀተን እና ኒው ጀርሲ
ሠፈሩ ። አብዛኛዎቹ ከአገራቸው ሲሰደዱ ከዋናው የተሐድሶ ቤተ ክር
ስቲያን መለየት አይፈልጉም ነበር ። ባህላቸውን እና ሥርዓታቸውን
አመስተርዳም እንዳለው ለመጠበቅ ሞከሩ። ባህላቸው ሳይለወጥ እንደ

[234] **Hastin, Mason & Pyper** *The Oxford Companion to Christian Thought., p.,429*



መጀመሪያው ይዘውት ቆዩ። በኋላም ሪፎርምድ ችርች በአሜሪካ የተሰ
ኘው በሆላንዳውያን በ1867 ተመሠረተ።

በአሜሪካ የተከፋፈሉ ብዙ የዳች ሪፎርምድ አብያተ ክርስቲያ
ናት አሉ ። ባጠቃላይ ዛሬ የአባላቶቻቸው ብዛት 300,000 ሺ አካባቢ
ሲደርስ 1,000 ሺ አብያተ ክርስቲያናት አሏቸው። አብዛኛዎቹ የሚገ
ኙት በመካከለኛው አሜሪካ ውስጥ ነው ። ስሙን ለወጥ ተደርጎ ፍሪ
ሪፎርምድ ቸርች ኖርዝ አሜሪካ ተብሎ ይታወቃል።

## (፬) ሜተዲስት በአሜሪካ

ሜተዲስት የሚባለው እምነት የዛሬ 300 ዓመት ዌስሊ ተብሎ ከሚጠ
ራው የእንግሊካን ቄስ ቤተሰብ ውስጥ ከዘጠኝ ልጆች መካከል የተወ
ለዱ ጆን ዌስሊ[235] እና ወንድሙ ቻርለስ ዌስሊ[236] የሚባሉት ወንድማማ
ቾች መሠረቱት፤ ጆን ዌስሊ በ6 ዓመት ዕድሜው ቤተሰቡንና እራሱን
ከእሳት ቃጠሎ አትርፎ ስለዳነ ራሱን "ከእሳት ተርፎ የወጣ" እያለ
ይጠራ ነበር።

ጆን ዌስሊ በእንግሊዝ ታሪክ ውስጥ የታወቀ ሰው ነው። የእን
ግሊዝ ቤተ ክርስቲያንን በጣም የሚያገለግል ነበር ። እነዚህ ወንድማ
ማቾች ትምህርታቸውን የተማሩት ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ነው። በዩኒቨ
ርስቲ ውስጥ በሚካኼደው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ባለማቋረጥ ይሳ
ተፉ ነበር። ጆን ዌስሊ በማርቲን ሉተር የተሠራጨውን የሮሜ መልእ
ክት ጸሑፍ አነበበ።

እነዚህ ወንድማማቾች ወደ አሜሪካ ለስብከተ ወንጌል በ1735
ተጉዘው ነበር ። በዚህ ጊዜ አሜሪካን ያለው ኑሮ እንደ እንግሊዝ
ኾኖ አላገኙትም። ስለዚህ ከሦስት ዓመት ኑሮ በኋላ ወደ አገራቸው
እንግሊዝ ተመልሰው በእንዲት ሠፈር ውስጥ ባለች ሕንጻ ቤተ ክርስቲ
ያን ስብከት ያካኼዱ ጀመር ። ከዚያም ዓለም ኹሉ መሰበክ አለበት
በማለት ወደ መንገድ ዳር ወጡ። ወንድሙ ቻርለስ በሙዚቃ መሣሪያ
ይዘምራል፤ ጆን ዌስሊ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ በመንገድ ላይ ሲሰብክ ቀስ
እያለ ብዙ ሰዎች በንግግሩ እየተማረኩ መበራከት ጀመሩ።

ጆን ዌስሊ ቀደም ሲል በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ የተማሪዎች
ማኅበር (ክለብ) በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ጊዜ ሜተዲስት የሚል ቅጽል

[235] (1703–1791)
[236] (1707–1788)

ስም ወጥቶለት ነበር። ይህም ማለት ሥራውን በቅደም ተከተል የሚያከ
ናውንና የሚሠራ ስለነበር በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሜተድ (method) ከሚል
ተነስተው የእምነቱንም ስም ሜተዲስት አሉት።

የሜተዲስት እምነት አሜሪካንን የቅኝ ገዢ ክፍሉ በነበረ ጊዜ
ጆሴፍ ፒልመር፣ ሪቻርድ ቦርድማን ከዚያም ፍራንሲስ አስበሪ የሚባ
ሉት ሰባኪዎች ይዘውት ተጓዙ ። ፍራንሲስ አስበሪ የአሜሪካ ሜተዲ
ስት አባት በመባል ሲታወቅ፤ በአሜሪካ ተመሠረተውም በ1784 ነው።

## (ሀ) አፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስኮፓል

የሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ በፍራንሲስ አስበሪ በአሜሪካ
ቢመሠረትም በነጮች የዘር አድልዎ ምክንያት ጥቁር ሰባኪው ሪቻርድ
አለን እና በተሰባሰቡ ጥቁሮች አንድነት ከነጮች ተገንጠሎ የተመሠ
ረተ ቤተ ክርስቲያን ነው ። ይህም የጥቁሮች አፍሪካን ሜተዲስት
ኤጲስኮፓል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1814 ተመሠረተ።

እስቴክሊ እስታርግ የሚባል በሰሜኑ የዳልዌር ግዛት ውስጥ
የሚኖር ሀብታም ገበሬ ሪቻርድ አለን የሚባለውን ባርያ ገዝቶ በእር
ሻው ቦታ ላይ በማሠማራት ያሠራው ነበር። በኋላ በነጻነት እንዲኖር
ለቀቀው ። ሪቻርድ አለን ነጻ ከወጣ በኋላ ጥቁሮችን እያሰባሰበ መጽ
ሐፍ ቅዱስን ያስተምር ጀመር። ብዙዎች ጥቁሮች ወደ ነጮቹ የሜተ
ዲስት ቤተ ክርስቲያን ይጓዙ ጀመር። በቤተ ክርስቲያን ከነጮቹ ይልቅ
የጥቁሮቹ ቁጥር በረከተ። ሌላ ተጨማሪ የተለየ ስገነት እንዲሠራና
ጥቁሮች ለብቻቸው እንዲኾኑ የሚል ከነጮቹ ሐሳብ ቀረበ ። ጥቁር
በነጭ አጠገብ ኾኖ እንዳይጸልይ ለማድረግ ታስቦ ተዘጋጀ። የተለየው
ስገነተት ሥራው ተጠናቆ በኅዳር 1787 እሑድ ቀን አገልግሎት መስ
ጠት ጀመረ።

በዚህ ጊዜ ሪቻርድ ከጓደኞቹ ከአቢሰሎም እና ከዊልያም ጋር
በመኾን ለእነሱ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ወደ ዐዲሱ ስገነት መኼድ
ሲገባቸው ኹል ጊዜ ወደ ሚቀመጡበት ቦታ ወደ ነጮቹ ኼዱ ። በዚ
ያም ተንበርከከው ይጸልዩ ጀመር። ወዲያው ነጭ የቦርድ አባል (አስተ
ዳደር) አቤሰሎምን የተቀመጠበት ቦታ ለነጭ እንዲለቅ ተነስ በማለት
ገፋው ። አቤሰሎም ጸሎቱን እስከሚጨርስ ድረስ እንኳን እንዲታገ
ሠው ቢጠይቀው አልፈቀደለትም አኹኑን ተነስ አለው ። ብድጋሚ
ቢጠይቅም እምቢ ተባለ ። የቦርዱ አስተዳደር ሌላ ነጭ ረዳት ጓደኛ
ውን የቦርድ አባል ጠራና ገፍትረው አቢሰሎምን አስነሱት።



ጎልቶ በሚታየው የቀለም ልዩነት ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም
በስውር ይመካከሩበት የነበረው ጊዜ እውን ኾነ፤ ጥሩ ምክንያት ተገኘ
የጸሎት አገልግሎቱ ሲያበቃ እነዚህ የተገፉ ሰዎች ወጥተው በፊላዳል
ፊያ የመጀመሪያውን የጥቁሮች የቅዱስ ጊዮርጊስን ሜተዲስት ቤተ ክር
ስቲያንን መሠረቱ ። በዚኹ አይነት ቀስ እያለ የጥቁሮች ሜተዲስት
በፊላዳልፍያ እና በቦልቲሞር ከተማ በሌሎችም ቦታዎች ተስፋፉ ።
ሪቻርድ አለን በፍራንሲስ አስበሪ ቅብና ከዚያም የመጀመሪያው የሜ
ተዲስት የጥቁሮች ጳጳስ በመኾን ተሾመ።

## (ለ) አፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስኮፓል ዛዮን

ሜተዲስት ኤጲስኮፓል ዛዮን ቸርች የተጀመረው በኒው ዮርክ ከተማ
ነው ። ይኼም የተጀመረው ነጮች የዘር ልዩነት ምክንያት በመኾኑ
ነው። መለያየት የጀመሩበት ጊዜ 1796 ነው፤ አመሠራረታቸውም ፦

- ዌዝሊያን ሜተዲስት ቸርች 1843 ተመሠረተ
- ሜተዲስት ኢፒስኮፓል ቸርች 1844 ተመሠረተ
- ቀጥሎም ዩናይትድ ሜተዲስት ቸርች ። ሌሎችም...።
- ፍሪ ሜተዲስት ቸርች፣
- ፒሊግሪም ሆሊ ቸርች፤
- ዘ ቸርች ኦፍ ናዘሪን፤ ይህ የሉተራን ቡድን የተመሠረተው
በ1908 በቴክሳስ ግዛት ነው። በዚህ እምነት 600 000 ሺ ተከታዮች
በአሜሪካ ሲኖሩት በዓለም ላይ 1. 2 ሚሊዮን ተከታዮች አሉ።

## (ሐ) ሳልቬሽን አርሚ በአሜሪካ

ሳልቬሽን አርሚ የተመሠረተው በ1878 ነው ። መሥራቹም ዊልያም
ቡዝ ሲኾን የቀድሞ የሜተዲስት ሰባኪ የነበረ ሰው ነው። ይህ የፕሮቴ
ስታንት የክርስትና እምነት 450 000 ሺ ተከታይ ሲኖሩት ፤ በዓለም
ላይም እንዲሁ ተስፋፍተዋል።

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሜተዲስት በባርያ ሥርዓት የተነሳ
በብዙ ቦታ ተከፋፈለው ተመሠረቱ ። እነዚህ የተከፋፈሉት ሜተዲስ
ቶች በ1939 ሰሜንና ደቡብ እንደገና ተለያዩ ። በዚህ የተነሳ በ1968
ዩናይትድ ሜተዲስት ቸርች ብለው ውሕደት አደረጉ ።

ዛሬ አፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስኮፓል ቸርች 8. 5 ሚልዮን አባ
ላት ሲኖሩት አፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስኮፓል ዛዮን ቸርች 4 ሚሊዮን
አባላት አሉት። በጠቅላላ ፍሪ ሜተዲስቶች የሚባሉት ተጨማምረው

13. 5 ሚሊዮን ደርሰዋል። አብዛኛዎቹ የሜተዲስት ካህናት የቅድስት ድንግል ማርያምን በድንግልና መውለድ አይቀበሉም።

## (፩) አናባፕቲስት

አናባፕቲስት ከሮማ ካቶሊክ፣ ከሉተራውያን፣ ከካልቪኒስት ፣ በ1525 ተገንጥሎ የወጣ ከኹሉም ጋር ስምምነት የሌለው ነው። አናባፕቲስት የሚለው ስም የመጣው ከግሪክ ሲኾን ይህም ማለት የቅድሞው ጥምቀት ትክክል አይደለም እንደገና መጠመቅ አለባችሁ ሲሉ ያወጡት ስም ነው። ይህም ከሮማ ቤተ ክርስቲያንና ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ለመለየት ጥምቀት በመረጨት ሳይኾን በመዘፈቅ ነው ለማለት ነው።

ይህ እምነት የተጀመረበት ቦታ በጄኔቫ እና በዙሪክ ከተሞች ነው። በዙሪክ በ1525 በመረጨት መጠመቅን በመቃወም የተነሳ ኮንሮድ ግሬቤልና ጆርጅ ብላሮክ የተባሉ የሮማ ካቶሊክ ቄሶች በመስማማት ተራ በተራ በመዘፈቅ እንደገና ተጠማምቀው እምነቱን እንደ ጀመሩትም ይነገራል።

ወደዚያው በቶማስ የሚመራው ዋናው ቡድን በዊንትንበርግ ታየ። ከዚያ በስዊዝ በጃኮብ ሁተር የሚመራው በ1536 ታየ። የሉተር ተከታዮች ጥላቻ ስላደረባቸው ያሳድዷቸው ነበር። በዚህ አማካኝነት ተሰደው በሞሮቪያ ጥገኝነት ጠየቁ ። አናባፕቲስት ፤ በሉተራውያን ፣ በካልቪን እና በሮማን ካቶሊክ ሲሳደድ ኖሯል። ከሞሮቢያ አሜሪካን የገቡት ሞሮቪያን ቸርች የሚል ስም ይዘው ተስፋፍተው ይኖራሉ።

ሌሎች የአናባፕቲስት ቡድን ደግሞ በ1725 ወደ አሜሪካ ገብተው በዚያም መስፋፋት ጀመሩ። በዚህ እምነት ሥር ያሉ ኹሉ አልኮል መጠጥ ፣ ቁማር ፣ ዳንስ ፣ በመሳሰሉት የሚደረገው መዝናናትን ኹሉ አይፈቅዱም ። እንደምንኩስና ወይም የገዳማውያን አኗኗር ሥርዓት አይነት ያለ ኑሮ አላቸው። ይህም ሲባል ትዳር እና ቤተሰብ መሥርተው የሚኖሩ ናቸው። እነዚህም የአናባፕቲስት ቅርንጫፎች ሜኖናይት፣ አሚሽ እና ብራዘርን ይባላሉ።

## (ሀ) ሜኖናይት

ሜኖናይት ስሙ የመጣው በሆላንድ (ኔዘርላንድ) ውስጥ ፍሪዝላንድ ከምትባለው ቦታ ነው። ይህም የሆላንድ ቄስ ሞኖ ሲሞን (1496 – 1561) ከሮማ ካቶሊክ ወጥቶ ወደ ዙሪክ በተጀመረው አናባፕቲስት ገባ ። ሞኖ ሲሞን ጠንክሮ አስተማረ ተከታይም አገኘ ። የዚህ የሜኖናይት እምነት በኅብረተሰቡ በጣም የተጠላ ስለነበረ ከአንዱ አገር ሲያሳድዷችሁ ወደሌላ አገር ሽሹ የተባለውን መነሻ በማድረግ በመጀመሪያ ከስዊዘርላንድ፣ ከጀርመን እና ከኔዘርላንድ ተሰደዱ ፤ በመቀጠል በሺ የሚቆጠሩ ወደ ነጻነቱ ዓለም አሜሪካ ተጓጉዘው ገቡ።



በአሜሪካ ከጥንቱ የአናባፕቲዝም ባህል ተገንጥለው ወጥተው በካቶሊኩ ቄስ ሜኖ ሲሞን ስም ሜኖናይት በማለት መጠሪያቸው አደረጉት ። የተለያዩበትም ምክንያት አንዱ የዘር፣ የባህል እና የአሜሪካንን ባህል በመከተል የተነሳ ነው። ብዙዎቹ የስዊዝ እና የጀርመን ሜኖናይት በአሜሪካ በፔንሲላቫኒያ በዊልያም ፔን አሰባሳቢነት ተሰባስበው የራሳቸውን የነጻነት ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ።

ሜኖናይትና አሚሽ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ከአንድ ቤተሰብ የተፈጠሩ ናቸው። ይህ የሜኖናይት እምነት በሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገለገላል። በአኹኑ ጊዜ አሜሪካ በብዛት የሜኖናይት እምነት ተከታይ ይኖራሉ።

## (ለ) አሚሽ

የስዊዝ አናባፕቲስት አማኝ፥ ጃኮብ አማን አማካኝነት በ1690 የእምነቱ መጠሪያ ስም በአማን አሚሽ ተባለ ። መሪው ጃኮብ አማንም የአናባፕቲስት አማኝ ከኾናችሁ ቀበቶ ፣ የጫማ ማሠሪያ ፣ የልብስ ቁልፍ (አዝራር)፣ የጸጉር ጌጥ (ሪቫን) ሌላም.... ኩራትን እና ትቢትን የሚያስከትሉ ሀብቶች እንዳይኖራችሁ አለ። ጃኮብ አማን ብዙ የሜኖናውያን አማኞች እና አውሮፓውያን በይበልጥ ሆላንዳውያን ባህላቸውን ይዘው ተከተሉት።

በ1710 ወደ አሜሪካ ከፍተኛ የጃኮብ አማን ቡድን ተከታዮች ለኹለተኛ ጊዜ ተሰደዱ። እነዚህም በብሪታንያ ቅኝ ግዛት ዘመን በፔንሲልቫንያ ተቀመጡ ። አኗኗራቸው አብሮ በኅብረት በመረዳዳት ነበር (የሐ. ሥራ 4፥32-35 ፤ 11)።

በአሁኑ ጊዜ ጥቂት የዚህ እምነት ተከታዮች ኢንዲያና እና ኔብራስካ አካባቢ እንዲሁም ካናዳ ውስጥ ይኖራሉ ። በየቦታው የሚኖሩት የእምነቱ ተከታዮች ዘመን እና ጊዜ አለወጣቸውም ። አንድ አይነት ሥርዓት እና ባህል አላቸው።

በአሜሪካ 100, 000 የሚደርሱ ይገኛሉ። በቅርቡ በመንግሥት በተጠናው ጥናት ግማሽ የሚኾነው አሚሽ በእርሻ እንደሚተዳደር ተረጋግጧል ። እንዲኹም በማሽን በተሠራ ነገር ሳይኾን በእጅ በተሠራ

ነገር ብቻ እንኖራለን ይላሉ። በማሽን የተሠራ ልብስ አይለብሱም። መጓጓዣቸው በፈረስ እና በጋሪ ነው ፤ መኪና አይነዱም ። በእርግጥ ሌላ በሚነዳው መኪና ይኼዳሉ ፤ ሕክምናም በአካባቢው ሆስፒታል ይታከማሉ፤ በሌላ ነገር በብዙ የተለዩ ናቸው። ትራክተር ፣ ስልክ (ቴሌፎን)፣ የኤሌክትሪክ መብራት፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ የላቸውም ። ነገር ግን በየቤቱ እየተሰባሰቡ ይማራሉ ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ትእዛዝ እና ሥርዓት በመከተል እንኖራለን ይላሉ።

ጥቅምት 2 ቀን 2006 በፔንሲልቫንያ በአሚሽ መንደር ያልተጠበቀ ነገር ተደረገ ። ይህም በምስት ሴቶች ልጆች ትምህርት ቤት ውስጥ በትምህርት ገበታቸው ላይ እያሉ ቻርለስ ሮበርት በሚባል በአንድ ወጣት በጥይት ተገደሉ ። ይህም ለመላው ዓለም በዜና ማሠራጫዎች ሲተላለፍ ታሪካቸውንና ማንነታቸውን ለማያውቅ ኹሉ እንዲታወቁ ኾነ።

በአሚሽ እምነት ሥር የተፈጠሩ ሌሎች እምነቶች አሉ ፤ ኤቫንጀሊካል ፍሪ ቸርች ኦፍ አሜሪካ፣ ሞሮቪያን ቸርች እና ሌሎችም ናቸው።

## (ሐ) ብራዘር ኢን ክራይስት

በአንድ ወቅት ሜኖናይትና አሚሽ ወንድማማች በመባባል መግባባት ጀመሩ ። በዚህ የተነሳ ወንድማማቾች (ብራዘር) ተባባሉ። ይህም ወንድምናማቾች መባባል በኮሚኒዝም ሥርዓት ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህም ኹትሪያን ብራዘርን በ1530 ተመሠረተ ። የዚህ የኹትሪያን ብራዘርን ቡድን እንቅስቃሴ የተጀመረው በሞሮቭያ ነው። ሞሮቪያ ዛሬ በቼክ ሪፓብሊክ የምትገኝ አገር ነች ። ወዲያው በጥላቻ ሲያሳድዷቸው እስሎቫኪያ እና ዩክሬይን ገቡ ። ከዚያም ወደ አሜሪካና ካናዳ ከ1870 ጀምሮ እስከ አንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ጊዜ ድረስ ባለማቋረጥ ገሠገሡ ፤ ዛሬ እነዚህ ቡድኖች 40,000 ሺ የሚደርሱ በአሜሪካ ይገኛሉ።

ይህ የአናባፕቲስት ሥርዓት እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ትዛዝ ሥርዓት ምስጢረ ቀንዲልን ይፈጽማሉ (የታመመን በዘይት መቀባት)፣ እግርን ማጠብ፤ መተጣጠብን ዋና ሥርዓታቸው አድርገው ይዘውታል።



## (ኟ) ኮንግሬሽናሊስት ወይም ፒሩታንስ

ኮንግርጌሽናል የተባለ የፕሮቴስታንት ቡድን የእንግሊዝ የመጀመሪያ ስፋሪዎች ካልቪኒስት ወይም ፒሩታንስ እየተባለ በቀድሞ ስም የሚጠሩት ናቸው። ይህ የአሜሪካ ሃይማኖት ነው ይሉታል ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ከወረሰችው ባህል መጥራት እና መንጻት አለባት መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን መለያየት አለባቸው ብለው ወደ አሜሪካ በመጓዝ ኑሮ የጀመሩት እንግሊዞች ናቸው። ከመጀመሪያው ከ1620 ተጓዥ ቡድን ቀጥሎ ተጨማሪ ቡድን ከእንግሊዝ በቀጥታ በ1630 ገብተዋል። በአሜሪካ የቅኝ ገዢው ክፍል በጊዜው ይደግፈው ስለነበር ከላይ እንደተገለጸው አንደኛው የአሜሪካ መሥራች ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

እነዚህ የቀድሞ ሰደተኞች ፒሩታንስ በምድር ላይ ትክክለኛውን የክርስትና እምነት እንሰብካለን ይሉ የነበሩ ናቸው ። ኮንግርጌሽናሊስት በማለት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በማቋቋም ካህናትና ምእመናን ያሉበት ማኅበር ማለት ነው። አስፈላጊውን ጉዳይ በአስተዳደሩ ተነጋግረው ወደ ምእመኑ (ኮንግርጌሽን) ይወስዱታል እንጂ ጳጳስ፤ ሊቀ ጳጳስ አይመራውም። ጳጳስና ሊቀ ጳጳስ የሚመራው የእንግሊዝን ቤተ ክርስቲያን እና በአሜሪካ ያለውን አንግሊካን ኮምዩነን ነው።

በቀድሞ ጊዜ የኮንግርጌሽናሊስት የታወቁ ሰባኪዎቻቸው ኮተን ማዘር[237] እና ጆናታን ኤድዋርድ[238] የሚባሉ ነበሩ። የእነዚህ ሰባኪዎች ተከታዮቻቸው በተለያዩ ጊዜ ኹለት የተከፈሉ ቤተ ክርስቲያኖች ተቋቋሙ ። እነዚህ "ዩናይትድ ቸርች ኦፍ ክራይስት" እና "ዩኒቴርያን" የሚባሉት ናቸው።

## (ሀ) ዩናይትድ ቸርች ኦፍ ክራይስት

ዩናይትድ ቸርች ኦፍ ክራይስት ዋና መሠረቱ ኮንግርጌሽናሊስት ነው። ይህም የተመሠረተው ቀደም ብሎ በጆናታን ኤድዋርድ እንዲሁም በ1801 በአርቶን ስቶን ነው። የተመሠረተበት ቦታም በኬንታኪ ሲኾን በጊዜው ዐዳዲስ ሰዎችን በመመልመል ተጀመረ ። የምልመላው ዋና ሐሳብ የነበረው ኹሉም መዳን አለበት በሚል አመለካከት ነበር ።

[237] (1663 - 1728)
[238] (1703 - 1758)

ይህም ማለት የእምነቱ እንቅስቃሴ ፤ ኃጢአት የሚኾን ነገር የለም ኹሉ ነገር ቅዱስ ነው የሚል አመለካከት ስለነበራቸው ነው ። በዚህ ትምህርታቸው የሰው ልጆች ቋንቋ በፍጹም የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር አይገልጽም ይላሉ። ብዙዎች የኮንግረጌሽናሊስት አባላቶች በዚህ ትምህርት አይደሰቱም ነበር። ሊበራሊዝም ከሚባሉት ተመራማሪዎች እና ተከራካሪዎች ሊገጥሙ አይፈልጉም ። በአሜሪካ የዩናይትድ ቸርች ኦፍ ክራይስት አባላት ከ3 እስከ4 ሚሊዮን ተከታይ ሲኖሩት በዓለም ላይ ወደ 6 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል።

## (ለ) ዩኒቴሪያን

ዩኒቴሪያን የሚለው መጠሪያ በመጀመሪያ የታየበት ዘመን በ1682 በእንግሊዝ አገር ነው። ጀማሪው ቶማስ አምሊን ነው።[239] በለንደን ውስጥ በምስጢረ ሥላሴ ላይ ተቃውሞውን አቀረበ ። ከዚያም ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን በመወገዱ ወደ አሜሪካ ገብቶ ትምህርቱን ያስፋፋ ጀመር።

በአጠቃላይ ቸርች ኦፍ ክራይስት (ኮንግርጌሽናሊስት) እና ዩኒቴሪያን፤ ጥንተ አብሶ ፣ መሠረተ እምነት (ዶግማን)፣ ጸሎተ ሃይማኖትን አይቀበሉም ። በምስጢረ ሥላሴ ላይ ያላቸው አመለካከት እንደ አርዮስ ነው ። በመካከላቸው አንዳንዶቹ ምሥጢረ ሥላሴን እንቀበላለን ይላሉ።

በአኹኑ ጊዜ ዩኒቴሪያን ዩንቨርሳል አሶሴሽን ኦፍ ኮንግርጌሽናል በአሜሪካ በመባል ሲታወቅ፤ ቡድኑን የሚከተለው አብዛኛው ሰው ነው። ይህ ቡድን እንደገና ለሦስት ተከፍሏል። ባጠቃላይ 1.4 ሚሊዮን ምእመናን ሲኖራቸው፤ 6,100 ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ ውስጥ አሏቸው። ዩኒቴሪያኖች ጦርነትን ይቃወማሉ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋራ ኢኮሚኒዝም የሚባለውን ግኑኙነት ማድረግ አይፈልጉም።

## (፯) ባፕቲስት በአሜሪካ

ባፕቲስት ማለት ጌታ የተጠመቀው በ30 ዓመቱ ስለኾነ መጠመቅ ከደጉ በኋላ ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው። የሕጻናትን ጥምቀት የሚቃወሙ

239. (1883 - 1741)



ናቸው። ይህም እምነት ከቀድሞ የእንግሊዝ ሴፓሬቲስት (ካልቪኒስት) እምነት ሐሳብ ጋር ብዙ አይለይም።

በኦርቶዶክስ እና በጥንታውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ግን ለመጠመቅ የተወሰነ የዕድሜ ገደብ የለውም። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት የሕፃናት ጥምቀት አከራካሪ አልነበረም ። ለምሳሌ ቆርነሌዎስ ከነቤተሰቡ መጠመቁ (በሐ. ሥራ. 10፥48) ፤ ሊዲያ ከነቤተሰቧ በመጠመቋ (የሐ. ሥራ 16፥15) ፤ የእስጢፋኖስ ቤተሰቦች (1ኛ ቆሮ. 1፥16) የተጠመቁ መኾኑ ስለተገለጸ፤ ሐዋርያት ያጠምቁ የነበሩት ቤተሰብን በሙላ እንጂ ሕፃናትን አስቀርተው አልነበረም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የተናገረው ያመነ የተጠመቀ ይድናል ስላለ ሳይጠመቅ ሞት እንዳይቀድም በቤተሰቦቹ እና በቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ሕፃናት ይጠመቃሉ። ይህ የባፕቲስት የክርስትና እምነት ግን ይህንን ሐሳብ ባለማመን እና ባለመቀበል ተመሠረተ።

ባፕቲስትና አናባፕቲስት ማለት ተርጉሙ፤ ድጋሚ በመዘፈቅ ጥምቀት መጠመቅ ማለት ነው ። የእንግሊዝ ባፕቲስት የካልቪን ተከታዮችን ሐሳብ በመያዝ ከቀድሞ የፒሩታንስ ቡድን አንዱ ነው ። በእንግሊዝ ለንደን በ1612 ዕውቅናን አገኘ።

የባፕቲስት እምነት መሥራቾች ከኾኑት ውስጥ ከኬምብሪጅ ዩንቨርሲቲ ተመርቀው የወጡ ቶማስ ሁከርና ተከታዩ ሮጀር ዊልያም የሚባሉ ይገኛሉ ። የእንግሊዝ የካልቪን ተከታዮች የኾኑ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ለማድረግ በጥንት ቤተ ክርስቲያኖች ሕንጻ ላይ ያሉትን የግርግዳ ሥዕሎች (ሞዛይክ) አይጠቅሙም በማለት ለባብረው አጠፋፏቸው ። ከነዚህም ውስጥ ጥቂት ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ያለ ጳጳስ ገነጠሉ ። በዚህ የተነሳ ወደ አመስተርዳም ተሰደው በደንብ በአመስተርዳም በ1609 ተደራጁ።

ወደ አሜሪካ ሮዴ አይላንድ በ1639 ኼደው ቤተ ክርስቲያን መሥርተው ተስፋፉ። በቅኝ ገዢው የብሪታንያ ዘመን ከሮዴ አይላንድ ወደ ደቡቡ ክፍል ተጓዙ። በአሜሪካ ያለው ባፕቲስት አውሮፓ ካለው በባህሉ ለየት ይላል ። ከካቶሊክ ቀጥሎ በቁጥር ብዛት ትልቁን ቦታ ይዞ ይገኛል ። 47 ሚሊዮን የሚጠጉት አሜሪካውያን የባፕቲስት እምነት ተከታዮች ናቸው፤ በ1990 በተደረገው ጥናት ከ5ቱ አንዱ የአሜሪካ ነዋሪ የባፕቲስት እምነት ተከታይ እንደኾነ በጥናት ቀርቧል ። ከኹሉም ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኘው ግን የደቡብ ክፍል ያለው ነዋሪ ሕዝብ ነው። 39 በመቶ አሜሪካውያን ባፕቲስት አባላት በደቡብ ክፍል ያሉት ናቸው። የካቶሊክ ተከታይ ግን 40 በመቶ ነው።

የዚህ እምነት ተከታዮች የታወቁት የሰብአዊ መብት ተከራካሪው ቄስ ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግና የታወቀው የአሜሪካ ሰባኪ ቢሊ ግርሃም ይገኙበታል።

## (ሀ) ባፕቲስት (ቦርን አጌን)

ከላይ እንደተገለጸው ባፕቲስት ማለት እንደገና መጠመቅ እንደገና መወለድ ወይም ቦርን አጌን ማለት ነው። እንደገና መወለድ የሚለው የመጣው ዮሐንስ ወንጌል ም. 3 ጌታ ኒቆዲሞስን የተናገረውን መነሻ በማድረግ ነው ። ቦርን አጌን የሚባለው ቃል ባፕቲስትና ጴንጠቆስጤ እምነት ውስጥ ብዙ ጊዜ ይነገራል ። ባፕቲስት ቦርን አጌን (እንደገና መወለድ) የሚባለው የተመሠረተው በአሜሪካ ነው።

ከሜተዲስት የተወለደው የጴንጠቆስጤም ተከታዮች እኛ ነን ቦርን አጌን ይላሉ ። በሉተር እንደተገለጸው ከመጽሐፍ ቅዱስ በስተቀር ሌላ እንዲነገር አንፈልግም ባዮች ናቸው። ዳግም መወለድ (ቦርን አጌን) ከሌሎቹ የሚለየው በትምህርት በዕውቀት ያልበሰሉትንና ሳያዘጋጁ ምንም ስለመጽሐፍ ቅዱስ የማያውቁ እንግዳ ሰዎችን ጌታን ተቀበል በማለት እንዲሰብኩና እንዲናገር እንዲነቃቃ በማድረግ ዋናው መንገድ ነው። ይህም ዋና የመያዣ ዘዴ የአባላትን ቁጥር ለማበራከት በጣም አስፈላጊው ነገር ስለኾነ እንግዳ ኾኖ የገባው ሰው ሰንበት ሲል ሌላውን እንዲቀሰቅስ እና ቅርንጫፍ በመፍጠር ራሱን ችሎ እንዲያስፋፋ ይበረታታል።

የታወቀው የአሜሪካ የቴሌቪዥን ሰባኪ ፓት ሮቢንሰን ሲሰብክ እየደጋገመ የሚጠቀምበት ቃላት በድንገት! (Suddenly!) የሚል እና በዚህች ቅጽበት! (at this moment!) ክርስቶስ ነገረኝ ፤ መንፈስ ቅዱስ ወረደ! በማለት ሰውን የሚስውጥበትን ቃላት ያስገባል። ቢኒይ ሂን ፣ ሮበር ቲልተን ሌሎችም አሰባበካቸው፥ ጌታ ተገለጸልኝ ፣ አነጋገረኝ፣ አገኘሁት የሚል ስለኾነ አነጋገራቸው የብዙዎችን የአሜሪካውያን መንፈስ ለውጧል ። በዚሁ የስብከት ተግባራቸው ከተከታዮቻቸው የሚያስገቡት ንዋይ በጣም ሀብታም አድርጓቸዋል። የግል አውሮፕላኖቻቸውን እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በየአህጉራቱ በመዘዋወር ይሰብካሉ ። አንዳንዶችም የዚህ ቦርን አጌን ተከታዮች ለጥቂት ጊዜ ደስታ፣ ፈንጠዝያና ፍጹም የመኾን ባሕርይ ያሳያሉ።



ከ39 በመቶ የአሜሪካ ባፕቲስት የጥንት ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ሲኾን ከዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚኾነው አሜሪካዊ ቦርን አጌን እንደኾነ ይነገራል።

## (ለ) ናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን

ናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን በ1915 ተመሠረተ። በዚህ ሥር የሚገኙት አብዛኛው አፍሪካን አሜሪካን ሲኾኑ እነዚህም በቀድሞ ጊዜ ከባርነት ነጻ የወጡ የደቡቡ ክፍሎች ናቸው። በአኹኑ ጊዜ ከነጮች ተከታዮች ይልቅ ጥቁሮች እምነቱን 55% በመቶ አፍሪካን አሜሪካን ሲከተሉ ፤ በአነስተኛ ቁጥር 39% በመቶ ነጮች ይከተላሉ።

አብዛኛው አፍሪካን አሜሪካን ክርስቲያኖች 90% በመቶ በሦስቱ ታላላቅ ፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅት ውስጥ የተሰባሰቡ ናቸው። እነዚህም፣ ባፕቲስት፣ ሜተዲስት እና ጴንጤቆስታል ውስጥ ናቸው። የተለያዩ አፍሪካን አሜሪካን የባፕቲስት ማኅበራት አሉ፤ ጥቂቶቹ ስማቸው እንደሚከተለው ነው።

- ናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን
- ናሽናል ባፕቲስት ኮንቬክሽን ዩንይትድ እስቴት አሜሪካ
- ናሽናል ኮንቬንሽን አፍ አሜሪካ
- ፕሮግረሲቭ ናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን
- ናሽናል ፕሪሜቲቭ ኮንቬንሽን
- ናሽናል ባፕቲስት ቸርች በዩናይትድ እስቴት አሜሪካ

በአንድ ላይ 12. 3 ሚልዮን አፍሪካን አሜሪካን ጥቁሮች ይገኙበታል። ይህም ማኅበር 5,800 አብያተ ክርስቲያናት አሉት።

## (ሐ) ጄነራል አሶሴሽን ሬጉላር ባፕቲስት

ይህ ማኅበር በ1932 የተመሠረተ ነው ። ዋናው የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን በጣም ዘመናዊ ኾነ በሚል ምክንያት ተገንጥሎ የወጣ ነው። ዛሬ 90,000 ሺ የሚደርሱ የማኅበሩ አባላት አሉት። እንዲሁም 1,400 አብያተ ክርስቲያናት አሉት። ፊልም፣ ትያትር፣ ሮክ ኤንድ ሮል ሙዚቃ አይነቶች፣ ግብረ ሰዶም፣ ፅንስ መበጥበጥ አይደግፉም።

### (መ) ሳውዝ ባፕቲስት ኮንቬንሽን

ሳውዝ ባፕቲስት ኮንቬንሽን ከደቡቡ ክፍል የእርስ በእርስ ጦርነቱ ጊዜ የተደራጁት ናቸው። በጊዜው የባርያ ባለቤቶች የነበሩትን ኹሉ ባርያን እስካልለቀቁ ድረስ ወንጌል እንዳይሰብኩ በማለት የተቃወሚቸው ናቸው። እነዚህም አፍሪካን አሜሪካኖች ቤተ ክርስቲያናቸውን ጥለው የራሳቸውን ሳውዝ ባፕቲስት ኮንቬንሽን መሠረቱ።

ነጮቹም እርስ በእርስ ጠብ በመፍጠራቸው ባለመግባባት ተለ ይተው የተከፈሉት ፕሬሚቲቭ ባፕቲስት ቸርች መሠረቱ። ባኹን ጊዜ በማዕከላዊ አሠራር የመንፈሳዊ አገልግሎት ሥራ አላቸው ። ኮሌጅ፣ ዩንቨርሲቲ ፣ ሆስፒታል የመሳሰሉትን ይረዳሉ፤ ያቋቁማሉ።

ባፕቲስት በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ኮንግርጌሽናሊስት ወይም ስፓ ሬቲስት የሚባሉት ተዋሕደው የሚጠሩበት ነው። በደቡብ ያለው የአሜ ሪካ ክፍል ከፍተኛውን የባፕቲስት ቁጥር ይዞ ይገኛል፤ 36. 3 ሚሊዮን ይደርሳሉ ተብሎ ይገመታል ። በአጠቃላይ /በአሜሪካ እጅግ በጣም ብዙ የኾኑ የተከፋፈሉ የባፕቲስት ቡድን ማኅበራት አሉ።

### (፯) ኳከር

ኳከር የተፈጠረበት ቦታ እንግሊዝ አገር በ1605 ነው፤ ኳከር የስብሰቡ ስም ነው። በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተጀመረ ። ኹለተኛ ትውልድ ላይ የተገኘው ሮበርት ባርክሌይ የሚባል ሰው በስፍራው ተተካ። ይህ ሮበርት ባርክሌይ የሚባል ሰው ለእማንያኑ መመሪያ አወጣ ። ማንም በኳከር እምነት ተከታይ የኾነ አባል ከእምነቱ ውጭ ከኾነ ሰው ጋር ጋብቻን እንዳይፈጽም ብሎ ከለከለ ። በተጨማሪም ሌሎች ሥርዓቶች ንም አወጣ።

ከነዚህ የኳከር መሥራች ከኾኑት አንዱ የታወቀው ጆርጅ ፎክ ስ[240] ነው ። ጆርጅ ፎክስ በአሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ በምሥራቅ ሰሜ ናዊ ክፍል በፔንሲልቫንያ እና በሌሎች ቦታዎች ቀስ እያለ እንዲስፋፋ ያደረገ ነው። ይህ እምነት በአሜሪካ ዋና ስሙ ሬልጅየስ ሶሳይቲ ኦፍ ፍሬንድስ ይባል ነበር። እነዚህም ስብሰቦች ለመጀመሪያ ጊዜ በፊላዴል ፊያ በ1827 ዓመታዊ ስብሰባ አድርገው ነበር።

የኳከር እምነት ምንም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን (ምስጢራት) አያከኼድም ። በመሰብሰቢያ ቦታቸው ሲገናኙ ዝም ብለው በጸጥታ

[240](1624 - 1691)



ቁጭ ይላሉ ። አይቀድሱም ወይም አይዘምሩም እንደ ሌሎቹ ፕሮቴስ ታንት የሙዚቃ መሣሪያ የላቸውም ፤ ሰባኪ ወይም ለመስበክ የሚዘ ጋጅ የለም ። ነገር ግን ከተሰበሰቡት አንዱ ካለበት በመኾን ከዝምታ እና ከጸጥታው መጥቶ ቆም ንግግር አድርጎ ይቀመጣል ። የሚናገሩት ስለ እኩልነት፣ ስለ አንድነት ወይም ስለ ሰላም ነው ። የኳከር ሃይማ ኖት ባይኖር ኖሮ በአሜሪካ በባርነት የተያዙ ጥቁሮች በቀላሉ ነጻ አይ ወጡም ነበር የሚል አስተያየት አለ ። ዩናይትድ እስቴት አሜሪካ ካሉት የክርስትና ሃይማኖቶች ኳከር የተለየ ነው ።

በአኹኑ ጊዜ ከመስፋፋት ይልቅ ከበፊት ቁጥሩ እየቀነሰ እንደ መጣ ይነገራል ። ዛሬ በአሜሪካ ምድር በትንሹ ከ100,000 ሺ በላይ የሚኾኑ ተከታዮች አሉ።

በተከታይ ብዛት ከፍተኛ ቁጥሩ ያለው፤ በፍሬንድስ ዩናይትድ ሚቲንግ በሚባለው ቡድን ውስጥ ሲኾን ፤ ዘ ፍሬንድስ ጀኔራል ኮንፍረ ንስና ዘ ኢቫንጀሊካል ፍሬንድስ ኢንተርናሽናል የሚባሉ ይገኙበታል።

## ምዕራፍ ፲፯
## በአሜሪካ የተፈጠሩ ሃይማኖቶች
## (የአገር ተወላጅ[241])

በአውሮፓውያን ወደ አሜሪካ ተጉዘው የሰፈሩትን እምነቶች፤ አሜሪካ ሲደርሱ ከአብሪካቸው የተወለዱትን፣ ያደጉትን፣ የተስፋፉትን በጥቂቱ አይተናል። በአሜሪካ እዚያው ተፀንሰው የተወለዱትንና እየተስፋፉ ያሉትን እምነቶችን ደግሞ ቀጥሎ እንመለከታለን ።

### (፩) ሞርሞን

ሞርሞን በአሜሪካ በፍጥነት እየተስፋፋ የመጣ እምነት ሲኾን መሥ ራቹ ጆሴፍ እስሚዝ ይባላል። (ከልት)

የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሰሜን አሜሪካ ዐዲስ ነቢይ በመ ባል በደጋፊዎቹ ይጠራል ። ጆሴፍ እስሚዝ ካአባቱ ጆሴፍና ከእናቱ ሉሲ እስሚዝ ተኅሣሥ 23 ቀን 1805 ሻሮን ቬርሞንት በተባለ ቦታ ተወለደ። ወላጆቹ በፓልሚራ ኒው ዮርክ ውስጥ የሚኖሩ ፤ በፕሮቴስ ታንት ክፍል አንዱ በነበረው እምነት ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ነበሩ።

[241] MADE in AMERICA

በዚህ ዘመን በኒው ዮርክ ብዙ የተከፋፈሉ ፕሮቴስታንቶች በከተማዋ መንገድ ላይ ዐዲስ አባላትን ለማሰባሰብ በቅስቀሳ ተሰማርተው ወደ እኔ! ወደ እኔ! በማለት ውድድር ገብተው ነበር።

ጆሴፍ እስሚዝ በዚህ እኔ ነኝ እውነተኛ በሚለው ቅስቀሳ አል ተደሰተም ። የመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ፍላጎት ነበረው ። በዚህ ጊዜ እሱም እንደሚለው በዛፍ ስር ኾኜ ስጸልይ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው አምሳል ተገለጸልኝ አለ። ይህን ራእይ አየሁ ሲል ዕድሜው 14 ዓመት ነበር። በመቀጠልም ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ በእውኘተኛ መንገድ መታደስ አለባት ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮኛል ፤ ስለዚህ የሃይማኖት ጸሎት፤ ሌሎችም ሥርዓቶች በቂ አይደሉምና መቅረት አለባቸው አለ።[242]

ጆሴፍ እስሚዝ እንደገና በ17 ዓመት ዕድሜው ራእይ አየሁ አለ። በዚህ ጊዜ በመስከረም 21 ቀን 1823 ሞሮኒ የሚባለው ከሞት የተነሳው የከበረው ነቢይ ተገለጸልኝ፤ እሱም በነርቢ ተራራ ላይ በወርቅ ሳህን ላይ የተጸፈ መጽሐፍ ተቀብሯል ብሎ አመለከተኝ አለ።

እንደሚለው ይህ መጽሐፍ በጥንት ጊዜ አሜሪካ ለሚኖሩ ሰዎች የተተወ ነው ። እነዚህም ሰዎች ፤ በነቢዩ ሌሂ መሪነት ከእሥራኤል ፈልሰው ከበዙ ሺህ ዓመታ 600 ዓ. ዓ. በፊት ሰሜን አሜሪካ የመጡ ዕብራውያን ናቸው፤ እነዚህ ዕብራውያን አሜሪካ በመጀመሪያ የደረሱ ጎሳዎች ኔፋውያን ይባሉ ነበር ፤ እነዚህም ጎሳዎች ለኹለት ተከፈሉ ፤ አንደኛው ኔፋውያን ክፍል ሲኾን ኹለተኛው ላማናውያን ይበሉ ነበር አለ።

በመቀጠልም ከኹለቱ አንደኛው ለእግዚአብሔር የታመነ አማኝ ሲኾን፤ ኹለተኛው ግን የማይታመን የማያምን ነበር። እነዚህ እርስ በራሳቸው ለዘመናት ተዋጉ ። በመጨረሻም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለኔፋውያን ጎሳዎች ተገለጸላቸው አንድ እንዲኾኑ አደረጋቸው አለ።

ከዚህም ጋር በአሜሪካ ምድር እውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያን እንዲመሠርቱ መመሪያ ሰጣቸው። ለጥቂት ዘመናት የኔፋውያን ጎሳዎች በሰላም ኖሩ። በኋላ በምድሪቷ ለረዥም ጊዜ የአየሩ ጠባይ በመለወጡ የኔፋውያን ጎሳዎች ከነሥልጣኔያቸው ተደመሰሱ። ነገር ግን ታሪካቸው እና የተማሩት ትምህርት በነቢዩ በሞርሞን አማካኝነት በወርቅ ሳህን ላይ ተጽፎ ነበር ። ከተደመሰሱት ውስጥ የተረፈው የኔፋውያን ወገን

[242] Hastin, Mason & Pyper., *p.,452*



የሞርሞን ልጅ ጄኔራል ሞሮኒ የአባቶቹን ሥልጣኔ በሰሜን ኒው ዮርክ በወርቅ ሳህን አድርጎ ከከበረ ድንጋይ መካከል በተራራ ላይ ቀብሮት ነበር።

ከዘመናት በኋላ ጆሴፍ እስሚዝ በሞርሞን ልጅ በሞሮኒ መን ፈስ ተመርቶ ያገኘው ይህን የሞርሞን መጽሐፍ ነው ። ጆሴፍ እስ ሚዝ ይህን መጽሐፍ በኹለት ፀጣም ልዩ የኾኑ ኡሪም እና ታሚም በሚባሉ ድንጋዮች መካከል አገኘው ። የመጨረሻው የኔፋውያን ባለታ ሪክ እና ከሞት የተነሳው ነቢይ ሞሮኒ ለጆሴፍ እስሚዝ ወደ እንግሊ ዝኛ እንዲተረጉም ፈቃድ ሰጠው ። ጆሴፍ እስሚዝ በእጁ ይህን የወ ርቅ ሳህን ይዞ ወደ ፔንሲልቫንያ ኼደ ። በተረጎመው ጊዜ ቤተሰቦቹ በፍጹም የወርቁን ሳህን አላዩም። በሞሮኒ ተወስዷል ተብሎ ይታመናል እስሚዝ ግን የነቢዩ ሞርሞንን መጽሐፍ ይዞ ወደ እንግሊዝኛ በ1830 ተርጉሞ ጨረሰ።

በመጋቢት 1830 በፓልሚራ እንዲባዛ ተደረገ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሞርሞን እምነት በይፋ በአሜሪካ ምድር ተመሠረተ። በ1831 ከኒው ዮርክ የተወሰኑት ተከታዮች ወደ ኦሀዮ እና ኢንዲያና ምዕራብ የአሜሪካ ክፍል እምነቱን ለማስፋፋት ተጓዙ ። ጆሴፍ እስሚዝ ሐዋር ያት፣ ነቢይ፣ ሽማግሌዎች...። በማለት የሥልጣን ተዋረድ እንዲኖር አደረገ። ስብከቱ ተቀባይነት ሲያገኝ የተከታዩን ቁጥር እንዲበዛ ሚስት ከኹለት በላይ ማግባትን እንደሚቻል ፈቀደ። እሱ ራሱ 49 የተለያዩ ሴቶችን አግብቶ እንደነበረ ይናገራል ፤ አንዳንድ ማስረጃዎች ደግሞ 27 ነው የሚሉም አሉ ። በሞርሞን እምነት ብዙ ሚስቶች ማግባት እንደመቀደስ ይቆጠራል።

ጥቁር ሕዝቦች (ኔግሮ) እና ኢንዲያን የተረገሙ የተጠሉ ናቸው በሚል በሞርሞን መጽሐፍ በየቦታው ተጽፏል (ሞሰስ 7፥8)። ይህም ትምህርት በ1960ና በ1970 ውስጥ በነበረው ሰብአዊ መብት ተከ ራካሪዎች ተቃውሞ ደርሶበታል። ሚዙሪ ግዛት የዔደን ገነት ነች ናአቮ እና ኢሊኖይስ የወደፊቷ መንግሥተ ሰማያት ናቸው (የእግዚአብሔር መንግሥት) በማለት ተከታዮቹን ይሰብክ ነበር።

ጆሴፍ እስሚዝ በ1844 የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ለመኾን ቅስቀሳ ያደርግ ጀመር ፤ ወደ ፖለቲካ ውስጥ ገባ፤ በመሠረታት ዐዲስ ከተማ ናአቮ ከንቲባ ኾነ ፤ ወዲያው ወታደራዊ ሚሊሽያ አቋቋመ ፤ የበላይ አዛዡም ጄነራል ጆሴፍ እስሚዝ በመባል እራሱን ሾመ ። ወንድሙ ሂሩም እና አሥራ ዐራት የሞርሞን መሪዎች በካርቴጅ ኢሊኖይስ ይኖሩ ነበር። ሞርሞን ያልተከተሉት እና እምነቱን የጠሉት የሚሠራ

ጨውን የሞርሞን ጋዜጣ በጥላቻ የተነሳ ማቃጠል እና ተከታዮቹንም መደብደብ ፣ መግደል ጀመሩ ። የተወሰኑት የሞርሞን መሪዎች በድርጊቱ ተቆጡ ። ከፍተኛ ረብሻ ተፈጠረ ፤ በረብሻው ምክንያት ጆሴፍ እስሚዝና ወንድሙ ሂሩም እስሚዝ ወደ እስር ቤት እንዲገቡ ተደረገ፤ ከእስር ቤት ከተፈቱ በኋላ ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር ባደረጉት ተደጋጋሚ ጠብ የተነሳ የጠመንጃ ተኩስ ልውውጥ ሰኔ 27 ቀን 1844 ተደረገ። በዚህ ተኩስ ልውውጥ ጆሴፍ እስሚዝ እና ወንድሙ ሂሩም እስሚዝ ተገደሉ።

ጆን እስሚዝ ሲሞት ሞርሞርን ለኹለት ተከፈለ ፤ አንደኛው የጆን እስሚዝን ቦታ ይዞ እንዲመራ የተደረገው አብረው ከነበሩት ውስጥ ቀደምትነት ያለው ተመረጠ። ይህም ሰው ቤርግሃም ያንግ የሚባል ነው። በጣም ኃይለኛ ሰው ነበር ። ቤርግሃም ያንግ በስሙ የትምህርት አካዳሚ አቋቋመ ፤ 53 ሚስቶች እና 57 ልጆች ነበሩት ። ቤርግሃም ያንግ የዩታን ጠቅላይ ግዛት እስከሚሞትበት እስከ 1877 ድረስ መራ ፤ በምትኩም ጆን ቴይለር ተተካ።

ኹለተኛው ቡድን ጆን እስሚዝ ሲሞት ቤርግሃም ያንግን አንከተልም ያሉት አዮዋ እና ኢሊኖይስ የሚኖሩት ከእስሚዝ ልጅ ጋር ቀጠሉ። የእርሱ ስም እንደ አባቱ ጆን እስሚዝ ጁኒየር ይባል ነበር። ሞርሞን የሚለውን በሌላ ስም ለውጦ "ቸርች ኦፍ ጅሰስ ክራይስት ሌተር ዴይ ሴይንት" በማሰኘት በዐዲስ ስም አሰየመ ። ከዚያ በኋላ በጣም በሐሳብ የተከፋፈሉ ብዙ ሞርሞኖች ተፈጠሩ። አንዳንዶቹ ብዙ ማግባት አያስፈልግም ይሉ ነበር ።

ጆሴፍ እስሚዝ ከሞተ በኋላ ጀምሮ የፕሮቴስታንትን ሐሳብ የሚከተሉ ሌሎችም በውስጡ ገብተዋል ። ይህም የሞርሞን እምነት በዩታህ ግዛት (እስቴት) በሶልት ሌክ ከተማ ውስጥ በብዛት ተከታዮች አሉት ። እምነቱን ለማስፋፋት መመሪያ ስላላቸው በጣም ተግተው ከ12 ዓመት የዕድሜ ክልል ጀምሮ እንዲሰብኩ ይደረጋሉ።

የሞርሞን መጽሐፍ በ1830 ላይ 116 ሚሊዮን ኮፒ ታትሟል፤ ወደ 102 በሚደርሱ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ከነዚህም አንዱ በዐማርኛ ቋንቋ ጭምር ተተርጉሞ ይገኛል። ይህ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍል የተወሰደው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከትንቢተ ሚልክያስ እና ከትንቢተ ኢሳይያስ ከዚያም ከሐዲስ ኪዳን ነው። ጆሴፍ እስሚዝ ኢየሱስን አይቸዋለሁ የሚለውንም ራእይ ጽፎበታል። እንዲሁ ደግሞ ስለ ቅዱስ ቁርባን፤ ስለ ጥምቀትና ስለ ምጽአተ ክርስቶስ ይናገራል።



የሞርሞን እምነት ክርስቶስን እምናለሁ ቢል እንኳን ምስጢረ ሥጋዌ እና ምሥጢረ ሥላሴን ስለማይቀበል። ከክርስትና እምነት ጋር ተጨምሮ አይቆጠርም። የመስቀል ምልክት እና ቀሳውስት የላቸውም። ከልት በመባል ይጠራል ። አልኮል መጠጣት ፤ ትንባሆ ማጨስ ፤ ቡናና ሻይ መጠጣት፤ ሥጋ መብላት የተከለከለ ሲኾን ፤ እንደ እስልምና ባህል ብዙ ሚስት ማግባት ግን የተፈቀደ ነው ።

የሞርሞን እምነት ተከታዮች በአሜሪካ ግዛቶች 5.5 ሚልዮን አባላት ተከታዮች ይኖራሉ ። በዚሁ በአሜሪካ ዛሬም ከ30 እስከ 60 የሚደርሱ የሞርሞን እምነቶች በመከፋፈል ተስፋፍተው ይገኛሉ። ነገር ግን ይበልጡን ቦታ ይዞ የሚገኘው በዋናው ዩታ ግዛት በሚገኘው ጅሰስ ክራይስት ኦፍ ሌተር ዴይ ሴይንት በመባል የሚታወቀው 97 በመቶ ደርሶ ይገኛል። የዚህ ሃይማኖት አማኞች ከአሜሪካ ውጭ በጣም እየ ተስፋፉ ይገኛሉ።

## (፪) ሰባተኛው ቀን አክባሪ (ሰቨን ዴይ አድቬንቲስት)

ሰባተኛው ቀን አክባሪ ማለት፡ ምጽአተ ክርስቶስ መምጫ ቀን ብለው የሚያምኑ ማለት ነው ። በአሜሪካ ክርስቶስ የሚመጣው በዚህ ቀን ነው፤ በዚህ ወራት ነው፤ እያሉ በቀጠሮ ሰው እየተሰበሰቡ ሲጠብቁ የነበሩ በኋላ ግን ያልኾነላቸው ብዙ እምነቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ የሰባተኛው ቀን አክባሪ (ሰቨን አድቬንቲስት) እና የሀዋ ምስክርነት (ጆሆቫህ ዊትነስ) ይገኙበታል።

የዚህ የሰባተኛ ቀን አክባሪ መሥራቹ ዊልያም ሚለር (1782–1849) ይባላል። ይህ ሰው ተራ ገበሬ የነበረ ነው ። በኋላ ጊዜ ወደ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን እምነት በመግባት መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጀመረ። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ምጽአተ ክርስቶስ እንደደረሰ ዘመኑን ይመረምር ጀመር።

የዳንኤልን የትንቢት መጽሐፍ መረጃው በማድረግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ1843 ዳግም ይመጣል እያለ በኒው ዮርክ ግዛት በየወረዳው ይሰብክ ጀመር ፤ ይህን ስብከቱን በትንሽ መጽሐፍ ጽፎ በተነ። ከዚያም በባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ለፓስተርነት ብቁ ነው ተብሎ የፓስተርነት ሹመት ተሰጠው ። በዚህ ወቅት ጥሩ አጋጣሚ ስላገኘ ከ1840 ጀምሮ በከፍተኛ ኹኔታ በሰፊው ይሰብክ ጀመር ። የጻፈውን መጽሐፍ ያነበቡት እና ስብከቱን የሰሙት ኹሉ ያን ሚለር ያለውን መጋቢት 21 ቀን 1843 ጀምሮ እስከ 1844 ድረስ ባለው ጊዜ ለአ

ንድ ዓመት ይመጣል በሚል ይጠብቁ ጀመር ። ይህን የሰሙ ኹሉ
የምጽአተ ክርስቶስን መድረስ በፍርሀት እንዲሁም በጉጉት ይጠብቁ
ነበር። መድረስ አይቀርምና ሲደርስ ምንም የኾነ ነገር አልነበረም።

ዊልያም ሚለር እንደገና ቀኑን ለውጦ ምጽአተ ክርስቶስ የሚ
መጣው በጥቅምት 22 ቀን 1844 ነው ብሎ ዐዲስ የአርማጌዶን ቀን
አለ። በድጋሚ ሳይኾን ቀረ ስለዚህ ተከታዮቹን በጣም አሳፈራቸው።
አጥባቂዎቹ ተከታዮቹ ግን እምነቱን ሊተውት አልፈለጉም፤ ቀየር አድ
ርገው ይመጣል ነገር ግን ቀኒቱና ሰዓቲቱን አይታወቅም ትብሏል
ብለው ይናገሩ ጀመር። ከዚያ ጊዜ ጀምረው ክርስቶስ የሚመለክበት
ዕለት በብሉይ ኪዳን ሰንበት ቅዳሜ ነው ። ክርስቶስ የሚመጣውም
በዚህ ቀን ነው አሉ ፤ ይህንም ዕለት ሰቨን አድቬንቲስት ተባለ ።
ይህም ማለት "ሰባተኛው ቀን የክርስቶስ መምጫ ዕለት" ማለት ነው።

በ1860 ዋናው የበላይ ጠባቂው የአስተዳደር ቦታው ከኒው
ዮርክ ወደ ባትል ክሪክ ሚቺጋን ተዛወረ።

ሰቨን አድቬንቲስት በጣም አጥባቂ ፕሮቴስታንት ክፍሎች
አሉት ። ይህ በጣም አክራሪው ክፍል ቅጣይ ከኾነው አንዱ ዴቪድ
ያን ከልት የሚባለው ነው። ቴክሳስ ክፍለ አገር በዋኮ በ1993 ዴቪድ
ኮረሽ የሚባለው የ33 ዓመት ዕድሜ ያለው ሰው የጌታ ኹለተኛ መም
ጣት ከእኔ ጋራ ነው፤ "እኔ የእግዚአብሔር በጉ ነኝ" (Lamb of God)
እኔ ራሴ መሢሕ ነኝ በማለት ሰዎችን መስበክ ጀመረ ። ብዙዎች አም
ነው ተከተሉት። ማውንት ካርሜል በሚባለው አንድ ቦታ ተሰባሰቡ ።
መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሰ ስለምጽአተ ክርስቶስ ይሰብክ ነበር። ስብከ
ቱን የሰሙ ኹሉ ተማረኩለት ። የብዙዎቹ ውሏቸው፣ አዳራቸው በዚ
ያው ከእርሱ ጋር ኾነ ። በኋላም ሰው መግደሉንና በዝሙት ልጃገረዶ
ችን ደፈረ ተብሎ ለመንግሥት ሪፖርት ተደረገ ። በዚህ የተነሳ ከመን
ግሥት ጋራ ድርድር ቢደረግ እምቢ በማለት እጁን አልሰጥም ስላለ
መንግሥት ያሉበትን ቦታ በታንክ አፈራረሰው ፤ በእሳት አቃጠሉት።
መሪው ዴቪድ ኮረሽ ከእርሱ ጋር ያሉት እንዲቃጠሉና በሰማዕትነት
እንዲሞቱ ያበረታታ ነበር ። ሚያዚያ 19 ቀን 1993 ሃያ አንድ ሕጻና
ትን ጨምሮ ወደ ሰማንያ አምስት የሚደርሱ ሰዎች በሕንጻ ውስጥ
አብረው ተቃጥለው ሞቱ።

ሰቨን አድቬንቲስት ዛሬ በአሜሪካ እና በመላው ዓለም እየተስ
ፋፋ ያለ እምነት ነው። በስሩም ብዙ ቅርንጫፎች አሉ።



## (፫) የሆዋ ምስክርነት (ጂሆቫህ ዊትነስ)

ጂሆቫህ ዊትነስ የተጀመረው በ1870 ነው ። የዚህ እምነት መሥራቹ
ቻርለስ ታዜ ረሰል የሚባል ሰው ነው። ነገር ግን ቀደም ሲል ሐሳቡን
የጠነሰሰው ጆሴፍ ፍራንክሊን እንደኾነ ቻርለስ ከእርሱ እንደተቀበለ
ይነገራል።

ቻርለስ ታዜ ረሰል (1825-1916) በአሜሪካ በፒተርስበርግ
ከተማ ውስጥ ተወለደ ። ያደገው ፒሩታንስ ወይም ኮንግርጌሽናሊስት
በሚባለው እምነት ስር ነበር ። በዚህ ዘመን ኹሉም የፕሮቴስታንት
ቡድኖች የእኛ ነው ትክክለኛ በሚሉበት ዘመን እርሱም የመጽሐፍ
ቅዱስ ጥናት ጓድ የሚባል ቡድን አቋቋመ (1868)። መጽሐፍ ቅዱስን
በቀጥታ ቃል በቃል ተርጉሞ ፤ ምስጢረ ሥላሴ አስፈላጊ አይደለም
በማለት የአርዮስን ትምህርት በመከተል እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶ
ስን ፈጥሮ እሱ ደግሞ እንዲፈጥር ፈጠረው የሚል ትምህርት ያስፋፋ
ጀመር።

ይህ ሐሳቡ በኒቅያ ጉባኤ የተወገዘውን የአርዮስን እምነት አስ
ተሳሰብ የተከተለ ነው። ይህም እምነት በጸሎተ ሃይማኖት (በሃይማኖት
ጸሎት) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፤ ከእውነ
ተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ"
በሚል ቅዱስ መጽሐፍን መመሪያ አድርገው ወስነውት የነበረ ነው ።
ይህን ትምህርት ባለመቀበሉ አርዮስ የተወገዘ ነው ። ቻርለስ ታዜ
ረሰል ይህንን የአርዮስን እምነት በዚህ ዘመን ለማደስ ተነሳ፤ ብዙዎች
ተከተሉት።

ቻርለስ ታዜ ረሰል ሌላው ስብከቱ ደግሞ በ1914 የዓለም ፍጻ
ሜ ይኾናል አለ። ክርስቶስ ቀደም ብሎ በ1874 መጥቷል ለታላቁ የአ
ርማጌዶን ዘመን እየተዘጋጀነው አለ ። በ1878 በፒተርስበርግ ከተማ
በአንድ ሰፈር ውስጥ የጂሆቫህ ዊትነስ ሰባኪ (ፓስተር) ኾነ ፤ በዚ
ያው በዓመቱ ወች ታዎር የሚል የክርስቶስን መምጣት የሚናገር
መጽሔት አዘጋጀ ። ነገር ግን ምንም ነገር ሳይመጣ ቀረ ፤ የአንደኛ
ዓለም ጦርነትም አበቃ።

የዚህ እንቅስቃሴ ተከታይ ጆሴፍ ኤፍ ሩተር ፎርድ የቻርለስ
ረሰልን ትንቢት እንደገና ተረጐመው ። ክርስቶስ በሰማይ በጂሆቫህ
ዙፋን ሲቀመጥ እና የመጨረሻውን መለከት ሲጠብቅ ነው በማለት
በራሱ ሐሳብ አስተካክሎ ይሰብክ ጀመር፤ ብዙዎች ተከተሉት።

ዛሬ ይህ አሜሪካ ውስጥ የተመሠረተ እምነት ማዕከሉ ዘ ዎች ታወር ይባላል። የሚገኘውም በኒው ዮርክ ከተማ በብሩክሊን አካባቢ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሱን በራሳቸው አጻጻፍ ለውጠውታል[243]። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጽሑፎች በጥንቃቄ አያዘጋጁ በየጊዜው ያሠራጫሉ። ከዩናይትድ እስቴት መንግሥት ጋራ ብዙ ጊዜ ተጋጭቷል። ነገር ግን ጠቅላይ ፍርድ ቤት (ሱፐሪየም ኮርት) የሃይማኖት ነጻነት ሕግ ስለአሰከበረ ምንም ማድረግ አልቻሉም።

በምስጢረ ሥላሴና በምስጢረ ሥጋዌ እንደ ማንኛውም የክርስቲያን እምነት ስለማይቀበሉ እና ስለማያምኑ የክርስቲያን እምነት (ደኖምኔሽን) አይባልም። ከዘመኑ አንዱ በሰው የተፈጠረ እምነት (ሴክት) በመባል ይጠራል ። የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጉባኤ ኅይም ተካፋይነት እና አንድነት የለውም ። የዚህ እምነት አባሎች ቤት ለቤት እየዞሩ በመስበክና በመቀስቀስ የታወቁ ናቸው ፤ ይህም ዋናው የእምነቱ መመሪያ ነው። በዚህ ክፍለ ዘመን የዚህ እምነት ተከታዮቹ ያለ ዕረፍት ቅስቀሳ ስለሚያደርጉ በከፍተኛ ፍጥነት በዓለም እየተስፋፋ ከሚገኙት አንዱ እምነት ኾኗል።

የጅሆቫህ ዊትነስ በአሜሪካ፣ በብራዚል፣ በሜክሲኮ እንዲሁም በአፍሪካ በከፍተኛ ቁጥር እየተስፋፋ ይገኛል፤ የመሰብሰቢያ ቦታቸውም ቤተ ክርስቲያን ሳይኾን ኪንግደም ሆል በመባል ይጠራል።

## (፬) ክርስቲያን ሳይንስ (ቸርች ኦፍ ክራይስት)

ክርስቲያን ሳይንስ የተመሠረተው በሜሪ ቤከር ኤዲ በኒው ሀምፕሸር በ1830 ነው። ሜሪ የተወለደችው ኮንከርድ ኒው ሃምፕሸር በሚባለው ቦታ ነው (1821 – 1910)። አባቷ የፒሩታንስ እምነት ተከታይ የነበር ብዙ ጊዜ ለችግረኞች ርዳታ የሚያደርግ ፤ ልብስ ለሌለው ልብስ የሚሰጥ ፤ የተራብ የሚያበላና የሚያጠጣ ፤ መጠለያ በመስጠት የሚረዳ ስራ የእርሻ ቦታ ያለው ሀብታም ገበሬ ነበር።

ሜሪ በልጅነቷ መጽሐፍ ቅዱስን ያለማቋረጥ ታነብ ነበር። እንዲሁም በቀን ስባት ጊዜ ትጸልያለች። ባንድ ወቅት የ12 ዓመት ልጅ በነበረች ጊዜ ትኩሳት ስለያዛት ጸለየች ወዲያው ትኩሳቱ ለቀቃት ። በዚህ የተነሳ ክርስቲያን ሳይንስ የሚል መጽሐፍ ጻፈች ፤ የጽሑፏን

243 New World Translation of the Holy Scriptures



የግሥ አገባቡንና ፀረፍተ ነገሩን የመንደሩ የፒሩታንስ ቄስ አረመላት። ሰው ኹሉ አእምሮውን እና አካሉን በጤና መጠበቅ አለበት ይህን ካደረገ ፈውስ ያገኛል ትል ነበር ። ይህን እምነቷን ክርስቲያን ሳይንስ በማለት ሰየመችው።

ሜሪ በ1877 ሀብታም የነበረውን ሦስተኛ ባሏን አግብታ ትኖር ነበር። እሱ ሲሞት ብዙ ንብረት ወረሰች ። ይህ ሀብት ማግኘት እምነቱን በገንዘብ ኃይል እንድታስፋፋው ረዳት። የክርስቲያን ሳይንስ በእንግሊዘኛ ተናጋሪው ዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀባይነትን አገኘ።

ሜሪ በኒው ሀምፕሸር በ1930 የመሰብሰቢያ ቦታ አዘጋጀች ። የታመሙ ሰዎችን ማከም፤ ቁስል ከኾነ ማጠብ ...፤ የመሳሰሉትን ታደርግ ነበር። ለእምነቷ ወና አድርጋ የምታቀርበው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል በአልጋ ላይ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አምጥተው እምነታቸውን አይቶ ሽባውን አንተ ልጅ አይዞህ ኃጢያትህ ተሠረየችልህ በማለት የፈወሰውን (ማቴ. 9፥7) ፤ እሷም እንደ ጌታ መፈወስ እንደምትችል በመስበክ እንቅስቃሴዋን ቀጠለች።

በአንድ ወቅት በረዶ አንሸራቷት የጀርባዋ አጥንት ተቀጥቅጦ ተጎዳች ። ኩምቢ የሚባለው ሰዓት ሠሪ ሕክምና አደረገላት ። ከዚህ በሽታዋ በተአምር እንደዳነች ይነገራል።

ዛሬ በቦስተን በሜሪ የተጀመረው ክርስቲያን ሳይንስ በአሜሪካ በትላልቅ ከተሞች ተስፋፍቶ ይገኛል። በየጊዜው ዘክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር የሚል መጽሔት እየተዘጋጀ ይሠራጫል ። ይህ ሜሪ የጀመረችው እምነት ቅርንጫፍ አውጥቶ በአሜሪካ ምድር፤ ከዚያም በዓለም እየተስፋፋ ይገኛል ። ስለ ጤና አጥብቆ ይመከራል ፤ በሳይንሳዊ መንገድ፣ በቅዱስ መጽሐፍ መሠረትነት መለኮታዊ ማዳን ይደረጋል ብለው ተከታዮቿ ኹሉ የሚያምኑ ናቸው።

## (፭) ጴንጤቆስጤ

ጴንጤቆስጤ በአሜሪካ ከሦስቱ በጣም በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ካሉት እምነቶች አንዱ ነው። እነዚህም ሞርሞን ፣ ዘ ክርስቲያን ቸርችስ እና ዘ እሴምብሊ ኦፍ ጎድ (ጴንጤቆስጤ) የሚባሉት ናቸው።

ጴንጤቆስጤ ሚያዚያ 12 ቀን 1906 በካሊፎርኒያ ግዛት በሎሳንጀለስ ከተማ በቁጥር 312 አዙዛ መንገድ (አዙዛ እስትሪት) በተባለው ቦታ ተጀመረ። መሥራቹም ዊልያም ሲሞር ይባላል ። ዊልያም

ሲሞር ትምህርቱን የተማረው ቶፔካ በሚባል ካንሳስ ግዛት ውስጥ ነው፤ የተማረበት ኮሌጅ ቤታኒይ ባይብል ኮሌጅ ይባላል።

ይህ ሰው የአፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስቆፓል ቸርች የተባለውን የቀድሞ እምነቱን ትቶ በመንገድ ላይ መስበክ ጀመረ። ለሦስት ዓመት ያህል ከሰበከ በኋላ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ትንሣኤ ባለፈ በሃምሳኛው ቀን ወይም በጴንጤቆስጤ[244] (በበዓለ ሃምሳ) ተሰብስበው ትምህርቱን ይሰሙ ነበር። ሦስት ዓመት ተሰባስበው የተማሩት ትምህርት በቃን ብለው ለየት አሉ። በሐዋርያት የወረደው መንፈስ ቅዱስ በእኛም ላይ በእሳት አምሳል አኹን ወረደብናል ብለው መንዘፍዘፍ፣ መጮህ፣ በልሳን እንናገራለን፣ በሽተኛ እናድናለን ይሉ ጀመር።

ወዲያው በአካባቢው ወሬው እየተስፋፋ ኼደ ። ይህ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንቅስቃሴ ወደ ሰሜኑ እና ወደ ምሥራቁ የአሜሪካ ክፍሎች በፍጥነት ተስፋፋ። በተለይም ከ1960 በኋላ ወደ ብዙ አገሮች ተሠራጨ ። እንዲሁም በአውሮፓ እና በደቡብ አሜሪካ ተስፋፋ ብዙዎች የነበሩበትን እምነት እየተው ገቡበት ። አንዳንዶቹም እምነቱን ተቀብለናል እያሉ መልኩን እየቀያየሩ በዐዲስ መልክ ሌሎችንም ቅርንጫፎች ይመሠርቱ ጀመር ፤

ባለመግባባት በሐሳብ እየተከፋፈሉ ቁጥራቸው በጣም ብዙ የኾኑ የጴንጤቆስጤ ቡድኖች አሉ። ከነዚህም ውስጥ በጣም ጥቂቶቹ እና ጎልተው የሚታወቁት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

- ቸርች ኦፍ ጎድ በ1897 በአሜሪካ በክሊቭላንድ ተከፍሎ ተመሠረተ ነው። ይህም እምነት በአሜሪካ 750, 000 ሺ የሚደርሱ ሲከተሉ በዓለም ላይ ግን 6 ሚልዮን አባላት አሉት፤ ይህ ስብስብ በፍጥነት ዕያደገ የመጣ ትልቁ የጴንጤቆስጤ አንዱ ክፍል ነው።

- ፎር እስኩዌር ጎስፔል የተመሠረተው በ1927 ነው ። ይህም በተለየ ስሙ ኢንተርናሽናል ኦፍ ዘ ፎር እስኩዌር ጎስፔል ይባላል ። በዚህ እምነት ወደ 235, 000 ሺ የሚደርሱ አሜሪካውያን ሲኖሩት 3.6 ሚሊዮን በላይ የሚኾን በዓለም ላይ ተከታዮች አሉት። የተመሠረተው ኤሚ ሴምፕሌ በምትባለው ሴት

[244] ጴንጤቆስጤ ማለት በግሪክ ቋንቋ ሃምሳኛው ቀን ማለት ነው።



ነው። ይህች ሴት በአሜሪካ ታዋቂ ከሚባሉት አንዲቷ ነች ። በዚህ ፎር እስኩዌር ጎስፔል ሥር ብዙዎች ተመሥርተዋል።

- ክርስቲያን ኤንድ ሚሽነሪ አሊያንስ፤ ይህ ቡድን 270 000 ሺ አሜሪካውያን ሲከተሉት በዓለም ላይ 2 ሚሊዮን ተከታይ እንዳሉት ይነገራል።
- ቪንያርድ ሚኒስቲሪስ የሚባለው እምነት ደግሞ በ1983 የተመሠረተ ነው። በዚህ ሥር ብዙዎች ቅርንጫፎች ተመሥርተዋል፤ በግምት100 000 ሺ አሜሪካውያን ይከተሉታል። የተጀመረው በ1974 ከአንድ ሕንጻ ውስጥ ነው። በ1982 በጆን ዊምቤር ቪንያርድ ተብሎ በመጠራት ይታወቅ ጀመረ። ከዚያም በ1983 ቪንያርድ ሚኒስቲሪ በማለት በፍጥነት ዓለምን ማጥለቅለቅ ጀመረ። አሁን በጣም እየተስፋፋ ያለ እምነት ነው።

- ጴንቴኮስታል አሴምብሊ ኦፍ ዘወርልድ የሚባለውም የተመሠረተው በ1907 ነው። ቀጥሎም ዘአሴምብሊ ኦፍ ጎድ በ1917 ተመሠረተ ። ይህ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ተነገረ እንጂ በየአህጉራቱ ብዙ በተለያየ ስም የሚጠሩ አሉ።

ቀደም ባለው ጊዜ አሴምብሊ ኦፍ ጎድ የተባለው ጴንጤቆስጤ ስለ ሥላሴ መሠረተ እምነት (ዶክትሪን) አልቀበልም ብሎ ነበር ። ጴንጤቆስጤ እምነት ተከታይ በአሜሪካ 10 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል ።

## (፮) ሜጋ ቸርች እና ካልቨሪ ቻፕል

ካልቨሪ ቻፕል አንዱ የጴንጤቆስጤ እምነት ነው። ይህ ካልቨሪ ቻፕል ቻክ ስሚዝ በሚባል ሰው በ1965 ተመሠረተ ። ቦታውም ኮስታ ሜሳ በሚባለው በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ ነው ። ቻክ እስሚዝ በትንሽ ጠባብ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ ወጣቶችን ሰብስቦ ስማደራጀት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማስጠናት ጀመረ። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተከታታዮች አብዛኛው በዕፀ ፋርስ (ጎጂ እጾች) ሱስ የተያዙ፤ ማደሪያ ቤት የሌላቸው፤ የመንገድ ላይ ተዳዳሪዎች ነበሩ።

በ1971 ዐዳዲስ አባላት ተጨምረው በጥቂት ወራቶች የእምነቱ አባል በመኾን ተጠመቁ ። ቀስ እያለ ይህ ስብስብ ቁጥሩ በመጨመር

15.000 ሺ ደረሰ። በተጨማሪ ከአካባቢው በተለያየ የክርስትና እምነት ውስጥ የነበሩ እየገቡ ስለአባዙት "ሜጋ ቸርች" በመባል ይጠራ ጀመር። ሜጋ ማለት ትልቁ ማለት ነው።

ቻክ እስሚዝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዝናው በአሜሪካን ተሰማ። በዙ ወጣቶች ተከተሉት። ከ1971 ጀምሮ በየቦታው ይህን ምሳሌ በመከተል በሰፋት ስብከት መስጠት ተጀመረ። በዚህ በሜጋ ቸርች ብዙዎች የፕሮቴስታንት ቡድኖች ይሳተፉበታል። ሳውዝ ባፕቲስት፣ ኤፒስኮፓል እና ጎድ፣ ኖናዶቅድ ሜተዲስት፣ ካልበሪ ቻፕል ፣ የጴንጤቆስጤ የተለያዩ ቡድኖች እና ሌሎችም ይሳተፉበታል ። በስፖርት ሜዳ ላይ፣ በእስታዲዮም፣ በታላላቅ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ሰፊ ቦታን በመምረጥ ይሰበሰባሉ። በዚህ ስብሰብ ወደ 20 ሺ የሚደርሱ በአንድ ጊዜ የሚገኙበትም ቦታ አለ። ሎስ እንጀለስ፣ ዳላስ፣ አትላንታ፣ ካሊፎርኒያ እና ፍሎሪዳ በከፍተኛ ኹኔታ የተስፋፉበትና የተስፋፉ ያሉባቸው ቦታዎች ናቸው። ሜጋ ቸርች ሰዎችን ለማሰባሰብና ለማሳብ በዙ ጊዜ ቴክኖለጂን በመጠቀም ቅስቀሳ ያደርጋሉ ። በቅጽል ስሙ ዲዝኒ ላንድ እየተባለም ይጠራል ። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የክርስቲያን ባህል አይቀበሉም ።

በአኹኑ ጊዜ በአሜሪካ 1200 የሚደርስ ሜጋ ቸርች አሉ። በማምት 250,000 ሺ አሜሪካውያን ተከታዮች ሲኖሩ ከአሜሪካ ውጭ በኮርያ፣ በብራዚል እና በአፍሪካ በመግባት እየተስፋፉ ይገኛሉ ።

## (፯) ሜትሮፖሊታን ኮምኒቲ ቸርች ።

ይህ የእምነት ስብስብ በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ እና በአውሮፓ እየተስፋፋ የሚገኝ ነው ። ሜትሮፖሊታን ኮሚኒቲ ቸርች ሊሽራል ዲኖምኔሽን ከሚባሉት አንዱ ነው ። ይህም ማለት ምን አለበት ወይም ኃጢአት የለም ከሚሉት አንዱ ክፍል ነው ። የሰዶም ሰዎች ይፈጽሙት እንደነበር የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን የሚፈቅድና የሚያበረታታ የእምነት ድርጅት ነው።

የተጀመረበት ቦታ በአሜሪካ በሎሳ አንጀለስ ጥቅምት 6 ቀን 1968 ነው ። መሥራቹ ሬቨረንድ ትሮይ ፔሪ ይባላል ። ይህ ሜትሮፖሊታን የኮሚኒቲ ቸርች ሲጀመርም 12 ሰዎች ኾነው በቤት በመሰባሰብ ነበር። ወዲያው እንደተጀመረ በአሜሪካ ሕዝብ ከፍተኛ ጥላቻ ደርሶበታል። በኋላ እየተለመደ መጥቶ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባል



እስከመኾን ደርሷል ፤ ቀስ በቀስ በአሜሪካ ግዛቶች መስፋፋቱን ቀጠለ ። በ1980 ላይ በኤድስ በሽታ 6000 ሺ የሚደርሱ የእምነቱ አባላት ተቀስፈዋል ።

መሥራቹ ትሮይ ፔሪ እስከ 2005 ድረስ ቡድኑን በመምራት አገልግሎ ሰጥቷል ። በኋላም በምትኩ ናንሲ ዊልሰን ለመሪነቱ ተመረጠች። የኒው ዮርክ ሜትሮፖሊታን ኮሚኒቲ ቸርች መሪ ሬቨረንድ ፓት ቡመጋርደኔር ይባላል ። በሰዶማዊ ተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ደጋፊ የኾነው ይህ እምነት ከአሜሪካ አልፎ በዓለም እየተዛመተ ነው ። በእንግሊዝ አገር በጣም እየተስፋፋ ያለ የዘመኑ የሰዶም እና የጎሞራ ኃጢአት ልቅ የኾነ እምነት ነው።

ይህ የክርስትና እምነት ተብሎ መጠራቱ እና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባል ኾኖ መቆጠሩ የሚያሳዝን ነው ። ይህ ብዙዎችን እንደሚያሳዝንና የሰው ልጆች እንደ ሰዶምና ጎሞራ የፍርድ ቀን እንደሚጠብቁ የሚያመለክት ነው (ዘፍ. 19፥24 ፤ ሮሜ. 1፥27)። ይህን የሚደግፉ ብዙ የፕሮቴስታንት ቡድኖች አሉ። ይህ ሰዶማዊነት ተግባር በዓለም ላይ መቅሰፍት የሚያስከትል ነው ። አንዱም በሉኹኑ ጊዜ መድኃኒት ያልተገኘለት በሽታ (ኤድስ) የተዛመተው ከዚህ ሰዶማዊ ተግባር የመነጨ በሽታ ነው።

## (፰) ቸርች ኦፍ ሳይንቶሎጂ

ቸርች ኦፍ ሳይንቶሎጂ የተጀመረበት ጊዜ በ1950 በአሜሪካ ነው። የጀመረው ሰው የሳይንስ ልብ ወለድ መጽሐፍ ጸሐፊ የነበረው ኤል ሮን ሐቨርድ በተባለ ሰው ነው ። ይህ ሰው ገንዘብ ማግኛ ዘዴ ይጠቅማል ብሎ ያመነበት እምነት በመፈልሰፉ ስኬታማ ኾነ። ይህም ዋናው የሰውን ባሕርይ ማጥኛ ዘዴ ማጥመጃው ዲኔቲክስ የሚባለው መንገድ ነው ።

ይህ እምነት መነሻ ያደረጋቸው የሕንድ የጣዖት አምልኮ ሃይማኖትን ባህልና የሲግማን ፍሮይድ የፍልስፍና መንገዶችን በመከተል ነው ። በዚህም የሰው ማጥመጃ ዘዴ ገንዘቡን፣ ሀብቱን ኹሉ ስለሚቆጣጠሩ በብዙዎች ዘንድ የማይደገፍ የእምነት ድርጅት ነው።

ሳይንቶሎጂ ማለት ዕውቀትን ወይም እውነትን ማጥናት ማለት ነው ይላሉ። ከአሜሪካ ውጭ ወደ 159 በሚደርሱ አገሮች በመስፋፋቱ ከ8 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች እንዳሉት ይነገራል ።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በብዛት እየተከፋፈሉ የተስፋፉም እን ደኾነ ይነገራል።

## (፪) ፋንዳሜንታሊዝም እና ካራዝማቲክ

አክራሪነት (ፋንዳሜንታሊዝም)[245] ከማንኛውም የክርስትና እምነት ውስጥ ያለ በስሜት ተቀስቅሶ የሚነሳ ቡድን ማለት ነው ። በ1750 ፣ በ1870 እና በ1950 አሜሪካ ወደ ውድቀት እያመራች ነው ፤ የቀድሞ ሃይማኖቷን ባተች ። መሪዎች እና የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች በደሉ የሚሉ ኃይለኛ ሰባኪዎች፤ ተከራካሪዎች ተነስተው ነበር።

ብዙ ጊዜ ይህ የሚከሰተው ከመንፈሳዊ ኮሌጅ ሲወጡ፤ ወይም መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር በማንበብ የብቃት መንፈስ ታይቶ ናል በማለት ብቅ የሚሉ የተሸከሙትን ፣ ያነበቡትን ስለሚዘረግፉት ብዙ ስሚ ያገኛሉ።

የዳርዊን ሓሳብ ከ1925 ጀምሮ በአሜሪካ ትምህርት ቤቶች ሲያጨቃጭቅ እና ሲያስቆጣ የቆየ ነው ። ፋንዳሜንታሊስት ናቸው ተብለው የሚታወቁት ሰዎች የዳርዊን ፅንሰ ሓሳብ እና ዘመናዊነት እም ነትን የሚያጠፉ መኾኑን አጥብቀው ይገልጻሉ።

ፋንዳሜንታሊዝም እንደ ጴንጤቆስጤ በልሳን መናገር የሚባ ለውን አይደግፍም። ይህ ዐይነቱ ለፖለቲካ መጠቀሚያ ነው ይሉታል፤ በልሳን መናገር በሐዋርያት ጊዜ አብሮ አልፏል ይላሉ። ባጠቃላይ ፋን ዳሜንታሊስት ማለት ቀዝቃዛ የኾነውን፤ ምን አለበት የሚለውን ሊበ ራሊዝምን የሚቃወም ነው። የንጉሥ ጀምስ (ኪንግ ጀምስ) መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ትክክል እርማት ያለው ትክክለኛው ነው የሚሉ ናቸው።

ካሪዝማቲክ[246] ሙቭመንት ለዚህ እንደ ምሳሌ ከሚኾንት አንዱ ነው። በ1907 ከላይ የተጠቀሰው በአሜሪካ ሎሳ አንጀለስ ውስጥ የሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን አባል በነበረው በኋላ በአዙዛ እስትሪት የተመሠረተ የጴንጤቆስጤ እምነት አንዱ የካሪዝማቲክ ቡድን ምሳሌ ነው ።

[245] **Fundamentalism** = Protestant movement distinguished by its members' faith in the literal truths and teaching of the Bible.
[246] **Charismatic** = One who believes in demonstrations of *charisma*, Greek for gifts, in reference to gifts of the Holy Spirit.



በተለይም ቪንያርድ ክርስቲያን ፌሎውሽፕ እና በ1980 በተ መሠረተው ካልቨሪ ቻፕል ኦርጋናይዜሽን በተባለው የቅስቀሳ ድርጅት እንዲኹም ክሩሴድ በተባለው የመስበኪያ ዘዴ ከአሜሪካ በመውጣት (ኤክስፖርት) ዓለሙን እያጥለቀለቁት ነው። በተለይም አፍሪካን ምድር ወረውታል ።

በዚህ በልዩ አቀራረብ በተመሠረተው የክራዝማቲክ እምነት ነጭ፣ ጥቁር ፣ ቻይናውያን ፣ ሜክሲካውያን ሳይቀሩ ገብተውበታል ። አንዳን ዶቹ ከነበሩበት የክርስትና እምነት እየወጡ የራሳቸውን ርካሽ በማድረግ ይሰገስጉበታል።

## ምዕራፍ ፲፰
## (፩) የፕሮቴስታንት እምነት በኢትዮጵያ

ቀደም ተብሎ በመግቢያው እንደተገለጸው ካቶሊክ እና ፕሮቴስታንት ምዕራባውያን በመባል ሲጠሩ ኖረዋል ። ዛሬ ግን ነጮች እየናቁ እየተ ዋቸው የመጡት የፕሮቴስታንት ድርጅቶች ከአሜሪካ እና ከአውሮፖ ተጉዘው ወደ አፍሪካ በገፍ እየገቡ ነው ። ከነዚህም አንዷ ተቀባይ ኢትዮጵያ ነች ። ይህ የፕሮቴስታንት ቡድን በተለያዩ የአገሪቷ ክፍል ገጠር እና ከተማ የብዙ ብዙ የሚኾኑ የምዕራባውያን የፕሮቴስታንት የእምነት ዝርያዎች ገብተውባታል። እነዚህም ከላይ የተጠቀሱት ፤ የዮህዋ ምስክርነት (የጂሆቫህ ዊትነስ) ፤ ፕርስቤተርያን፣ ባፕቲስት ፣ ሜተዲስት፣ ሜኖናይት ፣ ሞርሞን ፣ ጴንጤቆስጤ ፣ የሰባተኛው ቀን አክባሪ (አድቬንቲስት) ኤጲስቆፖልያን፣ ዩኒቴሪያን ፣ አንግሊካን፣ ዲሳ ይፕል ኦፍ ክራይስት፣ ክርስቲያን ፊሎሽፕ ፣ ባይንቶሎጂና ሉተራን ሌሎችም በመግባታቸው ኢትዮጵያ የነዚህ ኹሉ መናኸሪያ ኾናለች።

በታሪክ የፕሮቴስታንት እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው። በመጀመሪያ በሳሙኤል ጎባት ከእንግ ሊዝ በ1850 ፤ ከዚያም በጀርመናዊው ሊዊስ ክራፕፍ በ1856 ነው።

ሌላው ታሪክ በ1874 ወደ ጀርመርን በባርነት የተወሰደው የቀ ድሞ ስሙ ነሲቡ የተባለው ሰው የባርነት ሥርዓት ነጻነት በአውሮፓ ሲታወጅ እሱም ነጻነቱን አገኘ ። በጀርመን ሉተራውያን ተጠምቆ አናሲሞስ የሚል ስም ተሰጠው ።

አናሲሞስ የሚለው ስሙ የተወሰደው ከቅዱስ ጳውሎስ መል እክት ከፊልሞና (ፊሊ. ም.1፥12) ነው። በዚህ በቅዱስ ጳውሎስ መል እክት ላይ ያለው አናሲሞስ አገልጋይ ነበረና እነሱም ባርያችን ነበርክ

ለማስቶ አናሲሞስ አሉት ። ከጀርመናውያንና ከስዊድናውያን የተማረውን የፕሮቴስታንት (ሉተራዊ) እምነት ከሌሎች በባርነት ከተወሰዱት ጋር ከስዊድናውያን ሚሽነሪ ሶሳይቲ ጋር በመኾን ያስፋፉ ጀመረ። በመጀመሪያ በአስመራ ከተማ አጠገብ ገለብ በሚባለው አውራጃ የስዊድን የወንጌል መልእክተኞች (ሚስዮን) መጠለያ ጣቢያ ብዙ ወጣቶች ይኖሩ ነበር። የቦታው ስም ባሴል የሚስዮናውያን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት (Church Missionary Society) ይባላል ። የነዚህ የሚሲዮናውያን ዓላማ ከስብከቱ ጀርባ ኢትዮጵያን ለቅኝ ገዢዎች ለማመቻቸት ጭምር እንጂ ወንጌልን ለማስተማር ብቻ እንዳልተሰማሩ የታወቀ ነው።

አናሲሞስ የሉተራውያን ተቀባይ አገሮች ወደኾነችው ስዊድን ኼዶ ከፍተኛ ትምህርቱን አጠናቀቀ። ከዚያም በወለጋ የፕሮቴስታንትን እምነትን ከአስቴር ገኖ ጋራ በመኾን ማስፋፋት ጀመሩ ። አናሲሞስ የሚያስመሰግነው እምኩሎን በተባለ ቦታ ኾኖ የጥንታዊውን መሠረታዊውን የግእዝ ፊደል በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ መተርጐሙ ነው ። የማያስመሰግነው ደግሞ የሉተርን መጽሐፍ ወደ ኦሮምኛ በላቲን ፊደል የተረጐመው ነው ። በዚህም የተነሳ ጀርመኖች በላቲን ቋንቋ የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት ሲያዘጋጁ ቆይተው ዛሬ በዘመናችን ጊዜ ሲፈቅድላቸው በተባባሪዎቻቸው አማካኝነት በተኑት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዋሐደ ሕዝብ ነው። ዐማርኛ፣ ትግሪኛ፣ ጉራግኛ፣ ከንባትኛ፣ ወላሞኛ ተናጋሪዎች ጭምር ተዋሕዶ ፣ ተዋልዶ አንድነቱን ጠብቆ የሚኖርባት አገር ነች እንጂ የላቲን ተናጋሪው ሕዝብ አይደለም ። ይህ ኾን ተብሎ ለመከፋፈል የተደረገ መኾኑን ምንም ጥርጥር የለውም ። የሚቀርበው የፖለቲካ ምክንያት ለፖለቲከኞች እንደኾነ የታወቀ ነው ። ለዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመከፋፈል ኾን ተብሎ የታቀደው የምዕራባውያን ሚሺን የላቲን ቋንቋ ፊደል የኢትዮጵያ የኦሮሞ ፊደል ነው ለሚለው የረዥም ጊዜ እቅድ መሳከት መንገድ ከፈተ ። ይህም የጀርመንን ሚሽን ተቀብሎ ብሔራዊ የኢትዮጵያን የግእዝ ፊደልን መለወጥ የተዋሐደውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያኮራ ሳይኾን የሚያሳፍር ነው።

ከላይ እንደተገለጸው ቀደም ሲል ጀምሮ ጀርመናውያን ፣ እስካንዲኔቪያውያን፣ አሜሪካውያን እና ካናዳውያን ሚሲዮኖች የፕሮቴስታንት ቡድኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ስብከታቸውን ገፉበት። በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ በማለት ሲኖዶስ መሠረቱ ። በ1974



የሰሜኑ ኢትዮጵያ ክፍል እንደተለመደው በአሜሪካ ሉተራን ሚሽን[247] በድርቅ የደረሰውን ረሀብ ምክንያት በማድረግ የተዋሐደው የሰሜኑ ሲኖዶስ በማለት መሠረቱ። በኋላም ልክ እንደ አሜሪካኑ የመስበኪያ ዘዴ፤ ከምፓስ ክሩሴድ ፎር ክራይስት ብሚለው ድርጅት ሥር የሚስፋፋው የጴንጤቆስጤ ቡድን ቅርጫፍ እየመሠረቱ «ዘመቻ ፊልጶስ»፤ «የጽድቅ ፀሐይ» እያሉ ድርጅቶችን ያስፋፉ ጀመር። ችግረኞችን በችግራቸው በመግባት በተለይ በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ዘለቄታዊ ችግርን የማያስወግድ የዕለት ኑሮ መደለያ ስኳር፣ ብስኩት፣ ዱቄትና ያረጀ ልብስ በመስጠት፤ በከተማ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሥራ ያፈቱ ወጣቶችን በመደለል የሚያጠምዷቸው በዙዎችን ነው።

ከቅርብ ዓመታት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ኦርቶ ጴንጤ የሚል ተጀምሯል ። ይህም መልኩን ለወጥ አድርጎ ግራ የተጋቡት ከቀድሞ እምነታቸው ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የነበሩት ዐዲስ አማኒ ፓስተሮች የፈጠሩት ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ባህልና ሥርዓት እከተላለሁ ነገር ግን ማደስ አለብኝ የሚል አመለካከት አለው ። የያሬድን ዜማ ለመዘመር በመሞከር ፤ ጫማ አውልቆ ወደ ጸሎት ቤት መግባት ፣ በልሳን መናገር የሚባለውን በመተው ሌሎችንም ለማድረግ ሙከራ እየተደረገ ነው።

በዚህ መልኩ ባለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት የተለያዩ ፕሮቴስታንት ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ከአውሮፓና ከአሜሪካ በብዛት ገብተዋል። ከእነዚህ የፕሮቴስታንት ክፍሎች ጥቂቶቹ ኦርቶዶክስን በማጥላላት የስሕተት ሃይማኖት እንደ ኾነ አድርገው የሚያቀርቡናቸው።

## (፮) በአሜሪካ ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንት

በአሜሪካ አገር አትላንታ ግዛት ነዋሪ የኾኑት ኢትዮጵያዊ ፓስተር በአንድ ወቅት በስብከታቸው ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያደረሱት ነቀፌታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኒያንን ብዙዎችን አሳዝኗል ። ከአንድ ኢትዮጵያዊ በማይጠበቅ ነቀፌታ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትናን ሃይማኖት በማናናቅ እንዲሁ ለማዋረድ በመሞከሩ በአሜሪካ ነዋሪ የኾኑትን እና ከዚያም በኢትዮጵያ ያሉትን ኦርቶዶክሳውያን አማኒያን ኹሉ አሳዘነ ። በሳቸው አመለካከት ይሉት የነ

[247] John Gay Y. Christianity In Ethiopia and Eritrea 1998 Amman Jordan

በረው ኦርቶዶክስ የጨለማ ዘመን ነው፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አታማልድም ፤ ጻድቃን በማዕታት አይማልዱም ፤ ሌላም ብዙ ጸያፍ በመናገር እንዲጠላ ያማድረግ ፤ የማንቋሸሽ ንግግር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማንያንን አበሳጩ ። የፕሮቴስታንት እምነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ጸረ ማሪያሞች (ጠረ ማርያም) ተብለው በመጠራት ይታወቃሉ።

የፕሮቴስታንት ትምህርት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ማደሪያ ብቻ ናት ብለው ያስተምራሉ፤ ወላዲተ አምላክ ወይም የአምላክ እናት የሚለውን መናገር አይፈቅዱም ። የቃል ሥጋ ኾነ (ዮሐ. 1፥18) ምስጢር የቅዱስ ቄርሎስን ትርጉም እና ትንታኔ ለመረዳት የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለማወቅ ፍቃደኞች አይኾኑም ። ቃል ሥጋ ኾነ የሚለውን ሲተረጒሙት በተዋሕዶ ሳይኾን። በሕድረት የስሕተት ትምህርት ላይ ያተኩራሉ ። ስለዚህ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጉዳይ ክልተማሩት በሚገባ ካላጠኑት ብዙ አይገባቸውም።[248] ቢገባቸውም በጀመሩት መግፋት ስለሚፈልጉ መለወጡ ይከብዳቸዋል፤ ስለዚህ በአኹኑ ጊዜ ከላይ እንደተገለጸው አንዳንዶችም መልኩን ለወጥ አድርገው ኦርቶ-ጴንጤ በማለት በዐዲስ መንገድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት እየተከተልን ነው የሚሉም አሉ ።

በአሜሪካ ኢትዮጵያውያን ጰንጤቆስጤዎች በየግዛቱ ተስፋፍተዋል። በዋሽንግተን ዲ. ሲ. በገዳመ ተክለ ሃይማኖት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር እና በክሣቴ ብርሃን በሌሎችም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ራዲዮ ማሠራጫ የሰብከተ ወንጌል በመስፋፋቱና በመስጠቱ ኮብልለው የነበሩት ኹሉ በመመለስ ላይ ናቸው ። ከውስጣቸው እየወጡ ያሉ ብዙዎች ናቸው።

የራሳቸውን የኦርቶዶክስ እምነት ባለመረዳት የነጐዱ በኋላ ደግሞ እውነቱን የቱ እንደኾነ ሲረዱ ወደ ቀደመው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸው በመመለስ ንሥሐ የገቡ ብዙዎች ናቸው ። የዚህ የመመለስ ጉዳይ ያሳሰባቸው ታዋቂው የጴንጤቆስጤ ፓስተር በስብከታቸው ስድብን እና ማንቋሸሽን እንደ ዋነኛ የስብከታቸው መሣሪያ መንገድ አድርገው መያዛቸው ነበር ፤ ይህ ግን ስሕተት ነው።

[248] ብርሃኑ ብሥራት (መ. ብ.)፤ ፍኖተ ኦርቶዶክስ ዘተዋሕዶ።



# ምዕራፍ ፲፱

## አሜሪካውያን ወደ ኦርቶዶክስ መመለስ

የካቲት 15 ቀን 1987 በካሊፎርኒያ በሎሳ አንጀለስ በአንጾክያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ቀን 60 የፕሮቴስታንት ፓስተሮች እና ዲያቆኖች እንዲሁም 200 ምእመናንን ጨምሮ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነች በማለት ከነበሩበት ከካሪዝማቲክ፣ ካምፓስ ክሩሴድ ፎር ክራይስት ፣ ከቬን ያርድ ፌሎውሺፕ፣ ኢቫንጀሊካል ፍሪ ቸርች፣ ባፕቲስት ሚሽነሪ፣ ከአንግሊካን፣ ከኤፒስኮፓል፣ ከሉተራን፣ ከሜተዲስትና ከፕሬስቤተሪያን እየወጡ ወደ ኦርቶዶክስ ክርስትና እየተጠመቁ ብዙዎች ገቡ።[249]

እነዚህ ሰዎች ከተለያየ የፕሮቴስታንት ክፍል የመሪነትን ቦታ ይዘው የነበሩ ናቸው። አንዳንዶቹም ካምፓስ ክሩሴድ ፎር ክራይስት በሚባለው ድርጅት ውስጥ ኮከብ ኾነው ይመሩ የነበሩ ናቸው ። ይህ ካምፓስ ክሩሴድ ፎር ክራይስት የተባለው ወደ ኦርቶዶክስ ብዙዎቹ በመግባታቸው የጴንጤቆስጤ ድርጅትን አስደንግጦታል። እነዚህ የነገረ መለኮት ሊቃውንት የተባሉት የፕሮቴስታንት ምሁራን በቀጥታ ወደ መጀመሪያዊቷ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ የቀሩትን በጣም አወያየ።

### (፩) ፋዘር ፒተር ኢ. ጊልክስት

የቀድሞ የሉተራን ፓስተር በኋላ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ቄስ እንዲህ ይላሉ "ከረዥም አሽጋሪ ጉዞ በኋላ የፕሮቴስታንት የወንጌል ሰባኪዎች በመጨረሻ የቤታቸውን መንገድ አገኙ፤ ይህም መንገድ ኦርቶዶክስ ነው።" በማለት ከላይ የተገለጸውን በ1987 የተከሰተውን ይህን ወደ ኦርቶዶክስ የተመለሱትን ኦርቶዶክስ መኾን (BECOMING ORTHODOX) በሚል መጽሐፋቸው ጻፉት።

አሜሪካ የኦርቶዶክስ አገር መኾን አለባት በማለት ከተነሳሱት ውስጥ አንዱ የፕሮቴስታንት ተከታይ ናቸው። እኚህ ሰው የታወቁ የፕሮቴስታንት ሰባኪ እንዲሁም የካምፐ ክሩሴድ ሪጅናል ዳይሬክተርና መሥራች ነበሩ። ባንድ ወቅት እነዚህ የተለያዩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን መሪዎች ተወጣትተው ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማጥናት

[249] **Peter E. Gillquist** *Becoming orthodox California 1992 p. vii*

ጀመሩ ። ከብዙ ጊዜ ክርክርና ጭቅጭቅ በኋላ በሐዋርያት የተመሠረተችውን ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክስ፤ ሥርዓቷን፣ እምነቷን ጠብቃ የኖረች ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት የወረደ ሥልጣነ ክህነት ጳጳሳት በአንብሮተ እድ እንደ ተቀበለች ይህም ያልተቋረጠ መኾኑን ደረሱበት።

ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዋና እና አስፈላጊ መሪዎች መኾናቸውን፤ እንዲሁ ከክርስቶስ ወደ ሐዋርያት ከዚያም በአንብሮተ እድ ከሐዋርያት ወደ ተከታዮች ሲተላለፍ የነበረ መኾኑን በመረዳታቸው እውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያን አግኝተናል አሉ ። ብዙ የፕሮቴስታንት ተከታዮች ስለመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የሚያውቁት ታሪክ የለም። በዚህና በመሳሰለው ምክንያት አሜሪካንን ኦርቶዶክስ ማድረግ አለብን ብለው ወሰኑ። አልቀረም ምእመናኖቻቸውን ይዘው በአንጾኪያ ኦርቶዶክስ፣ በሩስያ ኦርቶዶክስ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስ፣ በአርሜንያን ኦርቶዶክስ ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ በሌሎችም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ብዙዎች ገቡ።

ፋዘር ፒተር ጊልክስት በአኹኑ ጊዜ ስለ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት እና ታሪካዊነት በመመስከር ላይ ይገኛሉ። ወደ አንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከገቡ በኋላ 32 ዐዳዲስ አብያተ ክርስቲያን የከፈቱ ሲኾን ከስድስት ሺ ዐምስት መቶ በላይ የኾኑ የአሜሪካ ፕሮቴስታንቶችን ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጥምቀው መልሰዋል።

## (፪) ቤነዲክት (አባ ዮሐንስ)

አባ ዮሐንስ የቀድሞ ስማቸው ቤነዲክት የአሜሪካ ዜጋ ናቸው ፤ ቅድመ አያቶቻቸው ከጀርመን የፈለሱ ከፕሮቴስታንት ክፍል የነባሩ ሲኾን አባቸው ግን የካቶሊክ የቤንት ቤነዲክት ገዳም መነኩሴ ኾነው በገዳም ይኖሩ ነበር ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሚገባ ያጠኑ አዋቂ ሰው ናቸው። ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በገቡ ጊዜ በጽሑፍ የሰጡኝን አስፍሬአለሁ። ለምእመናን በአውደ ምሕረት ከተናገሩት ውስጥ በጥቂቱ ይህን ይመስል ነበር ።

> ወደዚች ወደ ክርስቶስ የቀረበች ቤተ ክርስቲያን ከምእመኖቼ ጋራ ለመግባት ወሰኛለኹ ። ይህችም ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን ከወረደላቸው በኋላ ፤ በኢትዮጵያው ጃንደረባ ጥምቀተ ክርስትናን የተቀበለች ፤ ወደ ክር



> ስቶስ ትምህርት የተጠጋች፤ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መኮኗን በቂ ግንዛቤ፣ ዕውቀትና ትምህርት አግኝቻለሁ።

በማለት በውስጥዋ ገብተው ተጠመቁ፤ ምንኩስና ከዚያም የቅስና ሥልጣነ ክህነት ተሰጥቷቸው አገልገሎት ቀጠሉ። በአኹኑ ጊዜ በኦርቶዶክሳዊ ሥርዓተ አምልኮት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

እንደ እሳቸውም በብፁዕ አቡነ ይሥሐቅ በሌሎቹም ሊቃነ ጳጳሳትና የቅስና ማዕረገ ክህነት የተሰጣቸው ብዙዎች አሉ ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ቄስ ዴቪድ ጀሊ ይባላሉ። እኝህም በካንሳስ ኪዳነ ምሕረት፣ በዳላስ ሚካኤል እና በዋሽንግተን ማርያም በሌሎችም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት እየተገኙ አገልግሎት ከሚሰጡት አንዱ ናቸው። ጥምቀተ ክርስትና ተጠምቀው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቷ የገቡ ብዙዎች ናቸው።

### *ABBA YOHANNES*

I was born on October 22, 1960 in Pontiac, Michigan the first of two sons to John Edward and Katharine Spehar. I grew up in the communities of Pontiac and Waterford, Michigan, which are suburbs of Detroit. During the summers my mother, brother and I went to my maternal grandparents large dairy farm in Northern Michigan, where we worked the entire summer; so I experienced both city and country life.

After graduating from High School I attended College in Ann Arbor Michigan in order to be able to teach at Secondary Education level. After teaching in a large Parochial School (K-8 grades) in Detroit for a number of years, I moved to Arizona.

In 1986 I entered the Monastic Life within the Latin Church and was tonsured a monk of the Benedictine Order under the name of Francis Benedict. I received my theological education in Holy Incarnation Monastery and St. Paul's Seminary as well as with the Society of Jesus, (Jesuits) a Catholic Religious Order of men.

In July of 1987 I was ordained a Deacon and a year later ordained to the priesthood in the Catholic Church; I continued to live in the monastery as a monk who was also a priest. In March of 1990 I was approached by a group of men (some clergy) who had serious concerns with the Catholic Church being faithful in her teaching of the Ancient Apostolic faith. This prompted us all to do an in depth study of the historical Church founded at Pentecost. Our conclusions led us to the

Orthodox Church and in particular to the most ancient of these Churches, the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church.

About four years ago I had the great fortune to meet Father David Jolly, who is a Priest of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church. He introduced me to Kesis Asteraye and Abba Thomas of the Ethiopian Church in Kansas City, Kansas. There I received instruction in the faith, history and traditions of the Ethiopian Church. During a three-year friendship Kesis Asteraye, Father David and Abba Thomas introduced me to His Eminence, Abune Yeshaque, who has been a very concerned Spiritual father in my search.

After having been received into the EOTC and ordained to the Priesthood, I feel what must have been the same excitement felt at Pentecost. With the help of the Holy Spirit and through your prayers and encouragement I hope to bring the Ancient and Apostolic faith as professed by the EOTC to my fellow Americans who have long been in darkness.

After Pentecost the Holy Gospel of the Lord Jesus burned across three continents. Let us all pray that the Holy Spirit who breathed upon the Apostles on that day may through the EOTC breath the Orthodox faith upon the hearts, minds and souls of our fellow Americans.

Seeking your prayers of intercession before Our Lord Jesus Christ and His Holy Mother Mary.

**Abba Yohannes – June 14, 2004**

## (፫) ወጣት ታንያ

**ይህች ወጣት ዝርያቸው ከእንግሊዝ ቤተሰብ የኾነ ካቶሊክ እምነት ሥር ያደገች ነች።**

**እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መኾኗን ተረድቻለኹ ። የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ታሪክ ፤ ኢትዮጵያን በመጽሐፍ ቅዱስ ያላትን ታሪክ አንብቤያለኹ። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን መኾኗን ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪኳንና የገዳም ታሪኳን ተረድቻለሁ። እኔም ኾንኩ ብዙ ጓደኞቼ ይህችን ቤተክርስቲያን ስንፈልጋት ኖረናል። አኹንም ብዙዎች እየፈለጓት ነው። በማለት ቤተ ክርስቲያን ባለማቋረጥ ማስቀድስ ጀመረች። የቤተ ክርስቲያኒቷን ባህልና ሥርዓት፣ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን) ተማረች ። ከዚያ የትንሣኤ ዕለት ሚያዚያ 23 ቀን 1997**



**ዓ. ም. (ግንቦት 1 ቀን 2005) በቦልቲሞር ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተጠመቀች።**

**<u>The simple thoughts that cross my mind when one asks, why I am here.</u>**

My name is Tanya; I am 24 years of age, born and raised in Baltimore, Maryland with a Catholic background. Due to my independent spiritual nature, my life began to grow. At the age of 22 I bought my own house, a lot of my time is spent gardening, reading, and listening to music. These past times helped me to meditate upon what I really seek in life; true happiness. What else is there? I mean, all good things lead to happiness, even love is happiness. But more than that, I as a created human being have roots. I will better find myself when I find my roots. Life is more than what is here and now. Life started long ago, and from the very first seed that God planted, there is the beginning of my family tree. This is family to me. This is life.

Reading the scriptures has brought me closer to reality than ever before. Not necessarily reading about the lives of the people, but rather, seeking God's message in every story mentioned. My life is spent seeking out the hidden truths, in turn just making life make sense. Now, I could truly go on and on about how I got here, but the important thing is, why I am still here. By here I mean the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church. Church meaning a dwelling for God, Tewahedo meaning God in the flesh, Orthodox meaning the right belief, and Ethiopian because it is the oldest most unchanged and righteous Christian way.

I started my journey with Faith, knowing the existence of God. God created me, and for this, I love God, and will follow in his right ways. Following this righteous path is what makes me whole; this is what truly makes me happy. ..........................

Now that that is said and done, I must add just a few things. My orthodox name is Fikirta Sellasie, this means the love of the trinity. I also have a great love for the land of Ethiopia that I see as a very sacred land that is mentioned in the scriptures time and time again. Also from Ethiopia there was born a great leader by the name of Haile Sellasie I.

**TANYA (FIKRTA SILLASIE) May 2005**

## ምዕራፍ ፳
## ማጠቃለያ በፍጻሜ ዘመን

በአሜሪካ እስከ አኹን ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የገቡ ብዙዎች እንደኾኑ የታወቀ ነው ። የክርስትና እምነት በመጀመሪያ የተሰበከው በአፍሪካ ምድር በኢትዮጵያ ነው ። ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት አምላክ እስራኤል እያለች ታመልክ የነበረች ትንቢት የተነገረላት አገር ነች (መዝ. 67፥68) ። ጥምቀተ ክርስትናም የተሰበከባትም በሐዋርያት ዘመን ነው (የሐ ሥራ 8፥26-39)። ይህች ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳን ጊዜያዊ የአስተዳደር ችግሮች ቢኖሩባትም በአሜሪካ አገር እና በሌሎቹም አህጉራት እየተስፋፋች በክርስትና አማንያንም ቁጥር ብዛት የበላይነቷን እየያዘች ነው።

በአፍሪካን አሜሪካንና የካርቢያን ተወላጆች ከቀደም ጀምሮ ኦርቶዶክስን ተዋሕዶን ሲፈልጉ መኖራቸው የታወቀ ነው ። በፔንሲልቫንያ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ያሉት ምእመናን እና የያሬድ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንደምሳሌነት ሊጠቀሱ ይገባል። ይህ ሰንበት ትምህርት ቤት በአሜሪካ ተወልደው ባደጉ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ በኾነ ወጣቶች የተመሠረተ ነው። አርአያነታቸው የሚደነቅ ነው።

ይህች ታላቅና ታሪካዊ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እየለቀቁ በየጊዜው ሥርዓቱና የነገረ መለኮት ትምህርቱ (ቀኖናው እና ዶግማው) የሚለዋወጠውን፤ አውሮፓ እና አሜሪካ በቅርቡ በመጨረሻው ዘመን የተፈለሰፉትን እና የተወለዱትን የራስ ለማድረግ የሚሞክሩትን እና የሚጥሩትን የምንመክረው እውነተኛውን ታሪክ መርምረው መንገዳቸውን እንዲያስተካክሉ ነው። አፍሪካን አሜሪካን ወገኖች ቅድመ አያቶቻቸው አፍሪካውያን የነበሩበትን እየፈለጉ ባሉበት ሰዓት በራሱ ባህልና ሃይማኖት የማይከራ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ምን አይነት ኢትዮጵያዊነት መስያ እንደሚያስተላልፍ መገመቱ ያዳግታል። ሃይማኖታችንን ስንንቅ ፕሮቴስታንትን ስንፈልግ መታየቱ ለትዝብት ይዳርጋል።

አሜሪካ ሰፍረው ስለሚኖሩትና እንዲሁም በዓለም ውስጥ ስለሚገኙት ታሪካዊ የክርስትና እምነት አመጣጥ በከፊል አውስተናል።

አሜሪካ ኮሎምበስ በ1492 ካገኛት ጊዜ ጀምሮ ያለው ዘመን ከሌላው ዓለም ሲወዳደር በጣም አጭር ዘመን ነው ። በዚህ ዘመናት



ውስጥ ብዙ ነገሮች በፈጣን ኹኔታ ተለዋውጠዋል ። በክርስትና ሃይማኖት የጀርመናዊው ሉተር እና ካልቪን ሌሎችም የተሐድሶ ሃይማኖት ያስከተለው ፖለቲካዊ ጉዞ ጉዳቱም ጥቅሙም ታይቷል ። ይህም የፕሮቴስታንት የክርስትና እምነት በቡድን እየተከፋፈለ ቁጥሩ በብዛት የተፈጠረበት ይህ ዘመን መኾኑ ታይቷል ። ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን በመውረር ፣ ከዚያም ሰውን እንደ ዕቃ በመግዛት እና በመሸጥ (የባርነት ሥርዓት)፥ ካፒታሊዝም ደህና ሀብታም እንደ ሰማይ ርቀት ተራርቀው የሚኖርበት የከፍተኛ የስደት ዘመን መኾኑ ግንዛቤን ተገኝቷል።

እንደሚታወቀው አሜሪካ ጉልበቷ በሳይንስ ላይ የተመሠረተው ቴክኖሎጂና ኢኮኖሚዋ ነው ። ይህም ጉልበት ዓለምን እየመራ ሲኾን ፥ በአኹኑ ጊዜ ግን እየዋዠቀ ነው ። ይህም ሌላው አሳሳቢ የዓለም ችግር ነው። በአሜሪካ ያሉት የክርስትና እምነቶች በየጊዜው በሐሳብ የሚለያዩ የሚከፋፈሉ ናቸው ፤ ያም ብቻ አይደለም ኢአማንያን (atheist) በዝተውባታል ፤ የእስልምና አክራሪ ቡድኖችም እየተፈጠሩባት ነው ።

ይህ ዘመን ብዙዎች የፍጻሜ ዘመን መኾኑን ይናገሩታል ። የአውሮፓው ትንቢት ተናጋሪ የተናገረው ትንቢቱ ተፈጽሞለታል የሚሉት ኖስትራዳሞስ የሚባለው ሰው፤ እንዲሁ ሌሎች የእምነት ድርጅቶች በተለያየ መልክ እና አተረጓጎም የመጨረሻው ዘመን ነው በማለት ይናገሩታል።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ስምንተኛው ሺ ገብቷል ይባላል ። ይህም ያለምክንያት የተነገረ አይደለም፤ ዐመፃ፣ የፍቅር መቀዝቀዝ ፣ የመንግሥት ወንጌል በዓለም መሰበክ፣ የእምነት መጥፋት እና መቀዝቀዝ። ምልክቶች በግልጽ የሚታዩበት ጊዜ ስለኾነ የማንም ምስክርነት አያሻም።

ለመቆጣጠር ያልተቻለ የአዞን ሌየር (የምድር አየር መሳሳት)፣ የምድር በየቦታው መነዋወጥ (ትሱናሚ)፣ የኒኩሊየር ቦምብ (ማስ ዲስትራክሽን) ፣ በሽታ (ኤድስ) ጄነቲካል ኢንጂነሪንግ (ተፈጥሮ በሰው ሰራሽ መበረዝ) ፣ ሰዶማዊ ጋብቻ፣ ፅንስ ማፍረስ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ መብዛት፣ ሕይወትን በመምራት ላይ ያለው የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ውጥረት ሌሎችም እነዚህ ኹሉ የዘመኑ ችግሮች ናቸው። ከዐርባና ከሃምሳ ዓመታት በፊት አብዛኛዎቹ የሌሉና የማይታወቁ ነገሮችም ነበሩ። የምጥ ጣር መጀመሪያ የተባለው ይህ ይኾን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል

ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ ይህን እወቅ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይኾናሉ ፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች ፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የኾነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይኾናሉ ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል (2ኛ ጢሞ. 3፥1-5) ።

ይህም ስለተባለ ተስፋ መቁረጥ ተገቢ አይደለም ። ተስፋ መቁረጥ ኃጢአት ነው። በእምነት፣ በሰላም፣ በፍቅር ጸንቶ መኖር ያስፈልጋል። ምንም እንኳን ስለ ምጽአት ቢነገረም ፤ ጊዜው ደርሷል እያሉ ሥራን በመፍታት ጊዜን ማጥፋት አንዱ ኃጢአት መኾኑን በማመን ዘመኑን በመከተል በመማር ፣ በዚህ መጽሐፍ መቅድም እንደተገለጸው ትውልዱን በማስተማር ፤ የትውልዱን ጥያቄዎችና ፍላጎት የሚመልስ መጽሐፍ በማዘጋጀት ፤ በማንኛውም መንገድ ሥራን እየሠሩ ፤ አገርን እያለሙ ፣ ወገንን ዕየረዱ ፤ በሰላም መኖር ያስፈልጋል ።

ዓለም እንደ አንድ መንደር በተቆጠረችበት ዘመን ፥ ከቴክኖሎጂው ምጥቀት የተነሳ ተሰውሮ የኖረው ነገር ኹሉ እየተገለጠ የመጣበት ዘመን ስለኾነ ትውልዱ በመማር ከዚህ ጋር አብሮ መራመድ እና መጓዝ ያለበት መኾኑ የግድ ነው።

በተጨማሪም ወደ እውነተኛ የመጀመሪያዋ የክርስትና መሠረት የኾነችውን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ሥር ገብቶ በጸሎት ተግቶ፣ በእምነት ጸንቶ መኖር ፤ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው ፤ ይህንም ብዙዎች ተናግረውታል።

ባጠቃላይ ኑሮ እና ክርስትና በአሜሪካ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ነው።

አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር
ክብር ምስጋና ይግባው። አሜን!




## የአሜሪካ ግዛቶች እና ከተሞች ክርታ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ዋሽንግተን | ዲሲ | DC |
| 2. | አላባማ | ሞንቶ ጎሞሪ | AL |
| 3. | አላስካ | ጁንኡ | AK |
| 4. | አሪዞና | ፊኒክስ | AZ |
| 5. | አርካንሳስ | ሊትል ሮክ | AR |
| 6. | ካሊፎርንያ | ሳክራሜንቶ | CA |
| 7. | ኮሎራዶ | ዴንቨር | CO |
| 8. | ከነክቲኬት | ሀርትፎርድ | CT |
| 9. | ደላዌር | ዶቨር | DE |
| 10. | ፍሎሪዳ | ታለሀሲ | FL |
| 11. | ጆርጂያ | አትላንታ | GA |
| 12. | ሀዋዪ | ሆኖሉሉ | HI |
| 13. | ኢዳሆ | ቦይዚ | ID |
| 14. | ኢልኖይስ | እስፐሪንግ ፊልድ | IL |
| 15. | ኢንዲያና | ኢንዲያናፖሊስ | IN |
| 16. | አዮዋ | ደሞኝ | IA |
| 17. | ካንሳስ | ቶፕካ | KS |
| 18. | ኬንታኪ | ፍራንክፈርት | KY |
| 19. | ሉዊዚያና | ባተንሩዥ | LA |
| 20. | ማሳቹሴትስ | ቦስተን | MA |
| 21. | ሜይን | አጉስታ | ME |
| 22. | ሜሪ ላንድ | አናፖሊስ | MD |
| 23. | ሚቺጋን | ላንሲንግ | MI |
| 24. | ሚኒሶታ | ሴንት ፖል | MN |
| 25. | ሚሲሲፒ | ጃክሰን | MS |
| 26. | ሚዙሪ | ጀፈርሰን ሲቲ | MO |
| 27. | ሞንታና | ሄሊና | MT |
| 28. | ኔብራስካ | ሊንከን | NE |
| 29. | ኔቫዳ | ካርሶን ሲቲ | NV |
| 30. | ኒው ሀምፕሸር | ኮንኮርድ | NH |
| 31. | ኒው ጀርሲ | ተሬንቶን | NJ |
| 32. | ኒው ሜክሲኮ | ሳንታፌን | NM |
| 33. | ኒው ዮርክ | ባፋሎ | NY |
| 34. | ኖርዝ ካሮላይና | ራሌየህ | NC |
| 35. | ኖርዝ ዳኮታ | ቢስማርክ | ND |
| 36. | ኦሃዮ | ኮሎምበስ ሲንሲናቲ | OH |
| 37. | ኦክሎሆማ | ኦክሎሆማ ሲቲ | OK |
| 38. | ኦሬጎን | ሳሊም | OR |

| | | |
|---|---|---|
| 39. ፔንሲልቫንያ | ሀሪስበርግ | PA |
| 40. ሮዴ አይላንድ | ፕሮቪደንስ | RI |
| 41. ሳውዝ ካሮላይና | ኮሎምቢያ | SC |
| 42. ሳውዝ ዳኮታ | ፒይሬ | SD |
| 43. ቴንነሲ | ናሽቪል | TN |
| 44. ቴክሳስ | ሂዩስተን | TX |
| 45. ዩታ | ሶል ሌክ ሲቲ | UT |
| 46. ቬርሞንት | ሞንት ፒለር | VT |
| 47. ቨርጂንያ | ሪችመንድ | VA |
| 48. ዋሸንግተን | ኦሎፒያ | WA |
| 49. ዌስት በርጂንያ | ቻርለስ ታውን | WV |
| 50. ዊስኮንሰን | ማዲሰን | WI |
| 51. ዋዮሚንግ | ቺየኒ | WY |





ካፒቶል




ዋይት ሀውስ





ዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ
በየዘመናቱ የተዋሐዱት ክፍለ ሀገሮች ።





## ዋቢ የኾኑ መጽሐፍት
## Bibliography


1. **Alan C. McLean** *Martin Luther King Oxford University Press 2001*
2. **Albert J. Altschul,** *Wade in the River, the story of the African ch. Faith USA Kansas City 2001*
3. **Alison Baxter** *The USA Oxford 2001*
4. **Applewood Books** *The declaration of Independence Bedford MA USA1996*
5. **Arch Bishop Yesehaq** *The Ethiopian O. Tewahedo church New York 1989*
6. **Bill Adler** *The Quotable George W. Bush USA 2004*
7. **Coretta Scott King** *The words of Martin Luther king, Jr. USA*
8. **David Ewing Duncan** *The Calendar London 1988*
9. **David Mauk and John Oakland** *American Civilization an introduction USA1997*
10. **Earle E. Cairns** *Christianity in the United States Chicago 1964*
11. **Edward M. Riley** *Startin America The story of independence Hall USA 1990*
12. **Eric Freedman and Edward H** *J F. Kennedy In His Own Words NY 2005*
13. **Gary De Mar** *America's Christian Heritage 2003*
14. **George Sullivan** *MR. PRESIDENT A Book of U.S.A Presidents 2001*
15. **Harry Smith** *Ultimate Biography 2002 USA*
16. **Hastin, Mason & Pyper** *The Oxford Companion to Christian Thought.,*
17. **Jacob E. Safra & Ian Yeshua** *The new Encyclopedia Britannic Chicago 2002*
18. **Jackie Staddon** *Baedeker's USA New York 2000*
19. **Jerry Combee, Laurel, Mike** *The modern Age Vol 2 1991 USA*
20. **Jeffrey B. Webb,** *the complete Idiot's Guide to Christianity New York 2004*
21. **John Escott** *California. Oxford university Press 2001*
22. **John Gay Y.** *Christianity In Ethiopia and Eritrea 1998 Amman Jordan*
23. **John McManners** *The Oxford Illustrated History Christianity 1992 New York*
24. **Lutz Norma Jean** *The History of the Black Church USA 2001*
25. **Mark A. Noll & Nathan O. Hatch** *Christianity in America USA 1983*
26. **Marie and Douglas Gorsline** *North American Indians New York 1977*
27. **Michael A. Schuman** *M. L. king, JR. Leader for Civil Rights 1996*
28. **Michael Collins &Matthew** *The story of Christianity New York 2000*
29. **Marilyn Heldman** *A. Zion the sacred art of Ethiopia p. 107 London 1993*
30. **Nancy Hartley** *Quick Facts about the USA New York 1994*

31. **Patricia S. Daniels &Stephen G. B.** *Almanac Of World History USA 2003*
32. **Peter E. Gillquist** *Becoming Orthodox California 1992*
33. **Robert S.** *Cobble Stone the History magazine for young people USA 1984*
34. **Richard Deats** *M. L. King, Jr. Spirit-Led Prophet Great Britain 1993*
35. **Steck-Vaughn** *Social Studies 1996 USA*
36. **Steck Vaughn** *PRE-GED Social Studies 2000 USA*
37. **Stephanie Abraham H.** *States and Regions., 1985 USA*
38. **Susan Altman** *The Encyclopedia of African- American Heritage 1997*
39. **TIME** *The Year In Review 2004*
40. **Toby Mac and Michael Tait** *Under God 2004 USA*
41. **Warren J. Halliburton & William Loren katz** *American Majorities and Minorities 1970*
42. **William O. Kellogg** *American History the Easy Way St. Pole's School Concord, NH, New York 1995*
43. **Wubalem Fekade A** *Tale of Two Nations DC. USA 2004*
44. **ተክለ ጻድቅ መኩሪያ** *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ሦስተኛ መጽሐፍ ታኅሣሥ 1 ቀን 1966 ዓ. ም.*
45. **ጌታቸው ኃይሌ** *ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቀመሩ ቅርሳችን ከታሪክ ግ. ጋራ ኮሌጂቪሊ ሚኒሶታ 1993 ዓ. ም.*
46. **ሉሌ መልአኩ ፤** *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አዲስ አበባ 1986 ዓ. ም.*
47. **ዓለማየሁ ማሞ -** *መኖር በአሜሪካ ቀሽንግተን ዲ.ሲ. 1998 (2005)*


## ጋዜጦች እና መጽሔቶች
## News paper & Magazine


1. **Martha Mengesha** *A Tale of Two Nations Washington, DC 2003*
2. **Extra Ze** *Ethiopia April 2 , 2004*
3. **Jefferson Morley,** *Reader's Digest , The New Clue to JFK's Murder (March 2005)*
4. TADIAS *Ethiopian – American Lifestyle & Business Magazine March/April 2005*
5. **ማኅተም** *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 ሰኔ 15 ቀን 1994 ዓ. ም. (June 22, 2002 USA)*
6. **ነጸብራቅ ፤** *በስደት ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሔት መስከረም 1996 ዓ.ም.ቁጥር 8 (September, 2003 V. '10)*
7. **Guardian** Co. *UK Friday October 7, 2005*
8. **SocialistWorker** *UK 29 April 2006*
9. **ሰላም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጀርመን ሚ.** 1985 **ዓ. ም.**




## ጥናታዊ ፊልሞች
## Documentary films

1. **PBS HOME VIDEO** Abraham Lincoln Collection 1994
2. **PBS HOME VIDEO** Malcolm X Biography
3. **PBS HOME VIDEO Alfre Woodard** Underground Railroad
4. **PBS HOME VIDEO** Harry Louis Gates, Jr. AFRICAN WORLD documentary
5. **PBS HOME VIDEO** SCOTTSBORO An American Tragedy 2001
6. **PBS HOME VIDEO** Eyes On The Prize America's Civil Rights Years 1954 –1965
7. **PBS HOME VIDEO** Citizen KING

## Websites of Christian Denominations

| | |
|---|---|
| The Vatican Catholics | www.vatican org |
| Orthodox Church in America | www.oca.org |
| Church of England | www.cofe.anglican.org |
| Episcopal Church in the USA | www.episopalchurch.org |
| Lutheran Church History | www.lcms.org |
| Presbyterian Church in America | www.pca.net |
| Reformed Church in America | www.rca.org |
| Mennonite Church in America | www.mennonites.org |
| Moravian Church | www.moravian.org |
| Baptist Churches in the USA | www.abc-usa.org |
| United Methodist Church | www.umc.org |
| Quakers Religious Society of Friends | www.evengelical-friends.org |
| Pentecostal Churches | www.ag.org |
| Mormons | www.morman.org |
| Seventh - day Adventist | www.adventist.org |
| Jehovah's Witnesses | www.watchtower.org |
| Christian Science | www.tfccs.org |



መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

ኮሎምቦስ አሜሪካንን ከማግኘቱ ከ1000 ሺ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ተሰብኳል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቅድስት አገር ነች። አውሮፓውያን ለብዙ መቶ ዓመታት ክርስቲያን ሳይኾኑ ኢትዮጵያ የክርስቲያን አገር ነበረች።

የኤጲስሎፓል ቤ.ክ. አባል አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ሄነሪ ልዊስ።
(Harry Louis Gates, Jr. AFRICAN WORLD VIDEO documentary)

በማንበብ ትምህርት ማግኘትና የነበረውን ማዳበር ይቻላል። ይህ ጽሑፍ በዚህ መልኩ ትልቅ ሥፍራ አለው። ስለዚህም ነው ደራሲው በመነሻቸው ላይ ያስቀመጡት ዓቢይ ዓላማ ዕውን ኾኗል ለማለት የምደፍረው። በመጨረሻም ጽሑፉን በማንበብ ሐሳቤን ለመስጠት ብቻ ሳይኾን ብዙ እንድማር ዕድል ስለሰጡኝ አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር ሥራዎትን ከፍጻሜ እንዲያደርስልዎ ምኞቴ ነው።

ዶክተር ሰሎሞን አፈወርቅ

ይህ መጽሐፍ በአገር ውስጥም ኾነ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቢያነቡት ስለ አሜሪካ ኑሮ እና የክርስትና እምነት ጠቃሚ ዕውቀት፣ ግንዛቤ ሊያገኙ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ። ደራሲው ጠለቅ ያለ ጥናታዊ ጽሑፍ በማቅረባቸው ያለኝ አድናቆት ከፍተኛ ነው።

ዶክተር ማንደፍሮ በላይነህ

በቅርቡ ተከትለው የሚወጡ

- የመጠሪያ ስሞች
- ፍኖተ ኦርቶዶክስ ዘተዋሕዶ
- ኑሮ እና ክርስትና በብሪታንያ

Printed HY International Printers
Tel. 251-11-553 90 95

ዋጋ ብር 30
$ 20, £ 15, € 15